የማዕበል መንገደኞች

t.me/BooksandYou

በዓለማየሁ ማሞ

(ዋሽንግተን ዲሲ)

2005 በኛ 2013 በነርሱ

ወጀቡን አልፎ በጽናት ለቆመው ጓደኛዬና ወንድሜ
መጋቢ ምንይልክ ታምራት

የማዕበል መንገደኞች
ኮፒ መብት © 2005 ዓለማየሁ ማሞ
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
የናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ

Sailors in the Storm
Copyright © **2013** Alemayehu Mammo
All rights reserved
United States of America

ISBN 978-1-61119-138-7

Contact
alemayehudmammo@gmail.com
Call 240 560 ALEX (2539)
www.alemayehu.org
P.O.Box 12204
Silver Spring, MD, 20908

ማውጫ

1)ትንታኔው

ጥቂት ስለማዕበል.....6
ውስጣዊ ማዕበል.....11

2) ባሕርዩ

በድንገት.....24
ተደርቦና ተደራርቦ.....30
የማይቀር ዕጣ.....33

3) እውነታው

ጌታ ቢኖርም….....36
ይናፈቃል ፤ ያስናፍቃልም….....46
የማለፋችን ተስፋዎች….....52
ምርጫ ነው!.....54

4) በረከቶቹ

የሚያስጠጋ ማዕበል…….....60
ወጀብ ይለያል.....67
በማዕበል ውስጥ መሠራት….....73

5) ማዕበሉን ለማለፍ

ሀ) ራስን ማዘጋጀት….....81
ለ) ቀድሞ መጸለይ…….....86
ሐ) ድምፆችን መለየት….....92
መ) የተሻለውን መምረጥ….....104
ሠ) አመለካከትን መቀየር….....108
ረ) ጠንክሮ መዋጋት….....113
ሰ) ትክክለኛ ርምጃ መውሰድ.....119

መግቢያ

በቀዳማዊው ጆርጅ ቡሽ አዝማችነት አሜሪካውያን ሳዳም ሑሴንን ለማንበርከክና ኩዌትን ነፃ ለማውጣት ሠራዊታቸውን አስከትተው ነበር። ይህንኑ ዘመቻም የበረሃው ማዕበል ሲሉ ሰይመውታል።

በባሕረ ሰላጤው ውጊያ በግንባር ቀደምትነት ከተጠቀሙባቸው ታንኮች መካከል "ሐመር" የተሰኘውና አሸዋ የማያቆመው ተንከባላይ ብረት በፊተኛው ረድፍ ይጠቀሳል። ከዚያ በድል ሲመለሱም የዚህኑ ታንክ ሞተር ለመኪና መሥሪያ ስላዋሉት በተጠቃሚዎች ዘንድ ትልቅ ተቀባይነትን አግኝቷል። ቁልል በረዶ ሳይበግረው በአውራ መንገዶች ላይ በፈሰሰ ቁጥርም የበረሃውን ማዕበል ለሁሉ እያስታወሰ ነው።

ወደ አገራችንም ስንዘልቅ ብዙ ትከረትን ስቦ ስለነበረና የማዕበል ዋናተኞች ስለተሰኘ ድራማ በተደጋጋሚ ሰምቻለሁ። አንዱ አርቲስት በ1970ዎቹ መጨረሻ ፍቅርን ከማዕበል አመሳስሎ አዚሞበት እንደነበርም የምንዘነጋው አይደለም።

ማዕበል የውኃ መናወጥ ነው።

ነውጡ በሐይቅ ፤ባሕር ወይም ውቅያኖስ ላይ ተደጋግሞ ይታያል። እንደ ቀድሞ መርከበኛ ማዕበልን ከነግርማው አውቀዋለሁ። እሹሩሩ ከሚለው ለስላሳ የውኃ

ንቅናቄ ጀምሮ በታላቅ ድንፋታ እስከሚገፋተረው ወጀብ ድረስ እስኪበቃኝ ቀምሼዋለሁ። የዚህች መጽሐፍ ዓላማ ግን ውኃው በመርከቦችና በውስጡም ባሉ ሰዎች ላይ የሚያደርሰውን እንግልት መተረክ አይደለም። ይልቁንም እንደ ማዕበል ስለሚያንገላታን ምድራዊ ኑሮ ግንዛቤን ማስጨበጥ ነው።

ከምንም ይልቅ የዚህች ጥራዝ ተልዕኮ የማዕበል መንገደኞች መሆናችንን ማስታወስ ነው።

ስለሆነም በማዕበል የተመሰሉትን ስደትና መከራን ሌሎቹንም ተመሳሳይ አሳቦች በተነጻጻሪ ለመተንተን ሞክሬያለሁ። ተዛማጁን እውነታም ከባሕርያቸው ጋር አዳምሬ ዳስሻለሁ። ማዕበሉ የሚያመጣውን ንጦሽ ብቻ ተርኬ አላቆምኩም። ይህም አለ እንዴ ካላሰኘ በቀር ጥቅማጥቅሙንም በጥቂቱ ጨለፍ አድርጌያለሁ። በመጨረሻም ማዕበሉ መምጣቱ ሞገዱም መነሣቱ ካልቀረ አልፈነው ለመሄድ እሚረዱንን ጥቂት ነጥቦች አንስቻለሁ።

መልካም ንባብና መልካም ጉዞ

ዓለማየሁ ማሞ

ሲልቨር ስፕሪንግ (ሜሪላንድ)

ግንቦት 2013

1

ትንታኔው

ጥቂት ስለማዕበል

የዕለቱን ዜና ስንሰማ፤ ስናነብ ወይም ስንመለከት ቀዳሚ ርዕስ የሚወስዱ አንዳንድ ክስተቶችን ልብ እንላለን። ለምሳሌ ‘‘እከሌ በዛሬው ውድድር የዓለምን ክብረ ወሰን ሰበረ’’ የሚል ሊሆን ይችላል። ወይም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ መደረጉን በድንጋጤ እንሰማ ይሆናል። እነዚህ ከአለፍ አገደም ብቅ የሚሉና የዜናዎቹን የፊት ረድፍ የሚያጨናንቁ ወሬዎች ናቸው። ያም ሆነ ይህ ግን ማዕበል ካለ ያለጥርጥር የዕለቱ ዜና ርዕስ ነው። ማዕበል ብለን ከዚህ በኋላ የምናነሳው የግድ የውኃውን ያለቅጥ መንቦጫረቅ ላይሆን ይችላል። ግን ወሬውም ይሁን ግብሩ ሰዎችን ከሰላማዊ ኑሮ የሚነቀንቅ ብሎም አካባቢን የሚያናውጥ ከሆነ ያንን ማዕበል ብለን ነው እምንቀጥለው። ከምንም ይልቅ ማዕበል አናዋጭ እንደመሆኑ አንዳንዴም ነውጥ በሚለው ቃል እየተካን እንጠቀምበት ይሆናል።

ከላይ እንዳልነው ማዕበል እንዲያውም እንደ ኃይሉ መጠን ሰበር ዜና ሊሆንም ይችላል። ማዕበል በተለያዩ መልኮች ራሱን ይገልጣል። ቢሆንም በሚገባ ከምናውቃቸው መሃል ዶፍ ዝናብ፤ ዐውሎ ነፋስ፤ ሰደድ እሳት፤የመሬት

መንቀጥቀጥ፤ ጎርፍ፤ ናዳ፤ በረዶ፤ ሱናሚ፤ እሳተ ገሞራ ወይም ወጀብ መገለጫዎቹ ሊሆኑን ይችላሉ። ጦርነትም ከሁሉ የባሰ ነውጥ ነው።

ዶፍ ዝናቡ መጀመሪያ እንቅስቃሴን ይገታል። ከጉዞ ያዘገያል። እየገፋ ሲሄድ መሬትን ሸርሽሮ ወይም ኃይለኛ ጎርፍ አስከትሎ በሕይወትና በንብረት ላይ ቀላል የማይባል ጉዳትን ያስከትላል።

ዐውሎ ነፋሱ ብዙ የተደከመባቸውን ዕድሜ ጠገቦቹንም ሳይምር ዛፎችን ገንድሶ ወደፈለገበት አቅጣጫ ይጥላቸዋል። በዚህም መንገድ ይዘጋል። የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ግንዶችን አጋድሞና መስመሮችን በጣጥሶ ቤቶችን ያለ መብራት ያስቀራል። ያለ ኤሌክትሪክ መላወስ የማይችሉትን ሆስፒታሎችና የአዛውንቶችን መጦሪያ ሥፍራዎች ሳይቀር በጨለማ እንዲዋጡ ያደርጋል። ካሻውም እንደ ጉልበቱ መጠን ጣሪያ ሊገነጥል ቤትን ሊዘነጥልም ይችላል። በውስጡ የሚኖሩትንም በአንድ ጀምበር ቤት የለሽ ያደርጋቸዋል።

የመሬት መንቀጥቀጥ ለዘመናት የተደከመበትን የከተማ ግንባታ በጥቂት ደቂቃዎች ዶጋ አመድ ከማድረግ አይመለስም። በጥብቅ የሚጠበቁ የኑክሊየር ኃይል ማመንጫዎችን ይተናኮላል። የሰው ልጆችና እንሰሳቱንም ቢሆን ገና ሳይሞቱ በቁማቸው ለመቅበር አያመነታም።

ጎርፉ በተራው በፊት ለፊቱ ያገኘውን ሁሉ ጠራርጎ ወዳልታዘዘበት ሥፍራ እየተሸከመ ያግዛል። ወዳልተጠራበት ቤት፤ አዳራሽ ወይም የኳስ ሜዳ ገብቶ ዙሪያ ገባውን ያጥለቀልቃል። አገሩን ሁሉ የመዋኛ ገንዳ ወይም ድንበር የለሽ ኩሬ አድርጎት ይሄዳል። የደረሰውንና በግልና በሕብረት ብዙ ላብ የፈሰሰበትን እህል የገበሬው ዓይን እያየ እስከ አናቱ ይውጠዋል። አልፎ ተርፎም ለወባ ትንኝና ለሌሎችም ያልተፈለጉ ነፍሳት መራቢያ ይሆንና ተላላፊ በሽታዎችን ያስከትላል።

ናዳ ሁሌም ዱብዳ ነው። ከተራራ በታች የሚኖሩ የስጋት ጎረቤት የሚሆኑትም ስለዚህ ነው። አንድ ቀን ያለ ማስጠንቀቂያ ጉማጁን ልኮ ይጠርጋቸዋል። ንብረታቸውንም ያደባያል።

በረዶም በተራው ከልኩ ሲያልፍ መንገዶችን ይዘጋል። ያን ተከትሎ ትምህርት ቤቶች አምራች ድርጅቶችም ሆኑ መንግሥታዊ ተቋማት መዘጋት የግድ ይሆንባቸዋል። የዕፅዋትን ቅጠል አራግፎ ልምላሜያቸውን ገፍፎ በጭራሮ ያስቀራቸዋል። ይህ ነው ተብሎ የማይነገር ገደብ የለሽ ቅዝቃዜ ይልከናም የአዳምን ዘር አቅም ይፈትናል። በኃይለኛ ቆፈን ያስመርራል። ትንንሾችንና አዛውንትን ደግሞ ከልክ በላይ ይዳፈራል። ከቁር የተነሳ የሚሞቱም አሉ።

በቅርቡ የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት የሳበው አደገኛው የባሕርና ውቅያኖስ ማዕበል ወይም ሱናሚ በእሳተ ገሞራ በመሬት ወይም በባሕር ወለል ነውጥ ሳቢያ ብቅ የሚል ነው። ለምሳሌም በ2004 (እ.አ.አ) የሕንድ ውቅያኖስን ያናወጠው ሱናሚ በትንሹ ሁለት መቶ ሠላሳ ሺሕ ሰዎችን ገድሎአል።ይህ በሆነ በሰባት ዓመቱ ደግሞ ሰሜናዊ ምስራቁን የጃፓን ግዛት የመታው የመሬት ነውጥና አደገኛ የውቅያኖስ ማዕበል በሺሕ የሚቆጠሩትን ቀጥፎ በሚሊዮን የሚገመት ንብረት አውድሟል።

ወጀቡ በበኩሉ የመርከበኞችን ሕይወት ያኮመጥጠዋል። በፈለገው ጊዜና ሰዓት ባሕርና ውቅያኖሱን ያምሳል። ተጓጉችን መከራ ያበላል። የበሉት እሆዳቸው እንዳይረጋ እየናጠ ያስተፋቸዋል። ጀልባና መርከቦችን ይሰብራል። ሲመቸውም ይገለብጣል። እንዲያም አድርጎ ያሰጥማል። በዚያም መርከብና ጀልባን ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም ይውጣል። ክቡሩን የሰውን ልጅ ለዓሣ እራት ያደርገዋል። አንዳንዴም የውቅያኖሱ አልበቃ ብሎት የባሕሩ አንሶት ውሃው ጠረፉን አልፎ ይመጣና ሌላ ጉዳት ያደርሳል።

ከሁሉ የከፋው ነውጥ ደግሞ ጦርነት መሆን አለበት። የርስ በርስም ይሁን በአገሮች መሃልም ይደረግ የርሱ ጭዳ ክቡሩ የሰው ሕይወት ነው። ሰው እየተኮሰ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሌላ ሰው የሚፈጅበት አሳዛኝ

ትዕይንት ጦርነት እንጂ ሌላ አይደለም። ጦርነቱ አበቃ ወይም ባንዱ አሸናፊነት ተደመደመ ለማለት እንኳ የሚቸግር ነው። ተሸናፊው አንድ ቀን ጊዜ ሲያነሳው ጦር ሰብቆ ተመልሶ ይመጣልና። በዚያ ላይ የጦርነቱ ሰለባዎች አሉ። የደረሳባቸውን የአካል ጉዳት የአእምሮም ሕውከት ተሸክመው በሕብረተሰቡ መካከል ስለሚኖሩ ያን በአንድ ወቅት የተካሄደ ውጊያ መርሳት ያዳግታቸዋል። ጦርነቱ ካበቃ ከዓመታት በኋላም ቢሆን እነርሱ ጠባሳውን ይዘው ይዞራሉ። እነዚህ ከላይ ያየናቸው ጥቂት የማዕበል መገለጫዎች አንዳቸውም ለሰው ልጅ ወዳጅ አይደሉም። ለየብቻ መምጣታቸው ሳያንስ ተቀናጅተው የሰውን ልጅ መከራ ሊያበሉት ደግሞ ይችላሉ። ለምሳሌ ነፋስና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ መጣ ሲባል በማሳው ላይ ላለው ሰብል ጤና እንደማይሰጠው ግልጽ ነው።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ ሌሎችም ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች አናዋጮች ናቸው። ልክ ማዕበሉ መርከቦችን እንደሚያንገላታቸው ከግራ ወደ ቀኝም እንደሚያላትማቸው እንዲሁ የሰውን ልጅ ያደርጉታል። ይንጡታል። ያፈናቅሉታል። አንዳንዶቹን እንጂ ሁሉንም ማስወገድ ደግሞ አንችልም። ናዳውን በእርከን መገደቡ ተሳክቶልናል። ዐውሎ ነፋሱን ግን ለመከልከል የሚያስችል ቴክኖሎጂ አላገኘንም። እናም ነውጡ አብሮን ይኖራል። ለዚህ ነው የማዕበል መንገደኞች መባላችን።

ውስጣዊ ማዕበል

ከላይ የተነሡትን ጨምሮ ውጫዊ የሆኑት ነውጦች በተረጋጋው ሕይወት ላይ የሚያመጡት መመሳቀል እንዳለ ሆኖ ነውጡ ውስጣዊ ሲሆን ደግሞ እማይሸሹት እውነታ ሆኖ ይደቀናል። ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደሚኖር ከታወቀ የአካባቢው ነዋሪዎች ቀዬአቸውን ለቀው ሰላማዊ ነው ወደሚባለው ሥፍራ ሊፈልሱ ይችላሉ። ወይም ታላቁን አውሎ ነፋስ ከመሬት ሥር በተሠራ መጠለያ ውስጥ ተሸሽገው ሊያሳልፉት ይችሉ ይሆናል። በተለይ ከምድር በታች የተሠሩ ምሽጎች በጦርነት ቀጠና ለሚኖሩ ሰዎች እንግዳ አይደሉም። ግን ነውጡ ወደ ግለሰብና ወደ ቤተሰብ ከመጣና ከውጫዊ ይልቅ ውስጣዊነቱ ዐይኑን ያፈጠጠ እውነታ ከሆነ ማምለጫ ወይም መሸሸጊያ አይኖርም። ያኔ ችግሩ ከግለሰቡ ጋር አብሮ ውሎ ያድራል እንጂ የትም አይሄድም።

“ዋናው ነገር ጤና” እንዲሉ ከዚያው እንነሳ። ለብዙዎች የሐኪም ሪፖርትና የምርመራው ውጤት አበረታች አይደለም። ከሆስፒታል ወይም ከሕክምና ጣቢያ ተደውሎ “ባደረግኸው የሕክምና ምርመራ ውጤት ከልክ በላይ ተደንቀናል፤ ይህ ነው የሚባል ጉድለት ባንተ ላይ ማግኘት አልቻልንም። እንኳን ደስ ያለህ! ሙሉ ጤነኛ ነህ” የሚል ሪፖርት የሰማው ሰው ቁጥር እጅግ ጥቂት ነው። ለዚህም

ብዙ ተጠቃሽ ምክንያቶች አይጠፉም። ከኑሮ ሩጫ ባሻገር በቂ ዕረፍትና እንቅልፍ ያለማግኘት ያለንበት ክፍለ ዘመን አንዱ አሳዛኝ ገጽታ ነው። ጣራ የነካው የሕክምና ሳይንስ አበክሮ እንደሚነግረን ከሆነ ሰውነታችን ተገቢውን ዕረፍት ካላገኘ በቀር ሕዋሦቻችን እንደሚገባ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ይቸገራሉ። በሌላ አነጋገር አቅመ ቢስ ይሆናሉ። ያም ሳይበቃ በቂ እንቅልፍ ካልወሰደን ንቁ መሆናችን ቀርቶ ፈዘን እንደምንውል ሳይታለም የተፈታ ነው። በተለይም ያለመኪና አጋዥነት መኖር በማይቻልባቸው የሠለጠኑ አገሮች እየነዱ ማንጎላጀት አንዱና አሰቃቂው የአደጋ መንስዔ ነው። በገሚሱ በተገለጠ ዐይን መንዳትና የዙሪያ ገባውን እንቅስቃሴ መቆጣጠር አይቻልም። እረፍት ባጣ አእምሮ ፈጥኖ እርምጃ መውሰድና አደጋን መቅረፍ የማይሞከር ነገር ነው።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለዋወጠ የመጣው የምድራችን የአየር ጠባይ ሌላው መከራ ነው። ከካችምና አምና ከአምናም ዘንድሮ ሙቀት እየጨመረ መሄዱ የዕለት ተዕለት መነጋገሪያ ሆኗል። የምድራችን ሙቀት ሚዛን ለመጠበቅ ይረዳል የሚባለው በዋልታዎች ያለ የበረዶ ግግር እየቀለጠ ነው። ያም ሳይበቃ የአየሩ ንብረት ሊተነበይ በማይችል ፍጥነት ሲለዋወጥ ይስተዋላል። አየሩ ፈጥኖ በተቀየረ መጠን ሰውነታችን ራሱን ለማላመድ ይቸገራል። የጉንፋን፤

ኢንፍሉዌንዛና አለርጂ ወረርሽኝ የሚበዛው በወቅቶች ፍርርቅ ጊዜ መሆኑ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ሳይኖረው አይቀርም።

በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ያለውን የሕዝብ ቁጥር የሚመጥን ምግብ ለማቅረብ አልተቻለምና ያ ደግሞ በተራው ሌላ ማዕበል አስከትሎአል። የሚታረሰው መሬት እያነሰ ሲሄድ የበላተኛው ቁጥር ደግሞ ጣራ እየደረሰ ነው። ታዲያ በመስኩ የተሰማሩ ባለሙያዎች ይህንን ችግር ለመቅረፍ የመቱት መላ ጊዜያዊ መፍትኼነቱ ባያጠራጥርም ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሥራ ላይ የዋሉ የሳይንስ ውጤቶችም የማታ ማታ ሌላ ፈተና እየሆኑ ነው። ከነዚህ ውስጥ በተለይም የምግብን ሰብል በፍጥነትና በብዛት ለማምረት የሚያግዙ ማዳበሪያዎች ፤ የተመነደሡና የተዳቀሉ አዝርዕት፤ እንሰሳት በቶሎ አድገው ለቀለብ እንዲደርሱ የሚያግዙ ሆርሞኖች እንዲሁም ምግብን ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ የሚረዱ ንጥረ ነገሮች ለዚህ ዓይነተኛ አስረጂ ሊሆኑ ይችላሉ። ተጠቃሾቹና ሌሎችም የቴክኖሎጂ ግብአቶች ከጊዜ በኋላ በበላተኞች ላይ የሚያስከትሉት የጤና መዘዝ በጤና ሳይንስ ሙያ ላይ የተሰማሩትን እጅግ አሳስቧል። ምግቦቹ ተፈጥሮአዊ ባሕርያቸውን ለቅቀው ወደሰው ሠራሽነት ማዘንበላቸው በውስጣቸው ሊይዙት የሚገባውን አስፈላጊ ንጥረ ነገር ማጣታቸው ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እንዲልቅ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል። በተለይም ለፈጣኑ ትውልድ

ፈጣን ጥጋብ የታቀዱት ፈጣን ምግቦች ፈጣን ገዳዮች ተብለው ከተፈረጁ ሰንብተዋል። በነዚህና ሌሎችም በቅባትና በስብ የበለጠጉ ምግቦች ሰበብ ፈጣኑ ትውልድ በበርካታ በሽታዎች እጅግ ፈጥኖ እየተለከፈ ነው። በተለይም የደም ስብ መጨመር፤ የስኳር ሕመምና ከፍተኛ የደም ግፊት ወቅት የማይጠብቁ ወረርሽኝ ሆነው ተሰልፈዋል። የነዚህ በሽታዎች አስከፊነት ደግሞ በየግል ከሚያደርሱት ጉዳት የከፋ ነው። ለምን ቢሉ አንድ ላይ በማበር የልብ ሕመምን ያስከትላሉ። የልብ ሕመም ደግሞ ከዘመናችን ገዳይ በሽታዎች አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው። ከላይ የተዘረዘሩትን ተከትሎም ይሁን ራሱን ችሎ ባለቤቱን ሳያስፈቅድ ሰውነት ላይ ጉብ የሚለው የበሽታ ዓይነት ስንት እንደሆነ ቤቱ ይቁጠረው። ግን ከዓመታቱ ስቃይ የመጀመሪያው ቀን መርዶ የበለጠ እንደሚያስደነግጥ እሙን ነው። ቀጥሎ እንደተጠቀሱት አዛውንት ዜናውን አቅልሎ ማየት አዳጋች ነውና። ጮማ ሲበሉና ጠጅ ሲጠጡ የኖሩት እኒሁ አዛውንት ልጆቻቸውን ለመጎብኘት ወደውጭ አገር ብቅ ይላሉ። ልጆቻቸውም አገሩን ከእግር እስከራሱ አዙረው ካስገበኟቸው በኋላ አጋጣሚውን ተጠቅመው ጠቅላላ የጤና ምርመራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸዋል። መጀመሪያ ላይ ሽማግሌው በአሳቡ አልተስማሙም። በጣም ጤነኛ ነኝ ባይ ነበሩ። ልጆቻቸው ግን በደረሱበት ዕድሜ ለጤናቸው ማሰብ ተገቢ

እንደሆነ ያለመታከት አስረዷቸው። ለአዛውንት በሚሰጠው የነፃ ጤና ሕክምና እንዲጠቀሙም አግባቧቸው።በዚሁ ተስማምተው ይሄዱናም የደምና ሽንት ናሙና ሰጥተው ራጂም ተነስተው ይመለሳሉ። የምርመራቸው ውጤት ተመላሽ ከሆነ በኋላ ደግሞ ሌላ ቀጠሮ ተይዞላቸው የዶክተሩን ምክር ለመስማት በቢሮው ይገኛሉ። እርሱም የደምና ሽንት ምርመራውን ውጤት በማንበብ የራጂውንም ምስል እያገላበጠ በማየት በበኩሉ የተረዳውን ተራ በተራ ይዘረዝራል።

‘‘ጥቂት የማይባሉ ችግሮችን በምርመራዎ ላይ አይቻለሁ’’

‘‘እንስማዋ!’’

‘‘ ጉበትዎ መጠነኛ መመረዝ ያሳያል’’

‘‘ ካቲካላዋ ትሆን?’’

‘‘ ኩላሊትዎም ቢሆን ጥሩ ሁኔታ ላይ አይደለም’’

‘‘ በጂ’’

‘‘ ጨጓራዎ ክፉኛ ተነክቷል’’

‘‘ባይነካ ነበር የሚገርመኝ፤ ስንቱን ችዬ ነው የኖርኩት’’

እንዲህ እንዲህ እያለና ዘና ብለው በተቀመጡት አዛውንት ግድየለሽነት እየተደነቀ በመላው ሰውነታቸው ቢሮ

የከፈተ የሚመስለውን ግን በዘመናት መሃል ያጠራቀሙትን የበሽታ መዓት ሲያስተዋውቃቸው ቆየ። በተለይ የደም ስባቸው ከፍ ማለቱን ስኳራቸውም ጠርዝ ላይ መድረሱንና የደም ግፊታቸውም ወደላይ መውጣቱን አበክሮ አስታወቃቸው። ሪፖርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ደግሞ ያልገባቸው ነገር መኖሩን ጠየቀ።

‘‘ አሳምሮ ገብቶኛል፤ ግን ጥያቄ አለኝ’’ ይላሉ።

‘‘ ምን?’’

‘‘ ልቤ እንዴት ነው ዶክተር?’’

‘‘ ልብዎ ለጊዜው ችግር የለበትም!’’

‘‘ልቢቱ ሰላም ናት?’’

‘‘አዎን ከላይ ያልኳቸው ችግሮች ወደፊት ልብዎ ላይ ሳንካ ካልፈጠሩ በቀር አሁን ልብዎ ጤነኛ ነው’’

‘‘እንግዲያውስ አትስጋ’’

‘‘ እንዴት’’ አለ ሐኪሙ ግራ በመጋባት።

‘‘አየህ ለወንድ ልጅ ዋናው ልቡ ነው!’’

በዚህ ሁሉ የበሽታ አጥር ተከበው በልቤ ጤንነት እኖራለሁ ወይም ልቤ እስከ መጨረሻው ሰላም ይሆናል ብለው ማሰባቸው ፈገግ ያስደርጋል። ግን ገና ኮሽ ሲል የሚይዙትና እሚጨብጡትን ከሚያጡት የተሻለ ድፍረት ማሳየታቸው እሙን ነው። ነገሩንም ከምር ይልቅ ቀልድነቱን

ያጎላዋል። ዋናው ነገር ግን የቁርጥ ቀን ሲመጣ እንዲህ ዓይነቶቹን የሐኪም ሪፖርቶች በሽተኛው ዘና ብሎ ይሰማቸዋል ወይ የሚለው ነው። መልሱ ያለማመንታት ‘‘ፈጽሞ’’ የሚል ይሆናል። እንዲያውም ከላይ ከአዛውንቱ በተቃራኒ ቆመዋል ላው ወገኖች ብሎም ለብዙዎች ምላሹ ከዚያም የዘለለ ነው። እንዲህ ዓይነት በሽታ አለብህ ብሎ ዶክተሩ ንግግሩን ሳይጨርስ ራሳቸውን የሚስቱ አይታጡም። እዬዬ የሚሉ ቢኖሩ ወይም ‘‘እኔ እንኳ በልቻለሁ፤ ጠጥቻለሁ ወየው ልጆቼ’’ ባዮች ቢያጋጥሙ ለባለሙያዎቹ ይህ አዲስ አይደለም። ገዳይ በሽታ እንደተጠናወታቸው ሲሰሙ ማምሻቸውን ይሞቱ ይመስል የሬሣ ሣጥን የሚታያቸው ሰዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም። ውስጣዊው ማዕበል ወዲያውኑ ይጀምራል። በሽተኛውም ከተነገረው ታላቅ ወይም ታናሽ መርዶ በተጨማሪ ‘‘ ጭንቀት’’ የተሰኘውን ሌላ ችግር አክሎበት ይወጣል። ያ እንግዲህ ዓይነተኛው ዉስጣዊ ማዕበል መሆኑ ነው።

ከላይ እንደጠቀስነው የጤናን ጉዳይ ያስቀደምነው እንደ ዋና ነገር ስለተቆጠረ እንጂ የዉስጣዊ ማዕበል መንስዔዎች እጅግ በርካታ ናቸው።

መለያየት ሌላው የማዕበል ምንጭ ነው። አንዳንዶች ‘‘ ከዓይን የራቀ ከልብ የራቀ ነው ’’ ሲሉ ይደመጣሉ። ጥቂት እውነትነት አያጣም። ግን የልብ ርቀት የሚወሰነው በፍቅሩ

ጥልቀት ልክ ሳይሆን ይቀራል? ከልብ የምንወደውን ሰው መለየት በእውነቱ ቀላል ፈተና አይደለም። እንዲያውም የመለያየት ቀናት በጨመሩ ልክና በገፉ ቁጥር ናፍቆቱም የዚያኑ ያህል እየበረታ ይሄዳል። እንዲያውም የዕለት ተዕለት ኑሮ እንኳ አዳጋች እየሆነ ሊመጣ ይችላል። መለያየትን ከሞት ጋር አነጻጽረው ያቀነቀኑ በርካታ ድምፃውያን አሉ። እርሱም ቢሆን በሁለት ዓይነተኛ መንገዶች ማለትም ጊዜያዊና ዘላቂ ራሱን ሊገልጥ ይችላል። ጓደኛን ወይም ፍቅረኛን ማጣት የጊዜያዊው መለየት ጥሩ ምሳሌ ነው። ራስን ከአንድ ሌላ ግለሰብ ጋር በፍቅር ወይም በጥብቅ ጓደኝነት ለማቆራኘት የሚፈጀው ጊዜና የሚያስከፍለው ዋጋ እንዳለ ሆኖ ከዕለታት በአንዱ ቀን የዘመናቱ ሕልም ብን ብሎ ሲጠፋ ዙሪያው ይጨልማል። ይሆናል ተብሎ ያልታሰበው ሲከሰት ናላ ያዞራል። ዕይታን ያጥበረብራል። አብረው ውለው ለአዳር መለያየቱ ይጨንቃቸው የነበሩ ፍቅረኛሞች ለወራትና ዓመታት ሲራራቁ ኑሮአቸው ይኮመጥጣል። የሥራ ዝውውር ወይም አገርን ለቅቆ መውጣት ብዙዎችን ያራርቃል። በፍጥነት እያደገ ያለው የከተሞች መስፋፋት አብረው አፈር የፈጩትን የከንፈር ወዳጆችና የልጅነት ፍቅረኛሞች ያለርኅራኄ ይለያያል። በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት የሚፈጠረውን ያለመግባባት ተከትለው ‘‘መቃብሬ ላይ እንዳትደርስ’’ የሚባባሉም ጥቂት አይደሉም።

የመለያየት ነውጥ ለሁለቱም ተጓዳኞች የማይቀር ቢሆንም አንደኛው ግን የበለጠ የሚጎዳበት አጋጣሚ ደግሞ ብዙ ነው። ይልቁንም የመለያየቱ ሰበብ የአንድ ወገን ስሕተት ከሆነ ፈጥኖም ይሁን ቆይቶ ለፀፀት መዳረጉ መራር እውነት እንጂ ጣፋጭ ትውስታ አይደለም። በንግግር ከሆነ አፈን በድርጊት ከሆነ ደግሞ እጄን በቆረጠው ሲል የሚኖር ካለ እርሱ በዳይ ነው። መለያየቱ ሳያንስ በደለኝነት መከራ ያበላዋል። ከዚያም አልፎ እንቅልፍ በማጣት ሲገላበጡ የሚያድሩ በርካቶች ናቸው። የመብላት ፍላጎት እየቀነሰ የሚቸገሩ ሞልተዋል።ከዚያም የዘለለ እንደሆነ ራስን እስከ ማጥፋት የሚዘልቁ አሉ። ያኔ ግለሰቡ ከውስጣዊው ማዕበል ማምለጥ ባለመቻሉ ሰጠመ ማለት ይቻላል።

ወደ ሁለተኛው እንሂድ።

የተጣሉ ይታረቁ ተመልሰውም ይቀራረቡ ይሆናል። ለምን ቢሉ በዳይ ይቅርታ ሊጠይቅ ወይም ሦስተኛ ወገን ገብቶ ሊሸመግል ይችላልና። በመልክዓ ምድር የተለያዩ ደግሞ ከሁለት በአንዱ መንገድ ዳግም ዓይን ለዓይን ይተያዩ ይሆናል።ወይ የሄደው ተመልሶ ይመጣል ወይም የቀረው እዚያው ድረስ ይሄዳል። እናም ጊዜና አጋጣሚ የፈጠራቸው መለያየቶች እንዲሁ በጊዜ ሂደት ሊፈቱ ይችላሉ። ይህኛው እዉነት ሲታሰብ ዘለቄታዊው መለያየት የበለጠ ከባድ ነው

t.me/BooksandYou

ለማለት ያስደፍራል። እርሱም ለሰዎች ሁሉ የማይቀረው ሞት ነው።የ

የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚናገር ለሰው ልጆች ሁሉ መጀመሪያ ሞት ኋላም ፍርድ ይጠብቃቸዋል። የኋለኛው ፍርድ መኖሩን ያወቅነው አንብበን የተቀበልነውም አምነን ነው። ሞትን ግን ለዓመታት እናውቀዋለን። አብሮ አደጎቻችንን ሲቀጥፍ ደንግጠናል። ለጦርነት ወጥተው ያልተመለሱት ዘመዶቻችን መሞታቸውን ሰምተናል። ለዓይን የሚያሳሱትን ቆነጃጅት በኤድስ አማጭነት ከየመንደሩ ሲያግዝ አይተናል። በዕድሜ የገፉትንም ከዋሉበት አልጋ ላይ ሲነጥቅ አስተውለናል። ስለዚህ ሞት ለኛ አዲስ ድርሰት አይደለም። ይልቁንም ስናነበው የኖርነው አሮጌ መጽሐፍ ነው። እናም ወደጉዳዩ ስንመለስ ሁለቱም መላያየት ናቸው ብንልም የሚወዱትን ሰው በአካል መለየት እና በሞት መነጠቅ ለየቅል ናቸው። እስከምናውቀው ድረስ የሞተው ላይመለስ ሄዶአል።

አንድ ጊዜ በምንይልክ ሆስፒታል በኩል ወደሥራዬ ስሔድ ያጋጠመኝ ሞትና ዋይታ መቼውንም የሚዘነጋኝ አይደለም። አባት ይታመማሉ። ነርሷ ልጃቸው ደግሞ ወደምትሠራበት ወደዚሁ ቦታ እንድታመጣቸው ለታናሽ እህቷ ትነገራለች። እናም በትንሽ ታክሲ ጭነዋቸው እዚያ ይደርሳሉ። መኪናዋ ታችኛውን የድንገተኛ ሕክምና መስጫ

በር ዘልቃ እንደገባች ኋላ የተቀመጠችው ልጅ ወርዳ እህቷን ትጠራለች። የሕክምና ጋውኗን እንደለበሰች ብቅ ያለችው ነርስ ግን ገና አባቷን እንዳየች እሪታዋን አቀለጠችው። ሾፌሩም ይሁን ታናሽየዋ ያላዩትን ነገር እንደ ባለሙያ ዐይታ ነበርና። ሰውየው በተቀመጡበት ሞተዋል። ከዚያ በኋላ ሊደረግላቸው እሚችል ነገር የለም።

ሞተ ተብሎ የተመለሰ ሰው አላየንም። ጉዞው ዘላለማዊ ነው። በጊዜአዊው መለያየት ወቅት በዳዩ የመጸጸት ዕድል አለው። ይቅርታ ለመጠየቅ ጊዜ አያንሰውም። ተበዳዩን በአካል ባያገኘው በወረቀት ሊደርሰው ይችላል። በመልዕክተኛ ማረኝ ሊለው በስልክ ሊያናግረው ወይም በገጸ ተፋጠጥ (ፌስቡክ) ሊያዋራው ይችላል። ሰውየው ከሞተ ግን ክፉኛ ረፍዶአል። ሟቹ ያሸለበው በብዙ ሕመም ወይም መከራ ተሰቃይቶ ከሆነ ደግሞ “ ምን አድርጌለታለሁ?” የሚያሰኝ መልስ የለሽ ጥያቄ በቋሚው ላይ ደቅኖ ይኖራል። የተቀጠፈው በድንገተኛ አደጋ ከሆነም ሐዘኑን በቀሪው ላይ ያበረታዋል።

ምናልባትም “ይህ ዘላቂ መለያየት በመንፈሳዊው ምዘና የተሻለ ብያኔ አይኖረውምን?” የሚል ጥያቄ ሊከተል ይችላል። አዎን ሊኖረው ይችላል።ለዚያውም ለዘላለሙ ሕይወት ከተዘጋጁት ሁለት መኖሪያዎች ዉስጥ የሕይወት ሁሉ ፈጣሪ ባለበት በዚያ መገናኘት ከተቻለ ነው። ሌላኛው

መኖሪያ ለመገናኘት ምቹ አይደለም። ለሚወዱት ሰው የሚመኙትም አይሆንም። በዚያ እግዚአብሔር የለም። ስለዚህ የሚናፈቀው የዳግም መገናኛ ሥፍራ መንግሥተ ሰማይ መሆን አለበት። እርሱም ቢሆን ቀን ሊቀጠርለት አይችልምና የጊዜ ርዝመት ጥያቄ ያስነሳል።

የመሥራት ፍላጎቱና አቅሙ እያለ ልምዱና ተክኅኖውም ሳያንስ ሥራ ማጣት ባለንበት ዘመን የሚሊዮኖች ችግርና የነውጥ መንስዔ ነው። መቼም አቋራጭ ካልተገኘ በቀር ሰዎች በሥራ ዓለም ተሰማርተው ገንዘብ እሚያገኙበት መንገድ አንድ እርሱም ለዘመናት መማርና በመጨረሻ ላይ በቀሰሙት ዕውቀት መቀጠር ነው። እንግዲያው ለዓመታት ከትምህርት ጋር ታግሎ በመጨረሻ ሥራ ሳይሆን የኮሌጁን ዕዳ ታቅፎ ወጣ ገባ የሚል ገና ቁመናው ወጥቶ ያልታከተ ወጣት ውስጡ መረጋጋት ባይኖር ብዙ የሚገርም አይሆንም። አሁን ተማሪ አይደለምና ከቤተሰቦቹ የኪስ ገንዘብ ላያገኝ ይችላል። ዞር ዞር ብሎ ሥራ ለመፈለግም ይሁን እግረ መንገዱን ሻይ ቡና ለማለት ሳንቲም በኪሱ መገኘቱ ደግሞ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ይህኔ ወሳኝ ነው።

ፈቀቅ ሲልም በሰላም ለዓመታት ከሠሩበት መሥሪያ ቤት መፈናቀል አለ። ይባስ ብሎ አሁን ያለው ሉላዊ የኢኮኖሚ ውድቀት ቀጣሪዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ

ሠራተኞችን እንዲቀንሱ በር ከፍቷል። በዚህ አገባብ ለሥራ ያልደረሱ ለመብል ግን ያላነሱ ልጆች ያሉት የቤተሰብ ኃላፊ ሥራ ካጣ ያ ችግር ለርሱ ቁጥር አንድ እንደሚሆን አያጠራጥርም። ለምግብ ፍጆታ፤ ለኤሌክትሪክ፤ መብራት፤ ውኃ፤ ወዘተ... ገንዘብ ማስፈለጉ ያ ደግሞ በሥራ መገኘቱ ከታወቀና ሥራ ግን ከሌለ ታላቅ ማዕበል ተነሣ ማለት ነው። የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶች የሚያዩትና የሚሰሙት በመሆኑ ማዕበሉን ውጫዊ ለማለት ብንዳዳም ወደ ጉዳዩ ባለቤት ሲመጣ ግን ነገሩ ውስጣዊ ነው። በቂ ተቀማጭ ገንዘብ ከሌለ ወይም ወዳጅ ዘመድ ካልደረሰ በቀር እሚላስና እሚቀመስ አይኖርም። ቢኖርም እንኳ እንደበፊቱ በጥራትና በብዛት መመገብ አይቻልም። አስፈላጊውን የጤንነት እንክብካቤ አለማጓደልና ለሰውነት እሚበጅ እንቅስቃሴ ማድረግ ወደቅንጦት ይቀየራል። ወርኃዊው ክፍያ ጊዜውን ጠብቆ ካልተከፈለ መብራትና ውኃ ይቆረጣል። የስልክ አገልግሎት ትዝታ ይሆናል። ፈቀቅ ሲልም ቤት በሐራጅ ይሸጣል። ይህንኑ ተከትሎ በአንድ ጀምበር ያ ቤተሰብ የጎዳና ተዳዳሪ የመጠለያ ተጠዋሪ ይሆናል። የነዚህኑ ያህል ሌላም መጨመር ይቻላል።

2

ባሕርዩ

በድንገት

ዘመኑ ያመጣው ቴክኖሎጂ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ የተቻለውን ቢጥርም ማዕበል ግን ብዙ ጊዜ በድንገት ነው እሚከሰተው። ለነገሩ ማስጠንቀቂያውም ቢሆን የራሱ ውሽንብር አያጣም። የአየር ትንበያው ጥቂት ልም በረዶ ይወርዳል ብሎ ሲያበቃ አገር ምድሩ ነጭ ብርድ ልብስ የለበሰበትና ነዋሪዎች ለቀናት በቤታቸው የታጎሩበት ሁኔታ አለ። ማምሻውን ነፋስ የቀላቀለ ዝናብ ይመጣል ተብሎ ገና ከረፋዱ አገር ምድሩ በጎርፍ የተጥለቀለቀበት አጋጣሚም አለ። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ ሰዎችን ለቀጣዩ ክስተት ከመዘጋጀት ይልቅ እንዲዘናጉ ያደርጋቸዋል።

አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እንደተማርነው የእረኛው ታሪክ መሆኑ ነው። አማራጭ አጥቶ ሥራውን ቢቀበልም እንኳ ያ እረኛ ብቸኝነትን የማይወድ የመንደር ወግና ቧልት የለመደ ዝምታም የሚከብደው ቢጤ ነበር። እናም መንደርተኞቹ በጎቹን የሚያጠቃ ቀበሮ ወይም ሌላ አውሬ ከመጣ እንዲጮኽ መከሩት። እነርሱም ድምፁን ሲሰሙ ፈጥነው በመድረስ እንደሚረዱት ቃል ገቡለት። እናም ይሄ ሰው ለጥቂት ጊዜ እንደምንም ታግሦ ሥራውን ሲያከናውን ቆየ። ሆኖም ጥቂት ሰዓቶችን እንደገፋ ገና

ከወዲሁ የቀኑ ርዝመት አስፈራው። የሚያናግረው ሰው አለመኖሩ ደግሞ ይበልጡን አስከፋው። ስለዚህ ከሰዎች የሚያገናኘውን ብቸኛ አማራጭ አንድ ጊዜ ለመሞከር ወሰነ። እናም እሪታውን በማሰማት የድረሱልኝ ጥሪ አደረገ። መንደርተኞቹም እረኛው ጮኾ እንኳ ሳይጨርስ ተሯሩጠው አከባቢውን እንደ ንብ ከበቡት። ወዲያውኑም በተለያዩ አቅጣጫዎች ተበትነው አሰሳ ማድረግ ጀመሩ። ግን የቀበሮ ዘር ፈጽሞ አላዩም። ስለዚህ ለምን እንደጮኽ እየተገረሙ ጠየቁት። እርሱም ከልቡ እየሳቀ የጮኸው ብቸኝነት ስለተሰማው እንደሆነ ነገራቸው። መንደርተኞቹ ግን አልሳቁም። ሁሉም የየራሳቸው ሥራ እንዳላቸው በመግለጽ ስለስንፍናው ገሠፁት። አስከትለውም ከዚህ በኋላ እንዲህ ዓይነቱን የቀልድ ጥሪ እንዳያሰማ አስጠንቅቀውት ወደየመጡበት ተመለሱ። እርሱ ግን አላስችል ብሎት ብዙም ሳይቆይ አካባቢውን በጩኸት አተራመሰው። መንደርተኞቹም ከላያ ከታች ተሯሩጠው ደረሱለት። ጥሪው የሐሰት መሆኑን ለመረዳት ግን ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም።

በተደጋጋሚ ይህንኑ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ ግን በመጨረሻ የተፈራው ነገር ደረሰ። ወሳኙ ሰዓት መጣ። ቀበሮ በጎቹን ለመንጠቅ ብቅ አለ። እረኛውም ከሌላው ጊዜ በተለየ አኳኋን ባለ በሌለ ኃይሉ ጮኸ። መንደርተኞቹ ግን አልመጡም። እንደልማዱ ሲቀልድ ይሆናል ብለው በማሰብ

ባሉበት ቆዩ። ቀበሮውም የሚፈልገውን ይዞ ሄደ። እንግዲህ መንደርተኞቹን ምን እንዳዘናጋቸው ለማወቅ ብዙ ምርምር አይሻም። እረኛው በተደጋጋሚ እየጮኸ ስላደከማቸው እነርሱም በእረኛው ላይ አመኔታ ስላጡ ነው። እኛም አንዳንዴ ማስጠንቀቂያ ከመደጋገሙ የተነሳ መስማቱ ይሰለቸናል። እርምጃ መውሰድ አይታየንም። ማዕበሉ ግን በድንገት ይመጣና ይህ ነው እማይባል ጥፋትን ያደርሳል።

ከላይ እንዳነሳነው ዘመኑ ያመጣው ቴክኖሎጂ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ የተቻለውን ቢጥርም ነውጦች ግን ብዙ ጊዜ በድንገት ነው የሚከሰቱት። በቅርቡ ከአንድ የልብ ወዳጄ ዘንድ የተላከና እንዲህ የሚል ልብንም የሚያራራ ኢ ሜይል ደርሶኝ ነበር። “ የምወዳት ባለቤቴ በጠና ታማ ሆስፒታል ገብታለች፤ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት በጸሎት እንድትደግፉን እኔና ቤተሰቤ እንጠይቃችኋለን!”። ገና በቅጡ ሳልጸልይበት በጥቂት ቀናት ልዩነት ሌላ ሁለተኛ ኢ ሜይል ሰደደልኝ። ይህኛው እንደሚለው ከሆነ ደግሞ ባለቤቱ ጭራሹን ሕመሙ ጠንቶባታል። በዚያ ላይ መተንፈስ እንኳ እንደተሳናት ይናገራል። ከዚህም የተነሳ አየር በቱቦ እንደተቀጠለላትና ለመተንፈስም እየታገለች መሆኑን በመግለጥ አጭር መልዕክቱን ይደመድማል። ይህኔ ነገሩ ከአሳሳቢም በላይ መሆኑን ተገንዝቤ ጸለይኩ። ለባለቤቴም ትጸልይ ዘንድ ይህንኑ አካፈልኳት። በሳምንቱ መጨረሻ የተቀበልኩት

የመጨረሻ መልዕክት ግን ከዚህ በኋላ ይህን ማድረግ እንደማያስፈልገኝ አረዳኝ። እንዲህ ይላል። "በጸሎት ስለደገፋችሁንና አንዳንዶቻችሁም ደውላችሁ ስላበረታታችሁን እናመሰግናለን"። እናም ኢ ሜይሉ ከታች እህታችን ወደ ዘላለም ዕረፍት መግባቷን የሚነግር ዐረፍተ ነገር ነበረው። ከጥቂት ቀናት በኋላ ለማጽናናት አስቤ ወደ ወዳጇ ስልክ መታሁ። ብዙ ጊዜ ወደ አገር ቤት ስደውል የምቸገር ቢሆንም እንዳጋጣሚ ደግሞ በዚያን ቀን መስመሩን በቀላሉ አገኘሁት። በአጭር ንግግራችንም መሃል " ምነው ነገሩ ፈጠነ?" ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም ብዙ ሳያቅማማ "አዎን ልክ እንደጎርፍ ነው ያለፈው!" ብሎ መለሰልኝ።

በርግጥም ይህ ወዳጇ እንዳለው አንዳንድ ጊዜ የመከራ አመጣጥ እንደ ጎርፍ ነው። ባልታሰበ ጊዜና ሁኔታ በድንገት ብቅ ይልና በታላቅ ጉልበት የፈለገውን ጠራርጎ በዚያው ፍጥነት አልፎ ይሄዳል። የማስጠንቀቂያ ምልክት ሳይሰጥ ይመጣና በተጠቂው ላይ የማይጠፋ ጠባሳን ጥሎ ያልፋል።

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት የገሊላ ባሕር ጉዞ ገጠመኝም ለዚህ ማስረጃ አያጣም። ማዕበሉ የተነሳው በጉዞአቸው መካከል እንጂ ገና ጀልባቸውን እንዳነቃነቁ አልነበረም። መሃል ላይ ግን ባላሰቡት ሰዓት ድንገተኛው ማዕበል ተነሣ። ወደ ወታደራዊ ማሠልጠኛ የገቡ ምልምል ወታደሮችን

የሚቀበሉት አዛዦች ‘‘በጉዞ ደክማችኋል እረፉ’’ ነው እሚሏቸው። የዚያኑ ቀን ወደተኩስ ወረዳ አይወስዷቸውም። ሥልጠናቸውን ጨረሰው እና ጊዜው ደርሶ በድንገት ወደዚያ ሲወሰዱ ግን ብዙዎችን ጠርጎ የሚሄደው ሞት በጥይት አማካኝነት ሲዘራ ይመለከታሉ። ድንገተኛ ውጊያ ምን እንደሆነም እዚያው ይማራሉ።

ከአድራሚጢስ ወደ እስያ አውራጃዎች በመርከብ ይጓዙ በነበሩት በጳውሎስና ሌሎች እስረኞች ላይ የወረደው ማዕበል እንደዚያ ዓይነት ነው። በሐዋርያት ሥራ ሃያ ሰባተኛ ምዕራፍ የተተረከው የመርከብ ላይ ጉዞ እንደሚነግረን ከሆነ ቢያንስ የጉዞው ጅማሬ ሰላማዊ ነበር። የመርከቡ ባለቤትም ሆነ አዛዡ ወይም የእሥረኞቹ ኃላፊ የሆነው የመቶ አለቃ ለሰሰ ብሎ በነፈሰው የደቡብ ነፋስ እጅጉን ተዘናግተው ነበር። የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ለመስማት አለመውደዳቸው የጥፋቱ ጎርፍ መነሻ ነበር ለማለት እንደፍራለን። ጳውሎስ ከኪሱ አውጥቶ ስላልተናገረ ዞሮ ዞሮ ማስጠንቀቂያው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበርም ልብ ማለት ያሻል። ባለመርከቡ ባለሃብት አዛዦቹ ደግሞ ባለሥልጣኖች እንደመሆናቸው ለመልዕክቱም ይሁን ለመንፈሳዊ ጉዳይ የተከፈተ ጆሮ አልነበራቸውም። በዚያ ላይ አሳቡን ያልተቀበሉት ተናጋሪው ራሱ መብቱ የተገፈፈ እስረኛ ስለነበረ ወይም እንስማው ቢሉ እንኳ አሳቡ በድምፅ ብልጫ

ስለተሸነፈ ሊሆንም ይችላል። እናም ተራኪው ሉቃስ በሥዕላዊ ቃላቱ እንደሚለን ብዙም ሳይዘገዩ አውራቂስ የተሰኘ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ወርዶባቸዋል። ይህ ደግሞ መጀመሪያ ከቀመሱትና ወደ ሲዶናና ሞራ ካደረጉት ሰላማዊ ጉዞ ጋር ሲተያይ ድንገተኛ ውርጅብኝ ነው። አመጣጡ ሳይታሰብ ቢሆንም እንኳ በሚገባ ሳያሳስብ በቀላሉ አልለቀቃቸውም።

በመጀመሪያ መርከቡን ከመርከበኞቹ ቁጥጥር አውጥቶ ወደፈለገበት ነድቶአቸዋል። የተቄዳን ደሴት ለመጠለልም ይሁን ያለሸራ ለመቅዘፍ ያደረጉትን ጥረት ጨምሮ በርካታ ንብረቶችን ወደ ባሕር ቢወረውሩም እንኳ ኃይለኛው ንፋስ ቢያንስ ለአስራ አራት ቀናት አንገላቷቸዋል። አስቀድመው መርከቧ በሚንጣት ወጀብ እንዳትሰባበር በመስቀለኛ ዘዬ ተብትበው በማሰር ቀጥለውም ከአሸዋ ቁልል ጋር እንዳትላተም ሸራ በማውረድ ያደረጉት ጥረት ሁሉ ፍሬ አልባ ነበር። ፀሓይና ከዋክብትን ለሳምንታት ባላዩበት በዚህ መከራ ሰሞን የሁሉም ዐይን በችግሩ ላይ ስላረፈ ምግብ እንኳ መብላት አልቻሉም። መርከበኞቹም ተስፋ ከመቁረጣቸው የተነሣ ተሳፋሪዎቹን ወደኋላ ትተው እና መልሕቅ የሚጥሉ መስለው ለማምለጥ ሞክረው ነበር። በመጨረሻም በቅርብ ወዳዩት መሬት ለመቅዘፍ ያደረጉት ሙከራ መርከቡን ጥልቀት ወደሌለው ውኃ ገፍትሮ ከመሬት

ጋር በማጣበቅ ተደመደመ። ያን ጊዜ ደግሞ ነፋሱ በግላጭ ስላገኛት መርከቢቱን በመሰባበር ከጥቅም ውጭ አደረገ። ገሚሶቹ ዋኝተው የማይችሉት ደግሞ በጣውላና በመርከቡ ስባሪዎች ላይ ተንሳፍፈው የተረፉትም እግዚአብሔር በባሪያው ስለተናገረ ብቻ ነበር። እናም አውራቂስ እንደጎርፍ በድንገት ብቅ ብሎ የፈለገውን ጠራርጎ በዚያው ፍጥነት አልፎ ሄዷል። የማስጠንቀቂያ ምልክት መስጠት ሳያስፈልገው ልከኛውን ነፋስ ተከትሎ መጣና የማይጠፋ ጠባሳን ጥሎ አለፈ።

ተደርቦና ተደራርቦ

ማዕበል የተለመደ የውኃ ላይ ነውጥ ቢሆንም አደገኛ የሚሆነው በተደራራቢነቱ ነው። እያንዳንድዋ የውሃ ጉማጅ ትጋፋለች። በአንዱ ተንገዳግዶ መቆም ሲቻል አንዱ ባንዱ ላይ እየተነባበረ ሲመጣ ግን ከአቅም በላይ ይሆናል። እንዲሁም ችግር የሕይወት ጥላ ቢሆንም የበለጠ አስቸጋሪ የሚሆነው ተደርቦና ተደራርቦ ሲመጣ ነው። ሁለቱን አስማሚ ፍች ከሠጠናቸው በኋላ ጥቂት ማብራሪያ ማከል ይኖርብናል። ተደርቦ ስንል ከዚያ ቀደም ብሎ የተከሰተው ችግር ከመፈታቱ በፊት ሌላው የመድረሱን እውነታ ተከትለን ነው። ተደራርቦ ካልን ደግሞ ከመደረብም አልፎ በላይ በላዩ ተቆልሏል ማለት ነው። በአገራችን መደረብ ወይም መደራረብን ጥሩ አድርገው የሚገልጡ አባባሎች አሉን።

የመጀመሪያው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሚለው ነው። በቡሃ ላይ ቆረቆር ሊባልም ይችላል። በድንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ ወይም ከአባ ቁፍር እሸት ተበልቶለት እሚሉትም ቢሆኑ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

ተደርቦን ዘለን ተደራርቦ የምንለው ደግሞ ችግር በሰልፍ ወደ አንድ ሚላማ መገሥገሡን እያሰብን ነው። አንዲት ወገኛ ሴት ሊጠይቃቸው የመጣ ዘመዳቸውን "ቂጣ የለም እንጂ ወተትማ ቢኖር ያንን እያማግህ መቅሰስ ትበላ ነበር " ብለውታል ይባላል። ያወሩለት የተደራረበ ችግር ነው። በመጀመሪያ ቂጣ የለም። ወይ ዱቄቱ ከማድጋ አልያም ማገዶው ከጓሮ ጠፍቶእል። ወተትም እንዲሁ። ላሞች የሉም ቢኖሩም ነጥፈዋል ብሎ ማሰብ ይቻላል። በጥቅሉ ቤቱ ባዶ ነው።

ይህንን በተሻለ ምሳሌ እንደግፈው። ሰውየው ያልተጠባበቀው አደገኛ የመኪና አደጋ ደረሰበት። በአስቸኳይ ወደድንገተኛ ሕክምና መወሰድ ቢኖርበትም መንገዱ በትራፊክ መጨናነቅ በመዘጋቱ የድንገተኛ አደጋ ሠራተኞች ፈጥነው ሊደርሱለት አልቻሉም። እንደምንም አጥሩን ሰብረው በማለፍ አፋፍሰው አንስተውት ወደ ሆስፒታል ሲገሠግሡ ደግሞ አንቡላንሱ ተበላሸና ቆመ። እንደገና በዚያ የሚያልፉትን መኪኖች እያስቆሙ ርዳታ በመጠየቅ ፈቃደኛ አገኙና እንደምንም ወደ ድንገተኛ ክፍሉ አደረሱት። በዚያ

የመረመረው ዶክተር ደግሞ ከምንም በፊት ብዙ ደም ስለፈሰሰው የሚያስፈልገው እርሱ ነው አለ። አገሩ ቢታሰስ ከሰውየው ደም ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሊጋሽ ጠፋ። በብዙ ጭንቅ የተገኘ አንድ በጎ አድራጊ ደግሞ የኤድስ ተጠቂ ሆኖ ተገኘ። ተደራራቢው ማዕበል ይህን ይመስላል። ዒላማውም ይህንን ሰው በጥድፊያ ወደ መቃብር ማጋዝ ይመስላል።

በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የሰፈረው የኢዮብ እውነተኛ ታሪክ ጥሩ የመዝጊያ ምሳሌ ይወጣዋል። በአንድ ቀን ጀምበር በተከታታይና እግር በእግር የደረሱት አራት መረጃዎች እንደሚከተሉት ነበሩ።

በመጀመሪያ የሳባ ሰዎች በድንገት አደጋ ጥለው በሰይፍ ስለት ጠባቂዎቹን በመግደል በእርሻ ላይ የነበሩትን በሬዎች እንዲሁም በአቅራቢያው የተሰማሩትን አህዮች ዘረፉ።

ቀጥሎ ከሰማይ የወደቀ እሳት ተብሎ የተጠቀሰው መብረቅ ወርዶ በጎቹን ፈጀ፤ ጠባቂዎቹንም ገደለ። በሦስተኛ ደረጃ ከለዳውያን በበኩላቸው በሦስት በመከፈል አደጋ ጣሉና ልክ እንደሳባ ሰዎች በሰይፍ ስለት ጠባቂዎቹን ገድለው ግመሎቹን ዘረፉ።

በመጨረሻም ወንዶችና ሴት ልጆቹ በሙሉ በታላቅ ወንድማቸው ቤት እየተጋበዙ በነበሩበት ቅፅበት ዐውሎ ነፋስ የነበሩበትን ቤት መታውና ሁሉም አለቁ።

<u>የማይቀር ዕጣ</u>

በሰሜን፤ ደቡብ፤ ምሥራቅና ምዕራብ ቢኬድም እንኳ ከማዕበል ነፃ የሆነ ክልል የለም። ብዙዎች ግን ይህንን ባለመገንዘብ ከነውጡ ለመሸሽ ብለው አገር ሥራና ጓደኛ ይቀይራሉ። ግን አያመልጡትም። ሰውየው ነጋ ጠባ የሚበላው መላጣ ሽሮ ሰለቸው አሉ። እናም ከዕለታት በአንዱ ቀን ሥጋ መብላት ያምረውና ከርሱ የተሻለ ገቢ ወዳለው ወዳጁ ቤት የምሳን ሰዓት ጠብቆ ጎራ ይላል። እነርሱም በድንገተኛ አመጣጡ ተገርመው ይቀበሉታል። ትንሽ ካወጉ በኋላም መቼም የቅርብ ሰው ነውና አብሮአቸው ማዕድ እንዲቆርስ ጋበዙት። እርሱም የሄደበት ዓላማ ይኸው በመሆኑ ምንም ሳያቅማማ ይስማማል። ታዲያ ምግቡ ሲቀርብ ሰውየው ሐዘኑን መሸሸግ አልቻለም። ወዲያውም እንዲህ አለ።'' ወይ ሽሮ በየት በኩል ቀደምከኝ?''። አዎን ሽሮው ልክ እንደማዕበሉ በአቋራጭ ቀድሞ ጠብቆታል።

መንፈሳዊና ለትርፍ ያልተቋቋሙ የበጎ አድራጎትድርጅቶች እንዲሁም የተለያዩ አገልግሎቶች ከቀረጥ ነፃ የሚሆኑበት አሠራር በምዕራቡ ዓለም የተለመደ ነው። ይሄ ለብዙዎች ማበረታቻ ሆኗል። ለምን ቢሉ የሚያገኙትን ገንዘብ ያለምንም ገደብ ለወንጌልና የበጎ አድራጎት አገልግሎት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ለጋሾችም ለነዚህ ድርጅቶች የሚሰጡት የገንዘብም ሆነ የንብረት ስጦታ ከቀረጥ

ነፃ ስለሚሆንላቸው የበለጠ ለመስጠት ይበረታታሉ። ነገር ግን እነዚህን መንፈሳዊና ለትርፍ ያልተቋቋሙ የበጎ አድራጎትድርጅቶች እንዲሁም የተለያዩ አገልግሎቶችን ከማዕበል ነፃ የሚያደርግ አሠራር የለም። ስለዚህ የአዳም ዘር ሁሉ ራሱን ለማዕበል ማዘጋጀት ይኖርበታል።

የሚገርመው ደግሞ ልክ ምድራዊው ነውጥ ማለትም የመሬት መንቀጥቀጥ፤ ዐውሎ ነፋስና የባሕር ማዕበል አማኝና ከሃዲን ሳይለይ የሰውን ዘር በሙሉ እንደሚመታ ሁሉ ውስጣዊው ነውጥም እንደዚያው ነው። በማያምኑት ላይ ያየናቸውን ብሎም የተሳቀቅንባቸውን በሽታዎች በወገኖችም ላይ ልናያቸው እንችላለን። በአገር ላይ የሚመጣው ማንኛውም ችግር ዜጎችን ሁሉ ይመለከታል። ኢኮኖሚውን ተከትሎ የሚከሰተው የኑሮ ውድነት ወይም የዋጋ ግሽበት ለአማኞችም ይተርፋል። ቤተ ክርስቲያን ይህን ለመቋቋም የከፈተችው የሕብረት ሱቅ የለም። እንሻገራለን ቢባል እንኳ ብዙውን ጊዜ መሻገር የሚሆነው መጀመሪያው ችግሩ ከተቀመሰ በኋላ ነው።

እናም ዛሬ በሕይወት ያለን ሁላችን ከሁለት አንዱ ውስጥ እንመደባለን። የማዕበል መንገደኞች ወይም ሰላማዊ ቀዛፊዎች ነን። ወይ ማዕበሉ ውስጥ ገብተናል አልያም ወደ ማዕበሉ እየተጠጋን ነው። በወጀቡ ውስጥ አረፋ የሚደፍቁትን እያየ ለመቆዘም ወይም ለመሳቅ የተመደበ

የሰው ዘር የለም። እንደምንኖርበት መልክዓ ምድርና እንደ እምነታችንም መጠን የማዕበሉ ኃይል ሊለያይ ቢችልም እውነቱ ግን እንደጥላ የትም ይከተለናል። እናም ሐቁ ይህ ነው። ወይ ማዕበሉ ውስጥ ገብተናል አልያም ወደማዕበሉ እየተጠጋን ነው። መልካም ቀዘፋ!

3

እውነታው

ጌታ ቢኖርም ወጀብ ኣይቀርም!

ሐዋርያት ተፈትነው ያለፉባቸው ቢያንስ ሁለት የሚያህሉ ማዕበሎች በአዲስ ኪዳን ላይ ተዘግበዋል። በመጀመሪያው ላይ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበረ። ውኃው መከራዋን ባሳያት በዚያችው አንድ ጀልባ ላይ አብሮአቸው መቅዘፉን የወንጌል ጸሐፊዎች ከነገሩን ሌላ እንደቀሰቀሱትም ስለምናውቅ በዚያ ወቅት መምህሩ በጀልባዋ ስለመሳፈሩ ጥርጥር የለንም። ከዚህ የተነሣም ነው የመጀመሪያው ነውጥ ላይ ደቀመዛሙርቱ ብቻቸውን አልነበሩም ለማለት የደፈርነው። ወደ ባሕር የቀዘፉት ኢየሱስን በጀልባቸው ላይ አሳፍረው ነው። እነርሱን ስለ እምነት ያስተምር ዘንድ እርሱ በምትናወጠው ጀልባ ውስጥ መኖሩ አብሮም መንገላታቱ እኔን በብርቱ አስገርሞኛል።

ምናልባት ኢየሱስ በጀልባዋ ላይ በነበረ ጊዜ የተነሣው ማዕበል በርሱ መገኘት ፈጥኖ ተቀርፏል ብለን እናስብ ይሆናል። እውነትነት አለው። ቢያንስ ደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሳይመካከሩ አይቀሩም። ‘‘የምንችለውን ያህል እንታገል፤ ካልሆነ ግን ጌታን እናነቃዋለን’’። በመሠረቱ ያደጉበት የገሊላ ባሕር ከማዕበል ነፃ ሆኖ አያውቅም።

በተራሮች የተከበበና በዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ያለ እንደመሆኑ ሁሌም ሞቃት ነው። ከሜዲተራኒያን ባሕር የሚመጣው ቀዝቃዛ ንፋስ ከዚህኛው ጋር ሲጋጭ ታዲያ ዐውሎ ነፋስ ይፈጥራል። ዐውሎ ነፋሱ በተራው ውኃውና ያናውጥና ማዕበል ያስነሣል። እናም ደቀ መዛሙርቱ ለማዕበል አዲስ አይደሉም። ግን ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው ቀሰቀሱት። እርሱም አስቀድሞ ማዕበልና ወጀቡን ገሠፀ። ነፋሱና ውኃው ካረፈ በኋላ ደግሞ ወደእነርሱ ተመልሶ እምነት እንደሚያስፈልጋቸው ብቻ ሳይሆን ያላቸውንም እምነት በሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባቸው አስተማረ።

በሁለተኛው ጊዜም ቢሆን ደቀ መዛሙርቱ ወደገሊላ ባሕር ያመሩት በኢየሱስ ትእዛዝ ነው። ምክንያቱም ቀድመውት እንዲሄዱ የግድ ብሏቸዋል። ወይም በቀላል አነጋገር አዟቸዋል። እርሱን ባይዙም ፈቃዱን ይዘው ነው ጉዞ የጀመሩት። በራሳቸው ፈቃድና ንድፍ የተደረገ ቀዘፋ ከቶም አይደለም። ያም ሆኖ በማንኛውም ጊዜ እንደሚሆነው ኃይለኛው ማዕበል መጣ።

ይህ ወደ ሕይወት ሲተረጎም ማንኛውም የሚያንገላታን ችግር ሊሆን ይችላል። ታዲያ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ችግሩ ለምን ተከሰተ ከማለት ይልቅ እንዴት መጣ ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው። ማዕበሉ የተነሣው በራሴ ስሕተት ነው ወይስ መልካም በማድረጌ ብሎ ማሰብ አስተዋይነት

ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በሁለት ምክንያት ጥፊ ሊቀምስ ይችላል። ወንጌልን በመመስከር ወይም ሰዎችን በመዳፈር። በሁለት ምክንያት ማዕበል ሊያገኘው ይችላል። በመታዘዝ ወይም አንገትን በመጠምዘዝ። እናም ስለ ትዕዛዙ እንዲህ ብሎ ራስን መፈተሽ ይቻላል። እርሱ ተናግሮኝ ነው ወይስ ራሴን ተናግሬ? ተጠርቼ ነው ወይስ ራሴን ጠርቼ? ተቀብቼ ነው ወይስ ራሴን ተቀባብቼ? ተሹሜ ነው ወይስ ራሴን ሾሜ?

ጴጥሮስና ዮናስ ከላይ ላነሣናቸው ጥያቄዎች ጥሩ ማሳያ ሊሆኑን ይችላሉ። ጴጥሮስ ወደባሕር የወረደው ተልኮና ታዝዞ እንዲያውም የአማርኛው ትርጉም በትክክል አስቀምጦት ከሆነ የግድ ተብሎ ነው። ዮናስ ግን መርከብ የተሳፈረው አልታዘዝም ወደነነዌም አልሄድም ብሎ በእንቢተኝነት ነበር። ጴጥሮስ ሊሰጥም የጀመረው እምነትን ሊማር ተልኮ ነው። ዮናስ በዓሣ ሆድና በውኃው ጥልቅ እጥፍ መስጠም የገጠመው ክሕደትን ሲለማመድ ነበር። ጴጥሮስ ወደጌታው አቤት ያለው ገና መስጠም ከመጀመሩ ነው። ዮናስ ግን አቤቱ ለማለት እጅግ ዘግይቷል። በመጨረሻም ጴጥሮስ በውኃ ላይ ተራምዶ ለደቀ መዛሙርቱ መልካም አርአያና ታሪኩን ለሚያነቡም በረከት ሆኗል። ዮናስ ግን አብረውት ለሚጓዙት እንግልትና መከራን አምጥቷል። በራሱም ላይ ፍርድን ተናግሯል። የአገልግሎት ፍጻሜአቸውም ከዚሁ አተያይ ጋር በእጅጉ የሚዛመድ ነው።

የነነዌ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተውና በታላቅ ስብራት ንስሓ ገብተው ተመለሱ። ዮናስ በዚህ ደስ አልተሰኘም። በአንፃሩ "እንዴት ምሕረት ያገኛሉ" ሲል አጉረምርሟል። ጴጥሮስ በበኩሉ በበዓለ አምሳ ቀን በሺሕ የሚቆጠሩ ኃጢአተኞች ሲድኑ አይቶ ሓሜት አድርጓል። "እናንተ የሰቀላችሁት " ብሎ የጠቀሳቸው እነዚህ ኃጢአተኞች ምሕረት በማግኘታቸው አላንጎራጎረም።

ጉዞውን በተመለከተ ወደተሰጠው መመሪያ ስንመለስ "ቀድማችሁ ሒዱ" የሚለው የኢየሱስ ጥሪና ተስፋ ሲተርጎም " በሰላም ትደርሳላችሁ" እንጂ " ያለ ችግር ትቀዝፋላችሁ" የሚል አልነበረም። ያለ ችግር መቅዘፍና በሰላም መድረስ ደግሞ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። በርግጥ ጉዞን በተመለከተ የሁላችን ምርጫ ችግር አልባ ቀዘፋና ሰላማዊ አደራረስ ሊሆን ይችላል። ግን በመንፈሳዊው ዓለም ይህ ዓይነቱ ጉዞ ያልተለመደና ብዙም እማይታይ ነው። በዚያ ላይ ፈጥኖ ከመረሳቱም ባሻገር ምንም የሕይወት ልምድ አይገበይበትም። አልጋ በአልጋ በሆነ ኑሮ አገልግሎታቸውን የፈጸሙ ሰዎች ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የለም። ተጻራሪው ደግሞ ውጣ ውረድ የሞላበት ጉዞና የታሰበበት አለመድረስ ይሆናል። መጀመሪያ የተከፈለው ዋጋ ሳያንስ እንደገና ከግብ አለመድረስ ከታከለበት ይህ ጉዞ የመጨረሻው

ተስፋ አስቆራጭ ይሆናል። ምናልባትም ከጅማሬው በቂ ምሪት ያልነበረው ሊሆን ይችላል።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው የጉዞ መመሪያ ግን ከሁለቱ የሚለይ ነው። በሰላም እንደሚደርሱ በሚገባቸውና አብረውት በመኖር በተለማመዱት መንገድ ነግሮአቸዋል። ‘‘መንገዱ ሰላም ነው፤ እንቅፋትም አያገኛችሁም ’’ ግን አላለም። በአንፃሩ‘‘ወጀብ ሊኖር ይችላል፤ ግን እርሱን በእምነት ፀጥ ማሰኘት ትችላላችሁ’’ ነው ያለው። ቃል በቃል ይህንን ተናግሮአል ግን አላልኩም። ትምህርቱ ራሱ ጮክ ብሎ ይህንን ዐወጀ እንጂ። ይህ ደግሞ ኢየሱስ የወጠነው ትምህርታዊ ንድፈ አሳብ ሳይሆን ከዚህ በፊት እዚሁ ባሕር ላይ በተግባር የገለጠና ያሳያቸው እውነት ነበር። ዳሩ ግን ደቀ መዛሙርቱ ያንን ሥልጣን አልተጠቀሙበትም። እንዲያውም የሆነው የተገላቢጦሽ ይመስላል። በመጀመሪያው ማዕበል ‘‘ ጌታ እያለ እንዴት ይህ ይሆናል’’ ብለው ያሰቡ ቢኖሩ በሌላው ቀን ግን አልነበረምና ጭራሽ ተስፋ ሳይቆርጡ አልቀሩም። ማዕበሉ ደግሞ ሥራው ነውና አቅሙ ሳይደክም፤ ጉልበቱ ሳይቀንስ ግርማውም ሳይኮስስ ጌታ በሌለበት ሰተት ብሎ መጣ።

ይህ ምንን ያሳያል?

ማዕበሉ መነሣቱ ጌታ እጅግ እንደቀረበን ወይም ድምፁ እንደራቀን አመላካች አይደለም። ያለበለዚያማ ‘‘

እስከዓለም መጨረሻ ከእናንተ ጋር ነኝ'' ከሚለው ተስፋ ጋር እንዴት ይታረቃል? ጌታ አብሮን እያለም ይሁን ርቆ ማዕበሉ ሊመጣ ይችላል። ወይም በሌላ አነጋገር የወጀቡ መነሣት ከርሱ መኖርና አለመኖር ጋር ቀጥተኛ ዝምድና የለውም። ስለሆነም የማዕበሉ መነሣት '' በርግጥ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነውን?'' ወደሚል ጥርጥር ሊመራን አይገባም። ቸኩለንም ''ጌታ ከኛ ጋር ቢሆን ኖሮ ይህ ባልተፈጠረም ነበር'' ወደሚል መደምደሚያ መድረስ አይገባንም። ለምን ቢባል በማዕበል ተፈትነው እንዳለፉ ይቆጠሩ የነበሩት ዓሣ አጥማጆች በዚያው በሚያውቁትና ባደጉበት ማዕበል ተጨንቀው ሲጮኹ በማይገመት ሰዓት ሊያድናቸው በራሱ በውኃው ላይ እየተራመደ መጥቶአልና። ችግራችን ባሉት የተናወጠ ውኃ ላይ ዘና ብሎ ተረማመደበት። ለዚያውም የጮኹት ወደርሱ ስለመሆኑ የተጻፈ አላነበብንም። ማንም እንደሚጮኽ ግን ከጭንቅ ብዛት እንደዚያው አደረጉ። ጌታ መጣ የተባለበት የሌሊቱ አራተኛው ክፍለ ጊዜ ማለት ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ነው። በዘመኑ ቅኝ ገዢዎች የነበሩት ሮማውያን ምሽቱን በአራት ከፋፍለውት ነበርና ይህ ጊዜ ከምሽቱ ዘጠኝ እስከጧቱ አስራ ሁለት ያለው ይሆናል። ፍጥረት ያንቀላፋበት በጥልቅ እንቅልፍ የወደቀበት ጊዜም ነው። አዎን ለፍጥረት የመሸ ቢመስልም እርሱ ግን ይመጣል። በጠበቅነው ሰዓት ላይሆን ቢችልም በራሱ ጊዜ ግን ከተፍ ይላል።ደቀ

መዛሙርቱ በመጀመሪያው ክስተት ላይ ንፋስና ማዕበሉ የሚታዘዙለት ይህ ሰው ማን እንደሆነ እርስ በእርስ ለመጠያየቅ ተገድደው ነበር። አሁን ግን በዓይናቸው ፊት የተገለጠውን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል አጢነው በርግጥም ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መሠከሩ። ወድቀውም ሰገዱለት። የሚገባውን አምልኮ አቀረቡለት።

ንስር ልጆቿን በረራ እንደምታስተምር እርሱም ደቀመዛሙርቱን ስለእምነት ሊያስተምራቸው ይህንን አደረገ። ንስር ለአቅመ በረራ የደረሱ ልጆቿን ተሸክማ ወደገላጣው አካባቢ እንደምትወስድ በመጀመሪያው ማዕበል አብሯቸው ሆነ። በነበሩበት ጀልባ አብሮ ተሳፈረ። ኋላ ደግሞ ከከፍታ ሆና ከአየር ላይ እየለቀቀች ራሳቸውን ችለው ለመብረር እንዲጣጣሩ እንደምታደርግ እርሱም በተራራው ላይ ሆኖ እነርሱን በባሕር ላይ ማዕበሉን ተቋቁመው ይቀዝፉ ዘንድ ለብቻቸው ተዋቸው። ደግሞ ሊከሰከሱ ሲሉ ከሥር ገብታ እንደምትደግፋቸው ከሞትም እንደምታድናቸው እርሱም ሊሰጥሙ ሲሉ ደርሶ ታደጋቸው።

ያለንባት ዓለም የሚያሰጥም ነገር ሞልቶአታል። ለዐይን አምሮት እሚዳርገው የሥጋንም ምኞት እሚቀሰቅሰው አቅርቦቷ ልክ የለውም።ያንን ፈተና በማዕበል ውድቀትን ይልቁንም ከጽድቅ የተንሸራተተውን ልብ በመስጠም ልንመስለው እንችላለን። እናም ላለመስጠም ሌትና ቀን

በመታገል ላይ መሆናችን ሊሰመርበት ይገባል። በትግሉ ላይ ማራናታ የሚለው ጩኸታችን ሲታከል ኢየሱስ ይመጣል። በርግጥም ይመጣል። ወይ ከጊዜአዊው ችግር ሊታደገን አልያም ወደርሱ ሊሰበስበን ይገለጣል። ጊዜውን ባናውቅም የሚመጣው ግን ሊሰበስበን ከሆነ በቅፅበት ዐይን በመነጠቅ ከዚህ መከራ እንወጣለን። ደቀ መዛሙርቱ አንዴ ወጀቡን አልፈው ከተሻገሩ በኋላ በዚያ ያዩት ፈውስን ነበር። የጌንሳሬጥ ሰዎች በአስቸኳይ ተጠራርተው የፈውስ ፕሮግራም እንዲካሄድ ሁኔታዎችን አመቻቹ። እኛም ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስንሔድ ተመሳሳይ ነገር ይጠብቀናል። በዚያ ሞትና ሕመም የለም። እንኳን ሞትና ሕመም ልቅሶ እንኳን አይፈቀድም። እንባዎች ሁሉ ከፊታችን ይታበሳሉ። ሃሌሉያ!

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የኖሩትና ስደትን የጠገቡት የቀደሙ ክርስቲያኖች የሚለዋወጡት ሰላምታ

“ኢየሱስ ተነሥቷል!”

“በርግጥም ተነሥቷል!” የሚል ነበር።

እኛ ደግሞ በዚህ ዘመን

“ኢየሱስ ይመጣል!”

“በርግጥም ይመጣል!” እንድንባባል ጽኑ ምኞቴ ነው።

ለማጠቃለል ከላይ እንዳነሣነው የመጀመሪያው ማዕበል ጀልባይቱን ሲመታ ኢየሱስ በዚያ ነበረ። በጌታ መሆንን የችግር ሁሉ መፍትኼ አድርጎ የመውሰዱ አደገኛ አዝማሚያ መገታት ይኖርበታል። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የጠፉትን ለማዳን እንጂ የሰው ልጆችን ማለቂያ የለሽ ችግር ሊያስወግድ አይደለም። በምድር ከምናያቸው እልቆ መሳፍርት የሌላቸው ችግሮች ብዙዎቹ በራሱ በሰው ልጅ የተፈጠሩና ተመልሰውም በሰው ልጆች ሊፈቱ እሚችሉ ናቸው። ከምንም ይልቅ እርሱ የመጣው ሰዎች ሊፈቱት ያልቻሉትን እንቆቅልሽ ሊፈታ ነው። አንድ ሰው ቢደኸይ በሌላው ድጋፍ ሊበለጥግ ይችላል። ቢታመም ጣራ በነካው የሕክምና ቴክኖሎጂ ይታገዛል። መኖሪያ ቢያጣ ሌላ አገር ሄዶ ጥገኝነት ይጠይቃል። ከኃጢአት እሥራት ግን ያለአዳኝ ሊያመልጥ አይችልም። ኢየሱስ የመጣው ያንን ሊያደርግ ነው። ከዚህ የተነሣም የምንሰብከው ወንጌል ‘‘ ብታምን ከዘላለም ጥፋት ትድናለህ’’ ነው መሆን ያለበት። ሌላው ያንን ተከትሎ እሚመጣ ወይም በአንድ ቃል ተሳቢ ነው።

የዘመኑ አማኞች ስደትን አይተው ሐሤት ከማድረግ ይልቅ እንዲደነብሩ ከሚያደርጓቸው ዓይነተኛ ምክንያቶች አንዱ ወንጌልን የሰሙበትና የተረዱበት አኳኋን ነው ። በኢየሱስ ማመን መከራን እንደሚያስከትል፤ ከወዳጅ ዘመድ እንደሚያጋጭ፤ መሳቂያና መሳለቂያ እንደሚያደርግ አልፎ

ተርፎም ለእሥራት፤ ረሃብና ሲጠናም ለሞት እንደሚዳርግ አልተነገራቸውም። የሰሙት ኢየሱስ ከበሽታ እንደሚፈውስ በሃብት እንደሚያበለጥግ ከሱስና ሌሎች እሥራቶች እንደሚፈታ እና ሌሎችም ተአምራትን እንደሚያደርግ ነው። ኢየሱስን ከአዳኝነቱ ይልቅ በችግር አስወጋጅነቱ ነው ያወቁት። ፈቀቅ ሲልም ደክመውና ሠርተው በላባቸው ፍሬ ከመባረክ ይልቅ በቦዘኔነት ዕድሜያቸውን እንዲጨርሱ ነው በስመ ስብከት የተመከሩት። እንዴት ቢባል ለምሳሌ በተመኙት የሰው ንብረት እንበል ቆንጆ መኪና ላይ እጃቸውን ጭነው ለራሳቸው በመመኘት ትንቢት አይሉት መቋመጥ ያልለየለት ንግግር እንዲያሰሙ የሚያደርግ ዓይነት ሌላ ወንጌል ነው የተሰበከላቸው። ስለዚህ ጌታን ከተቀበሉበት ዕለት ጀምሮ በሽታ፤ ድኅነትና ጭንቅ አጠገባቸው እንደማይደርስ ነው የሚያውቁት። አንድ አፍሪካዊ ሐዋርያ ‘‘ብታምን ችግሮችህ ሁለ ይወገዱልሃል ተብዬ ጌታን ተቀበልኩ፤ የሕይወቴ ታላቅ ችግር ብቅ ያለው ግን በዚያው ቀን ነው’’ ሲል ሰምቼዋለሁ። በርግጥም ስደት ቀኑን ጠብቆ ከተፍ ሲል እንዲያ የተነገራቸው አዲስ አማኞች ሰማይ ናስ ይሆንባቸዋል። ደስ ሊሰኙ የሚችሉበት እውነተኛ አጋጣሚም ላይመለስ ያመልጣቸዋል። ወንጌል ይህን አያስተምርም። በጥቁርና ነጭ በዓለም ስንኖር መከራ እንዳለብን ነው

እሚነግረን። የእውነተኛው ክርስትና ማዕበል ደግሞ ስደት ነው።

ደቀ መዛሙርቱ መጀመሪያ ኢየሱስን ቀጥሎም ቃሉን ይዘው ተንቀሳቀሱ። በሁለቱም ጊዜ ማዕበል መጣባቸው። እናም ለዚህ ንዑስ አንቀጽ እንደሰጠነው መግቢያ ጌታ ቢኖርም ወጀብ አይቀርም።

ይናፍቃል፤ ያስናፍቃልም

ማዕበል ያለው ውቅያኖስ፤ ባሕር ወይም ሐይቅ ላይ እንጂ መሬት አይደለም። ስለዚህ ሊያየው እሚፈልግ ሁሉ እዚያው ድረስ መሔድ ይኖርበታል። በሲኒማ ማየትም ከተመልካችነት ያለፈ ምንም ግንዛቤ አያስጨብጥም። ቢያንስ አንድ ጉዞ በመርከብ ወይም ጀልባ ማድረግ ግን ትልቅ ዕድል ይሆናል።

እኔም ይህንን አጋጣሚ ካገኙት መካከል ነኝ። የመጀመሪያው የመርከብ ጉዞዬ ይህን ረቂቅ በምጽፍበት ወቅት ሠላሳ ዓመት ሊሆነው ነው። ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ እንኳ ትናንት የሆነ ይመስል በሚገባ አስታውሰዋለሁ። የመርከበኝነት ሥልጠናዬን በአሥመራ የባሕር ኃይል ማሠልጠኛ ማዕከል ጨርሼ ወደምፅዋ እንደተመለስኩ የሥራ ድልድሌና የምሠራበት መርከብ ተነገረኝ። እኔም መርከቧ ወደቆመችበት ሄጄ ሪፖርት አደረግሁ። የመርከቢቷ

የሠፈር ሹም እኔና ዘጠኝ ባልደረቦቼን እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎ ተቀበለን። እናም ጊዜ ሳያጠፋ መርከቢቱን እያዞረ አስጎበኘን። የእያንዳንዳችንን መኝታ ሥፍራና የግል ንብረት መቆለፊያ ከደለደለ በኋላም እንደየምድባችን ወስዶ ከከፍል ኃላፊዎችና ከመሰል መርከበኞች ጋር አስተዋወቀን። ወዲያውም የምሳ ሰዓት ስለደረሰ ወደ ካፊቴሪያ ወሰደንና ከሰውም ከምግቡም ጋር እንድንቀራረብ ጋበዘን። እዚያው የሚበስል ምግብ ለመጀመሪያ ጊዜ በመብላት የኑሮውን ጣዕም ለመቅመስ ሞከርን። በመጨረሻም የሠፈር ሹሙ መርከበኞች ከምሳ በኋላ ያለውን ኃይለኛ የሙቀት ጊዜ በአልጋቸው ላይ እያነበቡ ወይም አያሸለቡ ስለሚያሳልፉ እኛም እንድንገባበት ነግሮና መልካሙን ሁሉ ተመኝቶ ከአጠገባችን ዘወር አለ። እንግዲህ ያ ቀን ለኔ የብዙ መደነቅና የስኬትም ቀን ሆኖ ተቆጠረ። ለምን ቢሉ እዚያ ለመድረስ የከፈልኩት ዋጋ ቀላል አይደለም። ያ የተጀመረው ገና ለምዝገባ አዲስ አበባ ወደሚገኘው የባሕር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ በሄድኩ ቀን ነው። ያቀረብኩት የትምህርት ማስረጃ ሲመረመር ቆሜ ተመለከትኩ እንጂ እንድቀመጥ ወንበር ያመለከተኝ ሰው አልነበረም። የጤና ምርመራውን ጨምሮ ሌሎቹን መስፈርቶች አሟልቼ እንደተቀበሉኝ ለማወቅ ቀናትን ቆጥሬያለሁ። ከዚያም ወጥቼ ዘመድ ቤት ለማደር የማልጨክነው ሰው ሁሉን ተሰናብቼና አካባቢዬን ለቅቄ

መጓዝና በማሠልጠኛው ማዕከል ውስጥ ለወራት መቀመጥ ነበረብኝ። ጠዋት ማለዳ በሚቆፈንን ብርድ በአካል ማጎልመሻ እንቅስቃሴ ተጀምረው አመሻሽ ላይ በቤተ መጻሕፍት የጥናት ጊዜ የሚገባደዱትን ቀናት ጥርሴን ነክሼ ከመጋተር ሌላ አማራጭ አልነበረኝም። ያ ሁሉ ታልፎ ነው ትምህርቴን በጥሩ ውጤት አጠናቅቄ ወደ ባሕር የዘለቅሁት። እናም ቀኑን ሙሉ ስሜቴ ጥሩ ነበር። ያን አጣጥሜ ሳልጨርስ ግን ታሪኩ ተቀየረ።

አመሻሽ ላይ መርከቢቱ ለአደጋ ጊዜ የምታሰማው የድረሱልኝ ድምፅ ተሰማ። ምን ተፈጥሮ እንደሆነ ለማጣራት ስጠይቅ ሁሉ ሰላም እንደሆነ ግን መርከቢቱ ያንን ድምፅ ለሌላም ጉዳይ እንደምትጠቀምበትና አሁን ለጉዞ እንድንዘጋጅ ማሳሰቧ መሆኑ ተነገረኝ። የምንጓዝ ከሆነ ለምን በጊዜ እንዳልተነገረን ላቀረብኩት ተከታይ ጥያቄም የጉዞውን ምሥጢርነት ለመጠበቅ መሆኑ በአጭሩ ተነገረኝ። እናም እንደ መርከበኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የት እንኳን እንደምንሄድ ሳላውቅ ጉዞዬን ጀመርኩ። ብዙም ሳንጓዝ ኃይለኛው የቀይ ባሕር ማዕበል እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ታላቅ አቀባበል አደረገልን። ዞረን ለመጎብኘት ግማሽ ሰዓት የፈጀችብንን ትልቋን መርከብ እንደ ትንሽ ልጅ አሻንጉሊት ይጫወትባት ጀመር። ሞገደኛው ነፋስ የሚፈልገውን ያህል ውኃ እያፈሰ በመርከቢቱ ወለል ላይ መቸለስ ጀመረ። ትናንሽ

ዓሦች ወደ ቤታቸው ለመመለስ ሲንፈራገጡ ማየት ጀመርን። እኔም ሳልጠጣ እንደሰከረ ሰው መንገዳገድ ጀመርኩ። የምጨብጠው የመርከቢቱ አካል ሁሉ ለመገንጠል የሚታገል ይመስል ነበር። ወዲያ ወዲህ እንኳን ለማለት ብረት መያዝ የግድ ሆነ። ሰውነቴ ለተወሰነ ጊዜ ላይ ታች መናጡን ቢቋቋመውም የኋላ ኋላ ተዳከምኩ። መጀመሪያ ያቅለሸልሸኝ ኋላም ወደ ላይ ይለኝ ጀመር። ጣፍጦኝ የበላሁት ምሳ አይኔ እያየ በደቂቃዎች ልዩነት ወጥቶ ሄደ። ሆዴ ውስጥ የነበረው ሁሉ ሲያልቅ ባዶውን እንዲሁ መጓጎር ጀመርኩ። እየቆየሁ ደግሞ አረንጓዴ የመሰለ ፈሳሽ ሲወጣ ተመለከትኩ።

በዚያ በጨለማ የሚረዳኝ ሰው በዓይኔ ስፈልግ እንደ ጨለማው የጠቆረ አንድ ሳተና ባሕረኛ ተሹለኩልኮ መጣና በባትሪ ፈልጎ አገኘኝ። ግን እኔ አንዲት ቃል ከመናገሬ በፊት በላይኛው ወለል ላይ በአስቸኳይ እንደምፈለግ ነገረኝ። ለካስ ተረኛ ነበርኩ። በአረንጓዴው ቡድን ውስጥ ተመድቤያለሁ። የመርከበኛ እንግዳ የለውማ! እንደ ምንም ላይ ወጥቼ አንድ ነባር ቀዛፊ መሪውን እንዴት መዘወር እንዳለብኝ ሊያስተምረኝ ጀመረ። አሳቤን እዚያ ላይ ማሳረፌ ከቀጣዩ ስቃይ ፋታ ቢሰጠኝም እንኳ ሆዴ ባዶ ስለነበር ጉልበት ከዳኝ። መቆምም አቃተኝ። እዚያው ወለሉ ላይ ቁጭ አልኩ። ዙፋን የሚመስል ትልቅ መቀመጫ ላይ የተሰየመውና ዘና ብሎ የተቀመጠው የመርከቧ ካፕቴን በሞገሳማ ድምፅ “

አይዞህ ትለምደዋለህ፤ እኛም እንዳንተው ነበርን'' ሲለኝ ሰማሁ። ከእኔ ሦስት ሜትር ርቆ ያውም ከኋላዬ ለተቀመጠ ሰው የምመልስበት አቅምም ይሁን አንደበት አልነበረኝም። በልቤ ግን'' አንዴ ብቻ መሬት ልድረስ፡ - የፈለገው ይመጣል እንጂ ዳግም አልመለስም!'' አልኩ። ሁለት ቀንና ሌሊት ውኃ እንጂ ሌላ ነገር ወደ አፌ አልገባም።

በሦስተኛው ቀን ወደ አሰብ ወደብ ስንደርስ ጥሩ ምግብ ተዘጋጅቶ ጠበቀን። እስከማስታውሰው ድረስ እስከዚያች ቀን ድረስ እንደዚያ ምግብ ጣፍጦኝ አያውቅም። ለሁለት ሰው የሚበቃውን ብቻዬን ጥርግ አድርጌ በላሁ። በሚገባ አረፍኩ። ማምሻውን ከጓደኞቼ ጋር ወደ ከተማ ወጥቼ ተዝናናሁ። መርከባችን አንድ ሳምንት ሙሉ በዚያው ወደብ ቆየች። ወዘናችን ተመለሰ። ታዲያ አንድ ቀን ከጓደኞቼ ጋር በመኝታ ክፍላችን ስናወራ የሁላችን ፍላጎት አንድ ሆኖ ተገኘ። '' መቼ ነው ወደ ባሕር የምንመለሰው?''።

አስጨናቂው ማዕበል ተስፋችንን እንድንናፍቅ እፎይ ብለን የምናርፍበትን ቀን እንድናልምም ያደርገናል። ምግብ እንኳን የበለጠ ጣፍጦን የምንበላው ሲርበን እኮ ነው። ለምን ቢሉ በረሃቡ ሰዓት የምግብ ፍላጎታችን የመብያውን ሰዓት እንድንናፍቅ አስገድዶናልና።

ወላጂ እናት ልጇን አቅፋ ደስ የምትሰኘው ስለወለደች ብቻ አይደለም። ምናልባትም ገና ከመጀመሪያው

በአፍላ ዕድሜዋ የእናትነት ምኞት ነበራት። ያ የጀመራት ገና ጮርቃ ሕጻን ሳለች ሊሆንም ይችላል። ስለዚህ እናትነት ለዘመናት አብሮአት የኖረ ሕልም ነው ማለት እንችላለን። ከባልዋ ጋር በጓደኝነት ኳላም በእጮኝነት ብሎም በጋብቻ ስትኖር ሁሉ ጧትና ማታ የምታወጣና የምታወርደው ርዕይዋ እናትነት ነበር ማለት ይቻላል። በሆድዋ ውስጥ ሕይወት እንዲፀነስ ጥቂት ለማይባሉ ሳምንታት፤ወራትና ዓመታት ታግሳም ሊሆን ይችላል። ከዚያም የመጀመሪያዎቹ የእርግዝና ወራት የሚያስከትሉትን ሕመምና የስሜት መዘበራረቅ እየገፋም ሲሄድ ክብደቱንና ተዛማጅ ችግሮችን ተቋቁማ ነው እናት ለመሆን የበቃችው። የወር አበባዋ መቅረቱን ተከትሎ የጧት ማቅለሽለሽና ማስመለስ አሰቃይቷታል። ይህም ምናልባት ድብልቅ ስሜት የፈጠረባት ነገር ነው። በማርገዟ ደስ ስትሰኝ ሕመሙ ደግሞ ተፈራርቆባታልና። የደም ግፊትዋ ጨምሮ በእርግዝናው የመጀመሪያ ሦስት ወራት የማጎፀን ደም መፍሰስ አጋጥሟትም ሊሆን ይችላል። በነዚህ-ጊዜያት ሁሉ ያጋጠሟትን ችግሮች ተቋቁማ ድካሙንም አሸንፋ ሐኪሟም ዘንድ ደከመኝ ሳትል ተመላልሳ ነው ለዚህ ቀን የበቃችው። በተለይ ከስምንተኛው ወር በኋላ በየሳምንቱ ወደዚያው ማዝገም ነበረባት። ጤነኛ ልጅ ለመውለድ ብላ የራሷንም ጤና ጠብቃ ቆይታለች። ለዚሁም ስትል ቡናና ሻይ መጠጣቷን ጣፋጭ ምግቦችን መብላቷን አቁማ ወይም ቀንሳ

ይሆናል። ያም ሳያንስ ምጧ የመጣ እየመሰላት ደጋግማ ወደሆስፒታል ተመላልሳለች። የቁርጡ ቀን ሲመጣም በብዙ ሕመም ለሰዓታት አምጣለች፤ ደምም ፈሷታል። ይህን ሁሉ አልፋ ልጇን ማቀፏ ነው ደስታን የሚያጎናጽፋት። የእናትነት ናፍቆት፤ የእርግዝናው መከራና የምጡ ሕመም ሁሉ ተዳምረው ልጇን የምታቅፍበትን ቀን እንድትናፍቅ አደረጓት እንጂ ፈጽሞ ተስፋ አላስቆረጧትም።

<u>የማለፋችን ተስፋዎች</u>

አብሮን የሌለ ሲመስል ግን ጌታ አብሮን አለ። ያ የማለፋችን ዋነኛው መልሕቅ ነው። በአንድ ወቅት ወደ እንግሊዝ አገር ለስብሰባ ጉዳይ ሄጇ ሰንብቼ ነበር። በዚያም አንዲት እንደኔው ጸሐፊ የሆነች የአገሬውን ሰው ለንደን ላይ ተዋወቅሁና እርስዋ በምትኖርበት ከተማ ደርቢ ወደሚገኘው ወዳጇ ሠፈር ልትወስደኝ ተስማማች። ከረጅሙ የጎዳና ላይ ጉዞአችን በኋላ ሻይ ጠጥቼ እንዳልፍ ፈቃዷ ሆነና ወደቤቷ ጎራ አልኩ። እናም እርስዋ ኩሽና ጉድ ጉድ ስትል እኔ በግድግዳው ላይ የተሰቀሉትን ሥዕሎች፤ ፎቶዎችና የተለያዩ ጥቅሶች መቃኘት ጀመርኩ። ግን አንዱ ላይ ረጅም ጊዜ መውሰዴን ጋባዤ አስተውላ “ ወደድከው?” ስትል ጠየቀችኝ።:እኔም በአዎንታ ራሴን ነቀነቅሁ። ከሦስት ዓመታት በኋላ ዋሽንግተን ላይ ስሞሸር ያንን አስታውሳና

በትራስ ልብስ ላይ አሳትማ በስጦታ ላከችልኝ። ጽሑፉም እንዲህ ይነበባል።

“ አንድ ሰው በአንድ ምሽት የሚከተለውን ሕልም አለመ። በባሕር ዳርቻ ካለ አሸዋ ላይ ከጌታ ጋር የሚራመድ ይመስለዋል። በዚያኑ ቅፅበት ደግሞ ያለፈ ታሪኩን የሚያሳይ ፊልም መሰል ትርዒት በሰማይ ላይ ይመለከታል። እናም ለእያንዳንዱ የሕይወት ጉዞ የሁለት ሰዎችን የእግር ኩቴ ያያል። አንዱ የራሱ ሌላው ደግሞ የጌታ እንደሆነም ይረዳል። የመጨረሻው ትዕይንት ሲመጣ ኩቴዎችን ልብ ብሎ ሲመለከት አንድ ትልቅ ለውጥ ያስተውላል። ይኸውም ጥቂት ለማይባሉ ጊዜያት ኩቴዎቹ የአንድ ሰው ብቻ እንደነበሩ ነው። ይባስ ብሎም እነዚህ ጊዜያት በሕይወቱ ትልቅ አደጋና ፈተናን የተጋፈጠባቸው መሆናቸውን ተረዳ። ሁኔታው እጅግ ስለከነከነው ታዲያ ለጌታ እንዲህ ሲል ጥያቄውን አቀረበ። “ ጌታ ሆይ፡- አንድ ጊዜ አንተን ለመከተል ስወስን ሁሌም አብረኸኝ እንደምትሆን ቃል ገብተህልኝ ነበር። ታዲያ አሁን እዚህ የአንድ ሰው ኩቴ ብቻ የማየው በአስቸጋሪ የሕይወቴ ዘመናት ነው። በጣም በምፈልግህ በነዚያ ፈታኝ ቀናት ለምን እንደተውከኝ አልገባኝም?”።

ጌታም እንዲህ ብሎ መለሰለት። “ የተወደድክ ልጄ ሆይ፡- አዎን እወድሃለሁ። ደግሞም አልተውህም።

t.me/BooksandYou

በአስቸጋሪ የሕይወትህ ዘመናት የአንድ ሰው ኮቴ ብቻ የምታየው እኔ ተሸክሜህ ስለነበር ነው። ያ የኔ ኮቴ ነው!''

አዎን፡- አብሮን የሌለ ቢመስልም ግን ጌታ አብሮን አለ። እስከመጨረሻው ላይለየን ቃል ገብቷልና ያለውን ያደርጋል። ቃሉን ይፈጽማል። የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚነግረን እርሱ ይዋሽ ዘንድ ሰው አይደለም።

መከራ ምርጫም ነው

ለዘብተኞች ለስላሳ ቢጤ ስለሆኑ ብዙውን ጊዜ ተቃውሞ አያጋጥማቸውም። ግንባር ቀደሞች ግን ላመኑት ደፍረው ይጋፈጣሉና ለብዙ አደጋ ይጋለጣሉ።

አንድ ይህንን የሚያነሳ ቀልድ በምሳሌነት እንጠቀም።

ከሳሽና ተከሳሽ ፍትሕን ፍለጋ በዳኛ ፊት ቆመዋል። ዳኛው መዝገቡን ካዩና ሁለቱም ወገኖች መቅረባቸውን ካጣሩ በኋላ ከሳሽ ክሱን እንዲያስረዳ ጋበዙት። እርሱም በብዙ ሲቃ ተከሳሹ ያደረሰበትን በደል በዝርዝር አስረድቶ ጨረሰ።

ይህንኑ በጥሞና የተከታተሉት ዳኛ '' ትክክል ነህ'' አሉና ወደተከሳሹ ዞረው ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ጋበዙት። እርሱም የቀረበበት ክስ እውነትነት እንደሌለው በዝርዝር ገልጾ ጥፋተኛ አለመሆኑን በሙሉ ልብ አስረዳቸው። ዳኛውም ከመጀመሪያው ጀምሮ በመስማማት

ራሳቸውን ላይና ታች ሲያወዛውዙ ቆይተው እርሱንም ‘‘ ትክክል ነህ’’ አሉት።

ይህን ጊዜ ከታዛቢዎች አንዱ የመናገር ዕድል እንዲሰጠው አስፈቀደ። ዳኛውም ስለታዛቢው አቀራረብ ያላቸውን አድናቆት በፈገግታ ገልጸው እንዲናገር ፈቀዱለት። በዚሁ መሠረት ታዛቢው ጉሮሮውን ካጠራ በኋላ ለዳኛው ተከታዩን ጥያቄ አቀረበ። ‘‘ክቡር ሆይ፡- መጀመሪያ ከሳሹ የደረሰበትን በደልና የክሱን ጭብጥ ሰምተው ሲያበቁ ትክክል ነህ ብለውት ነበር። የተከሳሹን የመከላከያ ምስክርነት ከሰሙም በኋላ ያንኑ ደግመዋል። ታዲያ ሁለቱም ትክክል ከሆኑ ጥፋተኛው ማን ሊሆን ነው?’’። ዳኛውም በበኩላቸው ለጥቂት ጊዜ ተግ ብለው ካሰቡ በኋላ አሁንም ፈገግ ብለው እንዲህ መለሱለት። “አንተም ትክክል ነህ’’።

የእምነት ነገር ሲነሣ የዚህ ዓይነት አቋም ያላቸው ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። ሁሉንም ትክክል ስለሚሉት ማንም ደፍሮ በነርሱ ላይ አይነሣም። እንዲያውም እንደ ታላቅ ምሳሌ ይጠቅሳቸዋል። አብዛኞቹም በዚህ ጎራ ያሉት የቀለም ዕውቀት ድኖች አይደሉም። እንዲህ ዓይነቶቹ መከባበርና መቻቻል በተሰኙ ቃላት ተጀቡነው የሚኖሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከውጭ የሚደርስባቸው ስደት እጅግ ጥቂት አልያም ምንም ነው።

የክርስትና እምነት ጅማሪና ፈጻሚ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በዚህ ዓይነት አካሄድ አልተመላለሰም። የአንዳንዶች ክብር እንዳይነካ ወይም ሞራላቸው እንዳይወድቅ በማሰብ አልተለሳለሰም። እውነቱን እውነት ሐሰቱንም ሐሰት ሲል ነው የኖረው።

ለምሳሌ ፈሪሳውያን እጅግ ይጦሙና ከእንስላል ምርት እንኳ ሳይቀር አሥራታቸውን ይከፍሉ ነበር። ኢየሱስ ግን በጦምና አሥራትን በመክፈል የነበራቸውን ታማኝነት ተመልክቶ ሌላው በሂደት እንደሚሻሻል በማመን አላለፋቸውም። ግብዝነታቸውን በአደባባይ ደግሞና ደጋግሞ ነቅፏል። እንዲያውም ለብዙዎች መሰናክል መሆናቸውን ሲጠቁም "ወይ ራሳችሁ አልገባችሁም፤ አለበለዚያ ደግሞ ሌሎች እንዲገቡ በሩን አልለቀቃችሁም " በማለት ልክ ልካቸውን ነግሮአቸዋል። አጋጣሚውን ባገኘና ከነርሱም በተገኘኘ ቁጥር አካሄዳቸውን እንዲያስተካክሉ ጉድለታቸውን ይገልጽ ነበር። " እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ መንግሥተ ሰማያት በመግባት ረገድ ዝሙት አዳሪዎች ይቀድሟችኋል " ሲላቸው ፈገግ እንዲሉ ፈልጎ ነው ብለን ራሳችንን አናታልልም። እነርሱም እንደተለመደ ዘለፋ ቆጥረው ተዘባብተው አልፈውታል ማለት አስቸጋሪ ነው። በሌላም ስፍራ ከተለሰኑ መቃብሮች ጋር አመሳስሎአቸዋል። ውስጣዊ

ሕይወታቸውን ቸል ብለው ውጪውን ለማሳመር ጉድ ጉድ እንደሚሉም በወጭቱ ምሳሌ በግልጽ ነግሮአቸዋል።

ፈሪሳውያኑ ግን ሁሉን ዐውቀን ጨርሰናል በማለት በራሳቸው ከፍታ ላይ ጉብ ስላሉ ከመጀመሪያው ለመመከር ፍቃደኛ አልነበሩምና እርማቱን አልተጠቀሙበትም። ወይም ‘‘ጉድለታችንን የሚጠቁመን አንድ ሰው አገኘን ‘‘ ብለው የክርስቶስን ድፍረት አላደነቁም።

ይልቁንም ማለቂያ የሌለውን ጉዳቸውን በነገራቸው ቀጥር ክብራቸው ስለተነካ እናጠምደዋለን ብለው በፈተኑት ቁጥርም አላዋቂነታቸውን ስላጋለጠ ጠሉት። እስከ መጨረሻውም ሥራችን ብለው ሌትና ቀን አሳደዱት። ሌላው ቀርቶ ለዘመናት የበሽታ ቁራኛ የነበሩትን በምድራዊው ሕክምና ተስፋ የተቆረጠባቸውን ሕሙማን መፈወሱ አላስደነቃቸውም። ከዚያ ይልቅ የተፈወሱትን እየጠሩ አውጫጪኝ ማካሄዱና ፈውስ የተደረገበትንም ቀን ከቀን መቁጠሪያ ጋር ማመሳከር የቀናቸው ይመስላሉ። ከዚህም በዘለለ ከጥላቻቸው የተነሳ በቁሙ ሳለ የፈጠሩበት መከራ በቂ መስሎ አልታያቸውም። ተሰቅሎ ከሞተ በኋላ እንኳ መቃብሩ ላይ ዘበኛ እንዲመደብ ለመጠየቅ ሲሄዱ እፍረት ቢጤ አልተሰማቸውም።

ያለአንዳች ማመቻመች እውነትን መናገሩ ኢየሱስን ዋጋ አስከፍሎታል። ከላይ እንደተጠቀሰውም የምድር

ሕይወቱን በማያቋርጥ መከራ እንዲገፋ አድርጎታል። አገልግሎቱም ሁከትና ስደት የበዛው አሸሙርና አግቦ የማያጣው ነበር። በሰንበት ቀን የፈውስ ፕሮግራም አካሂደሃል ተብሎ ተከሶአል። ከኃጢአተኞች ጋር በመወዳጀትና ወደ ቤታቸው በመግባት አብሯቸውም በመብላት ተወንጅሎአል። ስጦታቸውንም ያለነቀፋ በመቀበሉ ሐሜት አግኝቶታል። የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ በማለቱ አብን ተሳድቧል ተብሎ በድንጋይ እንዲወገር ተበይኖበታል። ቢያንስ አንድ ጊዜ በአገልግሎቱ ላይ እያለ ተይዞ እንዲታሠር ተሞክሮአል። ስለ ትውልዱ ሁኔታ ተደጋጋሚ ነቀፋ ተሰንዝሮበታል። የአብርሃም ልጆች ነን ብለው ቀርበው አባት የለሽ ሊያደርጉና ከጋብቻ ውጭ እንደተወለደ ሊሞግቱት የሞከሩም ነበሩ። አጋንንትን ለማውጣት የበረታውን ጋኔን ማለትም ብዔል ዜቡልን ይጠቀማል ተብሎ በአደባባይ ተወርቶበታል። ከዚያም አልፈው አጋንንት እንዳለበት ሊያጣሩ የመጡም ነበሩ።

በመጨረሻም በደል ሳይገኝበት ተከሶ ሊቀ ካህናቱ ፊት ቀርቦአል። ከዚያው በተያያዘ በአንድ ጀምበር ሁለት ችሎት ቆሞ ጉዳዩ እንዲታይ ተደርጓል። ግን በሁለቱም አገረ ገዥ ዳኞች ማለትም ጲላጦስና ሔሮድስ ከጥፋት ነፃ መሆኑ በይፋ ተረጋገጠ። ጲላጦስ ነፃ ነው ብሎ ወደ ሔሮድስ የሰደደው ሲሆን ሔሮድስም በበኩሉ በደል ስላላገኘበት

እንደገና ወደ ጲላጦስ መልሶታል። እንዲያውም ለሁለተኛ ጊዜ ክሱን እንዲሰማ የተገደደው አንደኛው አገረ ገዥ "ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም፤ ባይሆን ገርፌ ልልቀቀው " ቢልም ሰሚ ባለማግኘቱ በከንቱ ከሚፈሰው ደም ንጹሕ መሆኑን ለማሳየት እጁን በሕዝብ ፊት ታጥቧል። ነፃ የተባለው ኢየሱስ ግን ያለ ፍትሕ በአደባባይ ከወንበዴዎች ጋር ተሰቀለ። የሚገርመው ደግሞ ለመፈታት የነበረችውን የመጨረሻ ዕድል እንዳይጠቀም እንኳ ከርሱ ይልቅ በርባን የተባለው ነፍሰ ገዳይ እንዲለቀቅ ተደርጓል።

ይህ ሁሉ የደረሰበት የተራቡትን ስላበላ ለተጣሉት ስለራራ ወይም ለሌላ በጎ ሥራው ሳይሆን እውነትን በድፍረት ለመናገር ስለጨከነ ብቻ ነው። በጥቅል አነጋገር ማመቻመች ከተቻለ ነውጡን ማርገብ ወይም ጭራሹኑ ማስቀረት ሲቻል ኢየሱስን እየመሰሉ መኖር ግን ስደትን ይጋብዛል።

ያ ደግሞ ምርጫ ነው!

4

በረከቶቹ

የሚያስጠጋ ማዕበል

ማዕበል የሚያማርር እንጂ የሚያዘምር አይደለምና ወደ ሕይወታችን እንዲመጣ ጊዜ ወስደን ወይም ጦም ይዘን አንጸልይም። እንኳን ምርጫው እያለን ይቅርና በአጣብቂኝ ተይዘንም ቢሆን እንኳ በነውን እንጂ ክፉውን ለራሳችን አንመኝም። እንዲያውም መላው ካልጠፋን በቀር ማዕበሉን እንኳን ለራሳችን ለሚጠሉንም ይሁን ለሚጣሉን አንመኘውም። ግን የድንገተኛው ወጀብ መምጣት የሚመጣበት ጊዜና የሚቆይበት ርዝመት ከዚህ ጋር ፈጽሞ ተያያዥነት የለውም። ወይም በሌላ አነጋገር ጸለይንም አልጸለይን ተመኘንም አልተመኘን ‘‘ነገርዬዎቹ’’ ጊዜአቸውን ጠብቀው ብቅ ማለታቸው አይቀሬ ነው። አዎን ከየት እንደመጡ እንዴትስ እንደመጡ ሳይታወቅና ቅድመ ዝግጅትም ሳይደረግ በድንገት ከች ይላሉ። ያኔ የሚያዘውና የሚጨበጠው ይጠፋል። አራቱም አቅጣጫዎች ይከበባሉ። መላውና መፍትኼው ይርቃል።

ያኔ የሚቀረውና መቼም ቢሆን እማይረፍድበት ማምለጫ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ብቻ ይሆናል። በርግጥም መሆኑ ካልቀረ ችግሮቻችንን ይዘን ወደ ጸጋው

ዙፋን አቤት እንዳንል የሚያቆመን አይኖርም። አንድ ታዋቂ የወንጌል ሰባኪ "ወደ ኢየሱስ የሚያስጠጋን ችግር በዋጋ ሊተመን የማይችል ቅርስ ነው" ሲሉ ተደምጠዋል።

እንደ መከራ ያለ ወደ ኢየሱስ የሚያቀርበን እርሱንም ወደ እኛ የሚያመጣው አጋጣሚ የለም። በክፉ ቀን ያለ እርሱ ማን አለን? በርግጥም አማራጭ ሲታጣና መላ ጠፍቶ ዙሪያው ገደል ሲሆን ወደ አፅናፊ ዓለሙ ፈጣሪ ብቻ የሚያደርሰው በር ክፍት መሆኑ ታላቅ ዕድል ነው። ሥጋዊ ዓይኖች ተጨፍነው ውስጠኛው ሲከፈት ብዙ አስገራሚ ነገሮች ይከሰታሉ። የዘነጋነው የመሰለንና ከዓመታት በፊት ያጠናነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ድንገት ትዝ ይለናል፤ በጾም ወደፊቱ መቅረብና ራስንም ማዋረድ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይከሰትልናል ፤ ካየናቸው ሰንበት ያሉና በሰላሙ ቀን ያልጠየቅናቸው በጸሎት የሚተጉ በምልጃ የሚታደጉ በምስጋና የሚያነጉ ወገኖች ገጽታ ድቅን ይልብናል። ከምንም ይልቅ በመከራ ስንከበብ ያለ እግዚአብሔር ረድዔት የትም እንደማንደርስ በውል ይገባናል። ያለበለዚያማ "ሁሉን በልክ" አድርጎ ዘና ባለ ሕይወት አያመሰገኑ መኖር ይቻላል።

በዚህ አጋጣሚ ከዓመታት በፊት የገጠመኝን አንድ ሁኔታ ለማንሣት እወዳለሁ። ለአስቸኳይ ሥራ ጉዳይ ወደ ጎረቤት አገር ሄጄ ነበር። የሄድኩበትን ተልዕኮ በትልቅ ስኬት ጨርሼ ስመለስ አምላኬን ለማመስገን እጅግ ቸኮልኩ። ጉዞው

ራሱ ታሪካዊና ፈጽሞ የማይታሰብ ከመሆኑም በላይ ነገሮች ተዓምራዊ በሆነና በሚታይ አኳኋን ተከናውነውልኝ ነበር። እናም ስለ መልካምነቱ ስለ ጥበቃው ስለ ሞገሱና በጥቅሉም በጉዞዬ ስላየሁት ቸርነቱ ለማመስገን ልቤ መነሣሣቱ ያለምክንያት አልነበረም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለሁ ነበር ካረፍኩበት የአዲስ አበባው ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ብዙም ሳይርቅ ያለ አንድ የወገኖች ሕብረት የታወሰኝ። ስለዚህ በወገኖች ተቋቁሞ በወገኖች ሥራውን ወደሚያካሂደው ወደዚያ የሕክምና ማዕከል በታክሲ ገሠገሥኩ።

ገና ከጥንስሱ የማውቀው ይህ ዘመናዊ ክሊኒክ በርካታ መንፈሳዊ እሤቶች ነበሩት። በመጠበቂያው ክፍል ውስጥ ለስለስ ያለ ነፍስን የሚያረሰርስ ዝማሬ ይደመጣል። በየጠረጴዛው ላይ ትራክቶች፤ መንፈሳዊ ጋዜጦችና መጽሔቶች በሥርዓት ተሰባጥረው ይቀመጣሉ። ጧት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሠራተኞቹ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ይሰበሰቡና ውሎአቸውን በጸሎት ለእግዚአብሔር ያስረክባሉ። ከምንም ይልቅ ወደዚያ ለሕክምና የሚመጡ ሕሙማን ሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውም እንድትድን ይማልዳሉ። በምሳ ሰዓት ዕረፍታቸው ደግሞ ተመልሰው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ያነባሉ።

በመሃሉም ለሚፈጠር ማንኛውም አስቸኳይ ጉዳይ የክሊኒኩ ሠራተኞች ተጠራርተውና ተሰብስበው ይጸልያሉ።

ዓርብ ከሰዓት በኋላ ሌላ ፕሮግራም በክሊኒኩ ውስጥ ይካሄዳል። ይኸውም የአካባቢው ሠራተኞች መጥተው በዚያ የሚያደርጉት ሕብረት ነው። በየሳምንቱ ቅዳሜ ምሽት ደግሞ የአዳር ጸሎት ይኖራል። እንዲያውም ከነዚህ የተወሰኑትን የመካፈል ዕድል ገጥሞኛል። በተለይ በአንዱ የአዳር ጸሎት ላይ በአቅራቢያው ያልፉ ከነበሩ ሴቶች አንዷን ተጠናውቶ የነበረ ኣጋንንት መሐል አስፋልት ላይ እንደጮኸ አስታውሳለሁ። በነዚህ ጊዜያት የተጋበዙ አገልጋዮች ይገኛሉ። እግር ጥሎአቸው ወይም ሕክምና ፈልገው የሚመጡም ቢሆኑ የማገልገል ዕድሉ ይሰጣቸዋል። ባጠቃላይ ቤቱ ያለማቋረጥ ምስጋናና አምልኮ ያለበት ነው።

እናም ይህን ሁሉ እያሰብኩ ደስ ደስ እያለኝ የተደረገልኝን ስነግራቸው ምን ያህል እንደሚጽናኑ እያሰብኩ ዋናውን በር አልፌ ወደ እንግዳ ክፍሉ ዘለቅሁ። ግን ጥቂት የማውቃቸውን ሠራተኞች ባላይ ኖሮ እዚያ መድረሴን እርግጠኛ ባልሆንኩ ነበር። በርግጥም ሌላ ቦታ የሄድኩ እስኪመስለኝ ድረስ ነገሮች ተለዋውጠዋል። አዳዲስ ሠራተኞች ላይ ታች ይላሉ። የዝማሬ ድምፅ ፈጽሞ አይሰማም። በዚያ ምትክ አየሩን ለመሙላት ደግሞ አውሮፕላን ላይ የምናደምጠው በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ

ሙዚቃ ሳሎኑን ሞልቶታል። ባናት ባናቱ የተደራረቡ ወቅታዊ ጋዜጦችና መጽሔቶች ጠረጴዛውን ሞልተዋል። ግን ከመካከላቸው አንዱ እንኳ ስለ ወንጌል እሚናገር አልነበረም። አንዳቸውም ለነፍስ የሚበጅ ቁም ነገር አላዘሉም። የደረስኩት በምሳ ሰዓት ቢሆንም ሠራተኞቹ ግን መጠበቂያ አዳራሹን ያጣበቡ እንግዶቻቸውን ለማስተናገድ ላይ ታች ይላሉ። በየደቂቃው አንድ ነጭ ጋውን የለበሰ ሰው ውልብ ይላል። ፈጥኖ ይራመዳል፤ እንደ መሮጥም ይላል። ሁሉ ይካለባሉ። የአንዱን በሽተኛ ጥያቄ ከመመለሳቸው በፊት የሌላኛውን ያደምጣሉ። ሰላምታ መስጠትም ይሁን መቀበል የተከለከለ ይመስላል። ቀድሞ ሮጠው የሚያቅፉኝ ሠራተኞች ዛሬ አይተው እንዳላየ ሲያልፉኝ ተመለከትኩ። እንደ እንግዳ የተቀበለኝ የለም። የበሽተኛ መቀመጫም ገና ዱሮ ሞልቶአል። ስለዚህ በምንም መልኩ ቦታ እንደሌለኝ ተረዳሁ።

ክፉኛ አዘንኜና አንገቴን ነቅንቄ ልወጣ ስንደረደር ዋናው በር ላይ እሚያቆመኝ የተለየ አጋጣሚ ተፈጠረ። ይኸውም አንድ ስገባ እንኳ ዘወር ብዬ ያላየሁት ትሑት የክሊኒኩ ጠባቂ ያቀረበልኝ ልብ የሚገባ ሰላምታ ነበር። እኔም አጸፋውን ዝቅ ብዬ መለስኩ። በዚያው አልተለያየንም። ይልቁንም እርምጃዬን ከገታሁ በኋላ እዚያው እንደቆምኩ

ጥቂት አወጋን። አጋጣሚውን ተጠቅሜም አንዳንድ ጥያቄዎችን ወረወርኩ።

“ የምሳ ሰዓት ጸሎት ቀረ እንዴ?”

“ ገና ዱሮ! አሁንማ ባተሌዎች ነን።”

“ የዓርቡም ሕብረት ታሪክ ሆኗላ?”

“ ጊዜው ሲኖር አይደል...”

“ እዚህ እየመጡ ሕብረት ያደርጉ የነበሩ ወገኖችስ?”

“ አሁን አይመጡም”

“ ጠዋትስ? ይጸለያል?”

“ ገና ስንመጣ ቤቱ ሙሉ ነው።”

“ ይሁን፤ የቅዳሜው አዳር ግን አይሰረዝም?”

“ እየቀለድክ መሆን አለበት፤ ከሰኞ እስከ ዓርብ የደቀቀ ጉልበት እንዴት ቅዳሜ መሬት ይይዛል?”

“ ባጠቃላይ ጸሎትና ሕብረት አያስፈልግም ነው የምትለኝ?”

“ እንደሱ ነው!” አለኝ በምፀት።

“ግን ለምን?” በማለት የማሳረጊያ ጥያቄዬን ሰነዘርኩ።

“ አየህ ያኔ እንደጀመርን ብዙ ችግሮች ነበሩን። ከከተማይቱ የጤና ቢሮ የሥራ ፍቃድ ማግኘቱ ቀላል እንቅፋት አልነበረም። የማስተዋወቁ ጉዳይም ራሱን የቻለ ፈተና ነበር። ዘመናዊ መሣሪያዎችን ማስገባትና መገጣጠም ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ነው ብዬ ላንተ አልነግርህም። ያ ሁሉ

አንድ በአንድ አለፈ! አሁን ሥራችን ብር መሰብሰብ እንጂ መጸለይ እንዴት ሊሆን ይችላል? ”

ያ ሰው እንዲህ የልቡን ሲያጫውተኝ ሐዘኑ በፊቱ ላይ የሚነበብ ነበር። እንዳለው ሁሉም አልፎ “ጸሎት ወደማያስፈልግበት” ደረጃ ተደርሶ ነበር። በጊዜው ለማግኘት አስቸጋሪ የነበረው የሥራ ፈቃድ ተገኝቷል። መሣሪያዎቹ ያለብዙ ችግር ገብተዋል። ገሚሶቹም ከአገር ውስጥ በጥሩ ዋጋ ተገዝተዋል። የማስተዋወቂ ሥራ እጅግ ፍሬያማ ለመሆኑ ደግሞ መጠበቂያ ክፍሉን የሞላው ታካሚ በቂ ምስክር ነው። እናም ወገኖቻችን ያኔ ብር በመሰብሰብ ተጠምደው ጸሎት ፋሽኑ ያለፈበት ተግባር ሆኖ ነበር። ግን በጌታ ፊት ሕብረት ማድረጉ ከዚያም ያለፈ ትርጉምና ጠቀሜታ እንደነበረው የተረዱ አልነበሩም።

ለማንኘውም እንዲሁ አልዘለቀም። ብዙም ሳይቆይ የንግዱ ሽርክና ባለመስማማት ፈረሰ። ከባለቤቶቹ እንዱ በአስተዳደር ሥራ ይጠቅሙናል ብሎ ያስጠጋቸው ግን ከነርሱ ጋር ተመሳሳይ እምነት የሌላቸው ሰው ሥራውን ተቆጣጠሩ። ዋና ዋና የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ተዋንያንንም አንድ በአንድ አሰናበቱ። በዚያ ክፍተት ደግሞ የራሳቸውን ሰዎች አስጠጉ። ባጠቃላይ በዚያ ቤት ተጀምሮ የነበረው ታላቅ መነቃቃት በዚህ መልኩ ተዳፈነ።

ያጋጠሙንን ችግሮች ሁሉ ወደሁሉን ቻዩ አምላክ ለመጠጋት ካልተጠቀምንባቸው በቀር ጊዜያቸውን ጠብቀው ወደሚያስቆጩ ኣጋጣሚዎች ይቀየራሉ:: በዚህ አሳዛኝ ታሪክ ውስጥ የሆነውም ይኸው ነው። የክሊኒኩ ባለቤቶችና ሠራተኞች መጀመሪያ በነበሩበት ሁኔታ ቢቀጥሉ ይህ ታላቅ ውድቀት ባልተፈጠረም ነበር። ያም ከሆነ በኋላ ከባላንጣዎች ጋር እሰጥ አገባ ከመጀመር ይልቅ ተመልሰው የእግዚአብሔርን ፊት ቢፈልጉ ሌላ አንድ ዕድል በኖራቸው ነበር። ያንን ሁሉ አልተጠቀሙበትም። አዎን ኋላ ከመቆጨት ይልቅ ያጋጠሙንን ችግሮች ሁሉ ወደ ሁሉን ቻዩ አምላክ ለመጠጋት እንጠቀምባቸው። እናም አናባክናቸው!

ወጀብ ይለያል

የማዕበል አንዱና ዓይነተኛ ጥቅሙ ገለባውን መለየቱ ነው። አዎን ማዕበል አሳምሮ ይለያል (ለ ላልታ መነበብ ይኖርባታል)። በሰላሙ ጊዜ አፋሽና አጎንባሽ የነበረው ሁሉ መከራ ሲመጣ ገለል ይላል። ሳይነገረው ሥፍራ ይለቃል። ደጀ ሰላሙን ቤቱ ያደረገውና በእኔ በኩል ሳታልፉ ሰማይ አትደርሱም ባዩ አስመሳይ ደግሞ ስደት ሲነሳ ሯጭነቱንም ያስመሰክራል።

ስለሁለት ፍቅረኛሞች የሚነገር አንድ ቀልድ አለ። ወደ ጫካ ሄደውና በለመለመው መስክ ላይ ተቀምጠው

ሲጫወቱ በርካታ ወጎችን ተጋርተው ነበር። በተለይም ተቃቅፈው ንጹሑን ነፋሻ አየር ሲምጉ ስሜታዊነት ተጠናውቶአቸው ነበር። ምድሩን ለቅቀው ወደራሳቸው ዓለም ገብተው ነበርና ስለሚናገሩት ነገር ብዙም አልተጨነቁም። እናም ቃል ኪዳናቸውን " ክፉሽን አያሳየኝ፤ ከአንተ እኔን ያስቀድመኝ" በሚሉ ዓይነት ንግግሮች ሲለዋወጡ ሳለ አንድ አዳኝ(ኝ ይጠብቃል) ከተፍ ይላል።

" እጅ ወደላይ!"

" ምን አጠፋን?"

" እሱ ሌላ ጥያቄ ነው፡ አሁን አንድ ሰው ማሰናበት አምሮኛል፤ ከሁለታችሁ ማንን ልግድል?"

" እኔ የምጦራት እናት አለችኝ" አለች ሴትዋ።

" ማየት የተሳነው አባት አለኝ፤ ሌላ ልጅ የለውም፤ የሷ ቤተሰብ ግን አንድ ቁና ነው" አለ ወንድየው።

" እኔ ክርክር አልፈልግም፤ ማንን ልግደል? ያለበለዚያ ራሴ መርጣለሁ" ።

" ክፉሽን አያሳየኝ ብሎአል፤ ስለዚህ እሱን ግደለው!"

" ከአንተ እኔን ያስቀድመኝ ስትል ነበር፤ እንደ ቃልዋ አስቀድማት"

"ጊዜዬን አታጥፉብኝ፤ አንድ ሰው ምረጡ ነው እምለው!"

"በቃ እሷን ግደላት!"

“የለም፤ እሱን ግደለው!”

“ ይኸው ነው በቃ” አለ አዳኙ እየሳቀ “ ከዛፉ ኋላ ተቀምጬ የምታወሩትን ሳዳምጥ ነበር። ያ ሁሉ መሓላና ግዝት ለዚሁ ነው? መልቲ ሁላ፤ በሉ ከዚህ ጥፉ!”።

ከዚሁ የሚመሳሰል አንድ ሌላ እውነተኛ ምሳሌ እናከል። እንደሚታወቀው የኮሙኒዝም ዘመን ዓይነተኛው ፍልስፍና “እግዚአብሔር የለም!” የሚል ነበር። እናም ከእውቁ ሪቻርድ ዉምብራንድ ጀምሮ የእምነት ሰዎች በሰሻሊስት አገሮች ስደትን የጠገቡ አሁንም የሚጠግቡ መሆናቸው የአደባባይ እውነት ነው። ታዲያ ከነዚሁ አገሮች በአንዱ የአካባቢው ክርስቲያኖች በሰዋራ ሥፍራ ባለች ምድር ቤት ውስጥ ተሰብስበው ሲጸልዩ ሳለ በድንገት ሁለት ወታደሮች ይደርሱባቸዋል። ሁሉም ሰው ለጸሎት ከተንበረከከበት እንዲነሣ ካደረጉ በኋላ መሣሪያ ደቅነው ለሁለት እንዲከፈሉ ቀጭን ትእዛዝ ይሰጧቸዋል። እምነታቸውን ለመካድና ሕይወታቸውን ለማትረፍ የሚፈልጉ በሰላም ወጥተው እንዲሄዱ ተፈቀደላቸው። በተቃራኒው ደግሞ ለእምነታቸው ለመሞት የሚፈልጉ እዚያው አዳራሽ ውስጥ እንዲቆዩ ተጠየቁ። ምርጫው በታወጀ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ያለምንም ማመንታት ከጉባዔው ሦስት አራተኛ ያህሉ ሹልክ ብለው ወጡ። ወታደሮቹ አሁንም ለቀሩት ተጨማሪ የማሰቢያ ጊዜ ሰጡ።

አሳቡን የሚቀይር ሰው ካለ አንድ ተጨማሪ ዕድል መኖሩን አስታወቁ። አሁንም ጥቂት ሰዎች ቤቱን ለቅቀው ወጡ። በመጨረሻም አንደኛው ወታደር ለቀሪዎቹ ቆራጥ አማኞች እንዲህ አላቸው። “ አሁን ጸሎቱን አብረን መቀጠል እንችላለን፤ እኛም እንደ እናንተው የምናምን ወታደሮች ነን። ግን ሕብረት ማድረግ የምንፈልገው ከጨከኑት ጋር ብቻ ነው፡ ያለበለዚያ ራሳችንን ለአደጋ እናጋልጣለን!”።

ፈተና አዳዲስ ከዋክብትን ያፈልቃል። ለምሳሌም ያ ታላቅ ማዕበል በጴጥሮስ ውስጥ የነበረውን ዕምቅ ብቃት ፈንጥቋል። በተለይም ደግሞ ዕድሉ ለሁሉም ከመሰጠቱ አካያ ሲታይ ጴጥሮስ አዳኙን ለመምሰል የወሰደው ቆራጥ ርምጃ የሚደነቅ ነው ። ጴጥሮስ “ ጌታ ሆይ፤ አንተስ ከሆንክ በውኃው ላይ እንድራመድ እዘዘኝ!” ብሎ ላቀረበው ጥያቄ ኢየሱስ ሲመልስ “ ና” ነበር ያለው። ያ ደግሞ አበረታች ነበር። ስለዚህ በጀልባዋ ላይ የነበሩ ሁሉ እንደርሱ በመጠየቅ በዓለም ታሪክ ያልተሞከረውን በውኃ ላይ የእግር ሽርሽር የመሞከር ዕድል አግኝተው ነበር ማለት ይቻላል። በርግጥም ጴጥሮስን ቀድመውም ሆነ ተከተለው “ እኔም ልምጣ?” ለማለት የሚያግዳቸው አልነበረም። ግን አንዳቸውም ይህን ሊያደርጉ አልደፈሩም። ጴጥሮስ ማንም ያልሞከረውን ለመሞከር በፈቃደኝነት እጁን አንሥቶአል። ያም ወደፊት የሚኖረውን የመሪነት ሚና አጉልቶ አሳይቷል። የአዲስ ኪዳኗ

ቤተክርስቲያን በተመሠረተችበት በዚያ ቀንም ቀድሞ ብድግ ያለው በድፍረትም የሰበከው እርሱ ነበር። በዚያ ቀንም ይሁን በሌሎች ጊዜያት ብቃቱን ስላስተዋሉ ከጌታ የተሰጠውንም ሹመት ስለተቀበሉ ሊሰብክ በመጀመሩ ሐዋርያት ወዳጆቹ አልተቃወሙትም።

እንዲህ የሚል ዝማሬ አለ።

“በባሕር ውኃ ላይ በተናወጠው፤

ጴጥሮስ ተራመደ ታምኖ በጌታው።

ነፋስ ሲበረታ ማዕበል ሲያስገመግም፤

ወደ ኋላ አየና ጀመረ ሊሰጥም።”

ስለጴጥሮስ ስናስብ የምንለው ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። “ ዓይኑን በኢየሱስ ላይ አድርጎ በውኃ ላይ መራመድ ጀመረ፤ ዓይኑን ከአዳኙ ላይ ሲያነሳ ግን መስጠም ጀመረ።” ከዚህ ይልቅ ግን ዓለም ከተፈጠረ በውኃ ላይ የተራመደ የመጀመሪያው ሰው እንደሆነ ብናስታውስ የተሻለ ይሆናል። ምንም እንኳ በጥሪና በትምህርት ሁሉም እኩል ቢሆኑ ሌሎቹ ጎመን በጤና ብለውና አርፈው ሲቀመጡ አዳኙ ያደረገውን ለመኮረጅ የደፈረ በእምነትም የተሻገረ ብቸኛ ደቀ መዝሙር ነው። ታሪኩ የተጻፈልን እኛም ያንን አንብበን ለተሻለ እምነት እንድንገሠግሥ እንጂ በሌሎች ላይ ስሕተትን እንድንፈልግ አልነበረም። በሌላ አነጋገር ጥሪያችን

ገብተን መወዳደር እንጂ ዳር ቆመን ነጥብ መቁጠር አይደለም።

በተጠባባቂነት ወንበር ላይ መቀመጥና ወደ ውድድሩ ሜዳ ገብቶ መጫወት በምንም መለኪያ አንድ ሊሆኑ አይችሉም። ተሰላፊዎቹም ይሁኑ ተጠባባቂዎቹ የአንድ ክለብ ተጫዋቾች እንደሆኑና ቡድኑ ካሸነፈ ሁሉም የአሸናፊነት ሜዳሊያ እንደሚያገኙ ይታወቃል። ግን ተሰላፊዎቹ ገድል የመሥራት ዕድል ተሰጥቶአቸዋል። ግብ ማግባት የሚችሉት እነርሱ ናቸዋ። የተጠባባቂዎቹ ዕድል ፈንታ የሚወሰነው ተሰላፊዎቹ በሚያሳዩት ብልጫና በሚያመጡት ውጤት ነው። እናም ጨዋታው እስኪያልቅ እንደማንኛውም ተመልካች ከማጨብጨብና ከማፏጨት ያለፈ ምንም ሊያደርጉ አይችሉም። ስለዚህ ውድድሩ ውስጥ መግባት እንጂ ተጠባባቂነት ጥሩ ምርጫ አይደለም።

በአሜሪካ ዘመናዊ አርበኞች የተሰኙት የእሳት አደጋ ሠራተኞችና ፖሊሶች ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩት ጦር ሜዳ ሄደው ሳይሆን በዓለም አቀፉ የንግድ ማዕከል ሕንፃ ፍርስራሽ ውስጥ ከሞት ጋር ተፋልመው ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የብዙዎቹ ስም በጀግንነት መዝገብ ላይ ሰፍሯል። የሚንቦገቦገው እሳት ውስጥ እየዘለሉ በመግባት ነፍሳትን ነጥቀው በማውጣት ከፍርስራሽ ውስጥም በሞት ወጥመድ

የተያዙትን ጎትተው በማትረፍ ብሔራዊ ጀግኖች የተሰኙበትን ገድል የፈጸሙት በመከራ ቀን ነው።

ደረታቸው በሜዳሊያ የተንቆጠቆጠ ተዋጊዎችም በጭንቅ ቀን ደምቀው ያበሩ ናቸው። አጠገባቸው የወደቀው ቁስለኛ አንዲት ጽዋ ውኃ ሲለምን መሬት በአረር ስትነድ በሬሳ ላይ ተረማምደው የጠላትን ፈንጂ ረግጠው ምሽጉንም ደርምሰው ድልን ለወገናቸው ያበሰሩ አንበሶች እንጂ የመሸታ ቤት ደንበኞች አይደሉም። ማዕበል ይለያል። ጀግኖች ሲሸለሙ ቦቅቧቆች ያፍራሉ። በሰላሙ ጊዜ ብዙ የደሰኮሩ ጭንቅ ሲመጣ መግቢያው ይጠፋቸዋል። በሰላሙ ዘመን ቦታ ጠበበን የሚሉ የአፍ ክርስቲያኖች ስደት ሲመጣ ፈጥነው አድራሻቸውን ይቀይራሉ። ብን ብለውም ይሰወራሉ።

በመከራ ውስጥ መሠራት

ሰው መከራ ሲበዛበት ምን ይሆናል ብለን ይህንን ንዑስ ምዕራፍ መጀመር እንችላለን። የምናወራው ስለአብዛኛው ሰው እንደሆነ እያሰብን ይሁን።የሚሆነው ነገር እንደሁኔታው ይለያያል። ራሱን ለዚያ መከራ ያላዘጋጀ ከሆነ ግር ብሎት ከአካባቢው ሊሰወር ይችላል። ክስተቱ ከተነገረውና ከሚያውቀው ውጭ ከሆነበት ደግሞ ‘‘ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥቼ ቢሆን ነው’’ ብሎ ሌላ ምርምር ውስጥ ይገባ ይሆናል። መከራው ከሚሸከመው በላይ ከሆነበትም እንዲቀርለት ሊደራደር ይችል ይሆናል።

አስቀድሞ ትርፍና ኪሣራውን ያሰላ ብርቱ የክርስቶስ ወታደር ከሆነ ግን ውጤቱ የተገላቢጦሽ ነው እሚሆን። በዓለም ሳለ መከራ ጎረቤቱ እንደሆነ የተገነዘበ ይህች ምድር ጊዜአዊ ድንኳን እንደሆነች አስቦ ዛሬን ብቻ ሊኖርባት የሚያቅድ ከዜግነት ይልቅ ስደተኝነቱ ጎልቶ ለሚሰማው አማኝ በጥቅሉ ማዕበል የሕይወት ጥላ እንደሆነ በአንድ ድምጽ ለተስማማ ግለሰብ መከራ ትምህርት ቤቱ ነው። ለዚህም ነው ጳውሎስ በእምነት ልጁ ለሆነው ጢሞቴዎስ እንዲህ የሚል ታላቅ ግብዣ ጽፎ የሰደደለት። "እንደክርስቶስ በጎ ወታደር አብረኸኝ መከራን ተቀበል"

ከደላን እኮ ማራናታ ልንል አንችልም፡ እዚሁ መንግሥተ ሰማይን ቀምሰናታላ። ስለዚህ ስለእምነት እሚቀበሉት መከራ ምንነት የገባውና የበራለት ሰው በመጀመሪያ ጠንካራ ፈቀቅ ሲልም አመስጋኝ ነው እሚሆን። ለምን ቢሉ አቤንኤዘር ወይም እግዚአብሔር እስከ አሁን ረድቶናል ማለት የሚችለው እኮ የዚያ ዓይነት ሰው ነው። በዚያ ላይ ደግሞ ጻድቅ ስለወንጌል መከራን ሲቀበል በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋው ትልቅ ነው። ኢዮብን የመሰሉና በታላቅ መከራ የተመቱ ሰዎች በታሪክ ውስጥ ካሉ በጣም ጥቂት መሆን አለባቸው። እርሱ ግን ከዚያ ሁሉ በኋላ እንዲህ አለ " እግዚአብሔር ሰጠ፤እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን!"። የደረሰበት መከራ ብዙ እጅግ ብዙ

እንጂ ጥቂት የሚባል አይደለም። በተመሳሳይ ቀን በአንድ ሰው ላይ ሊደርስ የሚችለው የመጨረሻው መከራ ደርሶበታል። ለማስታወስም ያህል የመከራው ዜና መዋዕል እንዲህ ነበር።

1) የሳባ ሰዎች አደጋ ጥለው በሰይፍ ስለት ጠባቂዎቹን ገድለው ሲያበቁ የሚያርሱትን በሬዎች እንዲሁም በአቅራቢያው የሚግጡትን አህዮች ዘረፉ።

2) ከሰማይ የወደቀ እሳት ወይም ብዙዎች እንደሚስማሙበት መብረቅ ወርዶ በጎቹን አቃጠለ፤ ጠባቂዎቹንም ገደለ።

3) ከለዳውያን በበኩላቸው በሦስት ዙር አደጋ ጣሉና በሰይፍ ስለት ጠባቂዎቹን ገድለው ግመሎቹን ዘረፉ።

4) ወንዶችና ሴት ልጆቹ በሙሉ በታላቅ ወንድማቸው ቤት እየተጋበዙ ነበር፤ ታላቅ የበረሃ ዐውሎ ነፋስ የነበሩበትን ቤት አራት ማዕዘኖች ስለመታ ቤቱ ላያቸው ላይ ተደረመሰ። ሁሉም ሞቱ።

እንግዲህ ይህ ሰው ምን ተርፎታል? ዕድሜውን በሙሉ የደከመበትን ንብረት በአንድ ጀምበር አጥቷል፤ በርሱ ዘመን የሰው ሃብት እሚለካው ባለው የቀንድና የጋማ ከብቶች ብዛት ነበር። ግን ግመሎቹ፤ አህዮቹ፤ በጎቹና በሬዎቹ ሁሉ ተዘረፉ። ከምንም ይልቅ የሚሳሳላቸውን ልጆቹን ተነጥቋል!

እርሱ ግን በተራው እንደሚስቱ ምክር ከመሳደብ ይልቅ እግዚአብሔርን ሊያመሰገን መርጧል።

መከራ ሰውን የበለጠ ያጠነክረዋል እንጂ በቀላሉ አይገድለውም። ብርቱ ግዳጅ የሚጠብቃቸው ወታደሮች አስቸጋሪ ሥልጠና የሚወስዱት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። እሳት እየተራመዱ በጭቃ ውስጥ እየተንከባለሉ በጨለማ እየዳከሩ የውጊያ ስልትን ያጠናሉ። ከዚያ በኋላ በቁርጡ ቀን ወደፍልሚያው ሲገቡ ጥንካሬ አያንሳቸውም።

የእስራኤል ልጆች ወደ ግብፅ ሲወርዱ ከአንድ ቤተሰብ የሚበልጡ አልነበሩም። ከዓመታት በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር የለቀቁት ግን በሺዎች ነበር። በዚያ በቆዩባቸው ዘመናት ሁሉ መዋለዳቸው ቢታወቅም የበለጠ የበዙት ግን የግብፃውያኑ ጭቆና ሲበዛባቸው እንደነበር የዘፍጥረት መጽሐፍ ይነግረናል። አዎን በጭንቅ ቀን ከሰላሙ ዘመን ይልቅ ፍጥነት ጨምረው በዝተዋል። አሁንም በስደት ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ከሌላዋ ይልቅ ፍሬያማ መሆንዋን ስናይ ይኸው እውነት ፍንትው ብሎ ይበራልናል። በአንፃሩ ባለንበት ክፍለ ዘመን ከችግር ይልቅ ምቾት የሚገድለው ይበልጣል። በሥለጠኑት አገሮች እንደምናየው ሚሊዮኖችን ወደ ከርሰ መቃብር የሚያግዙት እንደ ከፍተኛ የደም ግፊት የስኳር ሕመምና ከፍተኛ የደም ስብ በአብዛኛው ከምግብ ብዛት የሚመጡ ናቸው። ምቾት ሰውን ደስ አሰኝቶ

ዕድሜውን ሊያረዝምለት ሲገባው ገዳይ ሆኗል። ግን ከላይ እንዳልነው መከራ ሰውን የበለጠ ያጠነክረዋል እንጂ በቀላሉ አይገድለውም።

በተናወጠ ጉዞ ላይ እንቅልፍ ይጣፍጣል ቢባል ለአንዳንዶች ቀልድ ሊመስል ይችላል። እኔ ግን ትክክለኝነቱን ከራሴ የሕይወት ልምድ ልመሰክር እችላለሁ። የመርከቢቱ መነሣትና መውደቅ መኝታው ላይ ለተጋደመ መርከበኛ እሹሩሩ እንደምትል ሞግዚት ባለውለታ ነው። ለስላሳ ሙዚቃ የሚነበብ ወረቀት ወይም የጎን ለጎን ጭውውት ሳያስፈልግ ውዝዋዜው እንቅልፍን ጎትቶ ያመጣዋል። እንዲሁ ስለክርስቶስ መከራን የሚቀበሉ ሰዎች ዙሪያቸው ረብሻ ባያጣም ውስጣቸው ግን ሰላም ነው። ዕረፍትም ነው!

ማዕበሉ ለኔና ለባልደረቦቼ ባሕረኝነታችን ያስታውሰን ነበር። ጸጥ ባለ ባሕር ላይ መቅዘፍ ያሰለቻል! በተለይም ከሥራ ነፃ ስንሆን ግድየለሽነትና መዘናጋት እንዳይጎበኘን ነውጡ ባለውለታችን ነበር። በመርከብ ላይ በሦስት ቀለማት ማለትም አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ-ተከፍለን ነበር እምንሠራው። እያንዳንዱ ቡድን በውስጡ የምሕንድስና የኤሌክትሪክና የጉዞ ቁጥጥር ባለሙያዎችን ያቀፈ በመሆኑ መርከቢቱን የማነቃነቅ ብቃት ነበረው። እናም አንዱ ቡድን በግዳጅ ላይ ሲሆን ቀሪው ሁለቱ ዕረፍት ላይ ይቆያሉ። በዕረፍታችን ሰዓት የምናደርገውን የመምረጥ መብት ነበረን።

ስለዚህ እናነባለን፤ ቲቪ አናያለን፤ ራዲዮ እናደምጣለን፤ ተሰብስበን የባጥ የቆጡን እናወራለን፤ ዓሣ እናጠምዳለን፤ ወይም እናሸልባለን። እነዚያ ሰዓታት የሚናፈቁ ነበሩ። ሆኖም ከነዚህ የመዘናጋት ጊዜያት የሚገላግለንና ባሕረኝነታችንን የሚያስታውሰን ማዕበል ነበር። አሁንም መከራ የሚባለው ማዕበል እምነታችንን ያሳስበናል- “ እኔን እንዲህ ካደረጉኝ እናንተንማ” ብሏል ኢየሱስ መጪ ሕይወታችን ሲጠቁም።

ወደሌላ ነጥብ እንዝለቅ። በአብዛኛው ለሰዎች የሚራራ ሰው ራሱ በዚያ መከራ ውስጥ ያለፈ ነው። በአንድ ወቅት ቀምሶታልና አሁን ሌሎች በተራቸው ያሉበትን ችግር የሚገነዘብ ሰው ለጥያቄያቸው “የራስህ ጉዳይ” ወይም “እንደፍጥርጥርህ” ብሎ አይመልስም። ያለበለዚያ ከነርሱ በተለየ ዓለም እንደሚኖር ምላሹ ያሳብቅበታል።

በታሪክ ያነበብነው የንግሥቲቱ ልጅ የሠራችው ስሕተትም ከዚህ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው። በሥራ አጥነትና በኑሮ ውድነት የተማረሩት የከተማይቱ ነዋሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ጠርተውና ቤተ መንግሥቱን ከብበው “ዳቦ፤ ዳቦ” እያሉ ይጮኻሉ። ይህን በመስኮት አሾልቃ የተመለከተችውየንግሥቲቱ ልጅ ወደ እናቷ ተመልሳ “ ምንድነው እሚያስጮኻቸው? ዳቦ ከሌላቸው ለምን እንደኔ ኬክ አይበሉም?” አለች አሉ። የዚህች የዋህ ልጃገረድ መላ

በእርሷ አተያይ ትክክል ነው። አዎን ሰው ዳቦ ካጣ ለጊዜውም ቢሆን ኬክ በልቶ ሕይወቱን ሊያተርፍ ይችላል። ግን የቤተ መንግሥቷ ቅምጥል ያልተገነዘበችው አንድ እውነት ዳቦ መግዣ ከሌለ ኬክ ማግኘት ቅንጦት መሆኑን ነው። ግን መልካም አስተዳደርን እያጠናች የምታድግ የወደፊት መሪ ይህን እንዴት አታውቅም ቢባል ደግሞ መልሱ ቀላል ነው። ከዕለተ ልደቷ ጀምሮ ይህች ልጃገረድ ስለምትለብሰው ልብስም ሆነ ስለምትበላው ምግብ ተጨንቃ አታውቅም። ለተሰጣት የንጉሣዊ ቤተሰብ ማዕረግም የሠራችው ሥራ የለም። በማንኛውም ሰዓትና ሁኔታ የምትፈልገውን የማግኘት መብቷ ያለ ማመንታት የተጠበቀ ነው። መሥራት እየፈለጉ ወይም እየቻሉ ሥራ መፍታት ወይም ቅንጦቱ ቀርቶ ለመሠረታዊ ፍጆታዎች የመክፈል አቅም ማጣት ምን እንደሆኑ ምናልባት በጋዜጣ ላይ ካልሆነ በዓይኗ አይታቸው አታውቅም። በጥቅሉ ሰላማዊና ሰልፈኞቹና እርሷ በአምላክ አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ቢሆኑም እንኳ በአኗኗራቸው የሁለት ዓለም ሰዎች ናቸው። እናም በምንም መልኩ ችግራቸውን ተገንዝባ ልትራራላቸው አትችልም።

ለዚህም ነው ለሌሎች የሚራራ ሰው ሌሎቹ የሚያልፉበትን መከራ የቀመሰ ነው ማለታችን። ለምሳሌ በእምነቱ የተሰደደ ሰው በስደት ላይ ላሉት መሰሎቹ ይራራል። የጸሎት ርዕስ ቢሰጠውም በደስታና በብዙ ሽክም

ይጸልያል። የዕብራውያን መጽሐፍ ሊቀ ካህን ብሎ የሚያስተዋውቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የመራራቱ አንደኛው ምክንያት ከኃጢአት በቀር በሁሉ ነገር የተፈተነ ስለሆነ ነው ይለናል። በእምነታችን የሚደርስብን መከራ ይገባዋል። ይህንንም ስለሚያውቀው እንዘጋጅ ዘንድ አስቀድሞ ነግሮናል። የእርሱን ጌትነት ከማመናችን የተነሳ ማጣት፤ መራብና መታረዛችንን ይገነዘባል። በምድር ሳለ ሁሉንም ቀምሶአቸዋል። ሕመማችንን ይረዳል።በመለኮታዊ ዕውቀቱ ከመለየትም አልፎ የግርፋቱ እና የችንካሩ ያም ሳይበቃ በጦር የተወጋበቱ ቁስል ስቃይ ለርሱ አዲስ አይደለምና የሕመሙን መጠን ጠንቅቆ ያውቀዋል። በርግጥም ከኢየሱስ የተሻለ ርኅራኄን የተሞላ ሊቀ ካህን ሊኖር አይችልም!

5

ማዕበሉን ለማለፍ

ሀ) ራስን ማዘጋጀት

በዓለም ሳለን ከእምነት የተነሣ መከራ እንደሚኖርብን በግልጽ ተነግሮናል። ነገሩን የበለጠ ጉልህ የሚያደርገው ደግሞ የመረጃው ምንጭ ነው። ይህ ዜና በመላዕክት፤ በነቢያት ወይም በራዕይ የተገለጠ አይደለም። ክርስቶስ ራሱ ነው የተናገረው። የመከራው መንስዔ ልዩ ልዩ ሊሆን ቢችልም መኖሩ ግን የምናየውና የምንዳስሰውም ነው። እኛም ራሳችን ቀምሰን በሌሎችም ላይ አይተን ለምደነዋል። ስለዚህ አገር ሰላም ብለን በተቀመጥንበት ያልታሰበ ችግር በድንገት መምጣቱ ሊያስደንቀን አይገባም። ይልቁንም የኛ ኃላፊነት በተቻለን መጠንና በሁሉም መስክ ምላሾችን ዝግጁ ማድረግ ነው። ይህም ስለ ተስፋችን ለሚጠይቁን አመርቂ ምላሽ ለመስጠት ከምናደርገው ዝግጅት ይጀምራል። አለን ስለምንለው የዘለዓለም ሕይወት ሰዎች ቢጠይቁን ምላሽ እንዳናጣ ያንንም በትጎትናና በአክብሮት እንድናደርገው የእግዚአብሔር ቃል በአንደኛ ጴጥሮስ ሦስተኛው ምዕራፍና አስራ አምስተኛው ቁጥር ላይ በግልጽ ይነግረናል።

ቀጥሎ የተመለከተው የትንሹ ልጅ ታሪክ ለዚህ ጥሩ አስረጂ ይሆናል። የተሰጠውን የማስተማር ሥልጣን በመጠምዘዝ በእግዚአብሔር እናምናለን የሚሉ ተማሪዎቹን

ዕለት ተዕለት የሚያንጓጥጥ አንድ እምነት የለሽ መምህር ነበር። አንድ ቀን እንደለመደው ሁለተኛ ክፍሎችን ሲያስተምር ቆየና አምላክ የለም የሚለውን ፍልስፍናውን እያራገበ በሕልውናው በሚያምኑት ላይ ሊያላግጥ ተነሣ። ግን አልቀናውም። እንደሌላው ጊዜ የሚበቃውን ያህል ተሳልቆ ከመጨረሱ በፊት ተግዳሮት ገጠመው። እናም በእምነቱ ብርቱ ከሆነ የሰባት ዓመት ልጅ ጋር ተጋጠመ። እንዳይናገር ገድቦ የሚበቃውን ያህል ካሾፈበትና ለጓደኞቹም መሳቂያ ካደረገው በኋላ አንድ ጥያቄ አቀረበለት።

“ ለመሆኑ እግዚአብሔርን አይተኸዋል?”

“ አላየሁትም”

“ ታዲያ ሳታየው እንዴት አለ ትለኛለህ?”

“ ለማመን ማየት አያሻኝም”

“ ካላየኸው መኖሩን እንዴት አወቅህ?”

“ መኖሩን ለማወቅም ማየት የግድ አይሆንም”

“ በል አምላክህን አሳየኝ፤ያለበለዚያ ሁለተኛ...”

“ እሺ አሳይዎታለሁ!”

“ የታል?”

“ እንውጣና ላሳይዎ”

“ ፀሐይቱን ያዩኢታል?”

“ አዎ...ታዲያ...የታል?”

“ ፀሐይቱን ትክ ብለው ይመልከቷት”

“ አልችልም፤ ዐይኔ ይጥፋ እንዴ?”

“ግድየለም ይዩአት፤ እዚያ ነው ያለው”

“አልችልም”

“ ታዲያ ፍጥረትን አተኩረው ለማየት ከተቸገሩ እንዴት ፈጣሪን ያያሉ?”

አንድ ወታደር በመጪው ዘመን ምን እንደሚጠብቀው የሚያውቀው የዕለቱን ዜና እየተከታተለ ውይም ጋዜጣ እያነበበ አይደለም። በማሠልጠኛው ጣቢያ ሳለ ከአሠልጣኞቹ ወይም ተጓዳኝ ሥራ ከሚያከናውኑ የማዕከሉ ሠራተኞች የሰማውን እያሰላሰለም አይደለም። ይልቁንም ገና ለአገልግሎት ከመመዝገቡ በፊት ውትድርና ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ካላወቀም እንዲያውቀው ተደርጓል። በክፉው ቀን በፊተኛው ረድፍ ላይ ተሰልፎ እንደሚዋጋ በሰላሙ ጊዜ ደግሞ ፀጥታን እንደሚያስከብር ለበጎ ሥራም እንደሚተባበር እግረ መንገዱንም ለመጪው ውጊያ ራሱን እንደሚያዘጋጅ በቂ ዕውቀት አለው። ቀጣሪዎቹም ቢሆኑ “ ዓለምን ትዞራለህ፤ የወጣትነት ዕድሜህን በደስታና ተድላ ትፈጽማለህ” የሚል ዓይነት

የማይጨበጥ ተስፋ አያዘግኑትም። ያለበለዚያ ውጤታማና ታሪክ ሠሪ ወታደር ሊኖራቸው አይችልም።

በመርከበኝነቴ ዘመን ይህንን ታሪክ ሰምቻለሁ። በመርከብ ዓለምን ለመዞር የጓጓ አንድ ወጣት ወደ ባሕር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ብቅ ይልና በአባልነት ይመዘገባል። ገና ሲገባ ያየው " ባሕሩን ለማየት ባሕር ኃይልን ተቀላቀል" የሚል መፈክርም ይሁን ውስጥ ካሉ ባሕረኞች የሰማው ካሰበው የሚቃረን አልነበረም። ወደማዕከሉ ገብቶ በሥልጠና ላይ እያለ ግን በጣም ግር ይለው ጀመር። መርከበኛ ከማለት ይልቅ ራሱን ወታደር ብሎ እንዲጠራ ዓለምን ከመዞር የቁም ቅዠቱ ታቅቦ አባቶች ያቆዩትን የአገሩን የባሕር በር እንዲያስከብር በተደጋጋሚ ይነገረዋል። ይህኔ ይህ ወጣት አንድ ማለዳ ከመኝታው ሲነቃ ቁርጠኛ ውሳኔ አደረገ። በዚህም መሠረት ሥልጠናውን አቆመ። " የምታደርጉትን አድርጉኝ እንጂ በዚሁ አልቀጥልም" አለ። አለቆቹ በሁኔታው እየሳቁና እየተናደዱ ወደ ዘብጥያ ወረወሩት። "ትንሽ ቅመሳትና አልቅሰህ ትመለሳለህ" እያሉ ቀለዱበት። እርሱ ግን በውሳኔው ጸና። በወታደራዊ እሥር ቤት ቆይታው አሳቡን እንዳልቀየረ የተረዱት አለቆቹ በመጨረሻ በአገር መከዳትና ሠራዊቱን በማሳመፅ ወንጀል ክስ ፍርድ ቤት አቀረቡት። ጉዳዩን የተመለከቱት ዳኛ ግን በቂ መረጃ እስካልተሰጠው ድረስ ይህ ወጣት ጥፋተኛ አይደለም ወደሚል ድምዳሜ

ደረሱ። ውሳኔአቸውን አሰምተው ከሠራዊቱ ሲያሰናብቱትም እንዲህ ብለው መከሩት። “ ገና ልጅ ነህ፤ ምርጫ ስታደርግ ቆም ብለህ አስብ፤ ኃይል የሚል ነገር ካየህ ወደ ኋላ አፈግፍግ፤ ባሕር ኃይል፤ አየር ኃይል....”። እርሱም ስለ መልካም ፍርዳቸው አመስግኖና የሚከተለውን ተናግሮ ተሰናበታቸው። “ ክቡር ዳኛ በኔ ይሁንብዎ፤ እንዲህ ዓይነት ስሕተት አይደገመኝም፤ እንኳን አየር ኃይል መብራት ኃይልም አልቀጠርም።” ይህ ወጣት ውሳኔውን ለመቀየር የተቸገረውም ይሁን አላስፈላጊ ዋጋ የከፈለው ራሱን ባለማዘጋጀቱ ነው። ራሱን ያለማዘጋጀቱ ዓይነተኛ ምክንያት ደግሞ ትክክለኛ መረጃ ያለማግኘቱ ነው ማለት ይቻላል።

በነገራችን ላይ ይህ ዓይነቱ ገጠመኝ በሥራ መስክ ላይ ብቻ የሚፈጠር አይደለም። ለብዙ ዓመት የተጸለየበትና መንግሥተ ሰማይን በምድር ሊለማመዱ የጓጉለት ትዳር “ምነው በቀረብኝ” የሚያሰኝ ሊሆን ይችላል። ተበድረውና ተለቅተው የሄዱበት የውጭ አገር “ በቃ ይኸው ነው?” የሚያስብል የሚሆነበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። ለዓመታት የደከሙበትን የትምህርት መስክ ወደጎን ትተው በአንድ ጀምበር ወደሌላ የሚታጠፉም ሞልተዋል። ስለዚህ አስቀድሞ መዘጋጀት የሁልጊዜ ልምምድ መሆን ይገባዋል። በተለይም ከእምነት ጋር ተያይዞ ለሚመጣ መከራ!

ለ) ቀድሞ መጸለይ

የረጅም ርቀት ሩጫ ቁንጮ የሆኑ አትሌቶችን በየመድረኩ አይተናል። በታላላቅ የአትሌቲክስ ውድድሮችም ይሁን በየአራት ዓመቱ በሚካሄደው ኦሊምፒክ የአገራቸው ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲውለብለብ መጋደላቸው ለኛ ለተመልካቾች አዲስ አይደለም። ግን የእነዚህን ብርቅ አትሌቶች የዕለት ተዕለት ሕይወት ጠጋ ብለን ለማየት ዕድል የገጠመን ጥቂቶች ነን። አትሌቶቹ ካደጉበት መንደር ወይም ዕውቀት ከቀሰሙበት ትምህርት ቤት በሎጋ ቁመናቸው ተመርጠውና የስፖርት ትጥቅ ታድሏቸው ለውድድር የተላኩ አይደሉም። ይልቁንም ከመጀመሪያው የመንደር ሩጫ ጀምሮ ሁሉን ደረጃ በደረጃ እየሸነፉ ተመርጠውና ዓመታትን ቆጥረው ነው እዚያ የደረሱት። ምናልባትም መጀመሪያ ካሸነፉበት ውድድር መልስ ላባቸውን ለመለቃለቅ ወደ ምቹ መታጠቢያ አልወረዱም። ለመንደሩ ወደተተከለው የቧንቧ ውኃ ወይም በአቅራቢያቸው ወዳለው ወራጅ ወንዝ እንጂ። የመጀመሪያ የሩጫ ጫማቸውን ለዓመታት አልቀየሩ ይሆናል። አንድ ውድድር ላይ ስላልቀናቸው "ወደ እረኝነትህ ብትመለስ ይሻልሃል" ዓይነት ቅስም ሰባሪ አስተያየት ሰምተውም ይሆናል። ግን በዚህ ሁሉ አልተበገሩም። ያ ሁሉ ከታለፈም በኋላ የወርቁን ሜዳሊያ ከማጥለቃቸው በፊት ለሰዓታት ቀናት ወራትና ዓመታት ላባቸውን እያንጠፈጠፉ

ጠንክረው ተለማምደዋል። የልምምዱን ሜዳ ምን ያህል ጊዜ ዞረውታል ብለን ብንጠይቅ ስሌቱ ናላ ያዞራል። ወጣ ብለው የሚለማመዱበት መሬት ደግሞ እንደ ሩጫው ሜዳ ምቹ አይደለም። አባጣ ጎርባጣ ጉድባና ገደል ሞልቶታል። እሾህና ቆንጥር አለው። ጨጎጊትም አያጣም። በጭቃና በኮሮኮንች ላይ አበክረው ይሮጣሉ። በአጠቃላይ በልምምድ ላይ ምቾት አይጠበቅም። ምቾት እሚመጣው ከድል በኋላ ነውና።

ገበሬው መከሩን መሰብሰቡ አውነት ቢሆንም ከዚያ ቀደም ብሎ ግን ያከናወናቸው አድካሚ ተግባሮች አሉ። መሬቱን መንጥሮና አለስልሶ ለዘር አዘጋጅቷል። ከዘር በኋላ ደግሞ በአረምና በጉልጓሎ ላቡን አፍስሶአል። ሰብሉን ከሰማይ ወፎችና ከአጥፊ እንሰሳት ጠብቆአል። አጭዶ ከምሮአል። በውቂያው ደግሞ ምርቱን ከግርዱ ለይቶአል። ይህንን ሁሉ አልፎ እንጂ በድንገት ተነስቶ ምርቱን አላፈሰም። የሚያምን ሰው ደግሞ እንዲሁ በረከቱን ከማፈሱ በፊት እንዲሁ ለሰዓታት ቀናት ወራትና ዓመታት በጾምና ጸሎት መትጋት ይኖርበታል።

አንዲት ልጃገረድ ለጨዋታ ወደ ጓደኞቿ ቤት ሄዳ ነበር። ግን ሳይታወቃትና ሳታስበው ስለመሸ በጨለማ ብቻዋን ወደ መኖሪያዋ መመለስ ነበረባት። ቤትዋ ብዙም ስለማይርቅ ደግሞም መንደሯ ትንሽ ስለሆነች በጉዞዋ ምንም ስጋት አልነበራትም። ሆኖም በሰላም ቤቷ እንዲያገባትና

ከከፉም እንዲጠብቃት ወደ አምላኳ ጸለየች። ከዚያም ቀጥታውን መንገድ ትታ በአቋራጭ መራመድ ጀመረች። ግን ብዙም ሳትርቅ ነበር ጨለማውን ተገን አድርጎና ሰው የሚጠብቅ መስሎ የቆመ አንድ ሰው የተመለከተችው። ይህ ሰለቀፈፋት እንደገና በጥበቃው ይከልላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች። ወዲያውኑም ውስጧ በሚያጽናና ሰላምና ጸጥታ ተሞላ። አብሮአት የሚሄድ ሰው ያለ መስሎም ተሰማት። አቋራጩን መንገድ ጨርሳ በሰውየውም አጠገብ አልፋ በሰላም ወደ ቤትዋ ደረሰች።

በሚቀጥለው ቀን ግን አንዲት ልጃገረድ በዚያ አቋራጭ መንገድ ላይና በዚያው ምሽት የመደፈሯን ዜና አንድ ጋዜጣ ለገፀ ንባብ አበቃ። ወንጀሉ የተፈጸመው ደግሞ ይህች ልጃገረድ በመንገዱ ካለፈች በኋላ በሃያ ደቂቃ ልዩነት ነበር። በዚህ ዜና እጅግ አዝናና በርሷ ላይም ሊደርስ ይችል እንደነበር አስባ እጅግ አለቀሰች። ያዳናትን እግዚአብሔርን አመስግና ስታበቃ የወንጀሉ ሰለባ የሆነችውን ሌላ ልጃገረድ የምትረዳበት መንገድ ካለ ለማጠያየቅ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደች። ታሪኳንም ለፖሊሶቹ ዘርዝራ ነገረቻቸው። ይህኔ ከፖሊሶቹ መካከል አንዱ ወንጀለኛውን እንዳየችው ካረጋገጠ በኋላ ከተጠርጣሪዎች መካከል አስገድዶ ደፋሪውን ለመለየት እንድትረዳቸው ጠየቃት። እርስዋም ያለምንም ማቅማማት ተስማማች። ከቀረቡላት ምስሎች መካከል ሰውየውን

ለመለየት ብዙም ጊዜ አልወሰደባትም። ግለሰቡም ይህንን ሲሰማ ወዲያውኑ ወንጀሉን ተናዘዘ። የፖሊስ መኮንኑ ይህችን ብርቱ ልጃገረድ ካመሰገናት በኋላ ከነርሱ የምትፈልገው ነገር ካለ በማለት ጠየቃት። እርሷም ምንም እንደማትፈልግ ግን ለግለሰቡ አንድ ጥያቄ እንዲያቀርቡላት ብቻ ተማጸነች። ለምን እርስዋን አልፎ ሌላይቱን እንዳጠቃ ለማወቅ በጣም ጓጉታ ነበር። አስገድዶ ደፋሪውም ከፖሊሱ የቀረበለትን ጥያቄ እንደሚከተለው መለሰ። “ እርስዋን ያልተተናኮልኳት ብቻዋን ስላልነበረች ነው። በሁለት ረጃጅም ሰዎች ግራና ቀኝ ታጅባ ነበር የምትጓዘው!”።

ያለጸሎት ምጥ የተወለደ ታላቅ በረከት የለም። በርካታና ዐበይት ታሪካዊ ክንውኖች የመጡት የምልጃ ጸሎቶችን ተከትለው ነው። የማይነቃነቅ ምሳሌ እነሆ። ለሰው ሁሉ መድኃኒት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የጠፉትን ይፈልግ ዘንድ ከሰማያት ወረደ። በቤተልሔም ይሁዳ በቤተ መንግሥት ሳይሆን በከብቶች በረት ተወለደ። በምድራችን በሺሕ ዘመናት ከተነገሩ ታላላቅ ዜናዎች ሁሉ ግንባር ቀደሙ በዚህ ቀን የተለፈፈው መሆን አለበት። ተያይዞ ብሥራቱም የሚያደምቅ ወሬም ነበረበት። ይኸውም ድንግሊቱ ያለወንድ ጸንሳ ወንድ ልጅ የመውለዷ ተአምር ነው። ለምን ቢሉ እንደዚያ ዓይነት ነገር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ተፈጥሮ አያውቅም። ከዚያም በኋላ አልተፈጠረም። ዜናውን

ያበሠረው መልአክም ‘‘ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታና የምሥራች ’’ ብሎታል። ልብ የምንለው ዋነኛ ነጥብ ግን የሚከተለው ነው። ይህ ከዘመናት በፊት የታቀደ ከአዳም ጀምሮ ለብዙዎች የተሰጠ ተስፋ ተደጋግሞ የተነገረ መልካም ዜና ቢሆንም እንኳ ያልምልጃ ግን በዚያ ጊዜና ወቅት ወደ ምድር አልወረደም።

ይህን እንዴት እናውቃለን?

መጽሐፍ ቅዱስ ጥቂቱን ይነግረናል። ጥቂቱን የምንለው ደግሞ ሁሉም ነገር ስላልተጻፈ ነው። ይህን ለማብራራት ማርያምና ዮሴፍ ኢየሱስን ወደቤተ መቅደስ በወሰዱት ጊዜ በዚያ ስለተቀበሉት አገልጋዮች ማንነት ጥቂት ማለት ይኖርብናል። የመጀመሪያው ስምዖን ነው። ስለዚህ ሰው ቢያንስ ሦስት ነገሮች በዚያው ምዕራፍ በግልጽ ተነግረውናል። በመጀመሪያ ለእስራኤል የሚመጣውን መጽናናት በተስፋ ይጠባበቅ ነበረ፤ በሁለተኛ ደረጃ ጻድቅና ትጉህ ሰው ነበር። በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ የሚጠቀምበት ድምፁንም እሚሰማ እንደነበረ አናውቃለን። ከዚያም የተነሣ ጌታ የቀባውን (ማለትም ኢየሱስን) ሳያይ እንደማይሞት በመንፈስ የተነገረው ሰው እንደነበር ተጽፎልናል። ይባስ ብሎ ደግሞ የዚያች ቀን እንኳ ወደ ቤተ መቅደሱ ለአገልግሎት የመጣው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንጂ በልማድ ወይም እግሩ እንደመራው አልነበረም።

ኢየሱስን ከእናቱ ተቀብሎ ካቀፈው በኋላ ድምፁን ከፍ አድርጎ እግዚአብሔርን ማመስገኑም ለዚህ ነው። ከዚያው አስከትሎም እግዚአብሔርን “ አሁን እንደ ቃልህ ልታሰናብተኝ ትችላለህ፤ ምክንያቱም ለዓለሙ ሁሉ ያዘጋጀኸውን መድኃኒት በጥንድ ዓይኖቼ ተመልክቻለሁ “ በማለት ለምኖታል። በማጠቃለያውም ከእግዚአብሔር ሰምቶ ወደፊት ወደሕይወቷ ስለሚመጣው መከራ ለማርያም ትንቢት ተናግሯታል።

ሌላዋ አገልጋይ ደግሞ ከአሼር ወገን የተወለደችው ነቢይቱ ሐና ነች። የሰማንያ አራት ዓመት ባልቴት ብትሆንም በሰው መለኪያ እጅግ ብታረጅም እንኳ ማገልገልዋን አላቋረጠችም። መጽሐፉ እንደሚነግረን መጾምና መጸለይዋ እንዳለ ሆኖ የምታገለግለው ደግሞ ሌትና ቀን ነበር። ኢየሱስ ወደ ቤተመቅደስ በተወሰደበት በዚያ ሰዓትም በሥፍራዋ ነበረች። ቀርባ እግዚአብሔርን ያመሰገነችውም ለዚሁ ነው። በዚያም ሳትወሰን የመሢሑን መምጣት ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር። እንግዲህ ሁለቱም (ስምዖንና ሐና) በዕድሜ የገፉ አረጋውያን ሁለቱም ነቢያት ሁለቱም የመቅደሱ አገልጋዮች ነበሩ። ከምንም ይልቅ ግን የጸሎት ሰዎች እንደነበሩ ቅዱስ መጽሓፍ ይነግረናል። አነዚህና ሌሎችም ነበሩ በምልጃቸው ይህንን ቀን ያፋጠኑት።

በሁለተኛው ማዕበል ታሪክ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው በደቀመዛሙርቱ ጩኸት የተሳፈሩበት ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም ጀልባዎች ተርፈዋል። የጭንቅ ጸሎታችን ከቤታችን አልፎ ለሌሎችም መዳን ሊሆን እንደሚችል ማሰቡ በራሱ የበለጠ እንድንተጋ የሚያበረታታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ከሎጥ ጋር አምስት ወይም አስር ጻድቃን ቢኖሩ ሰዶምና ገሞራ ይተርፉ ነበር። በኢያሪኮ ምጥ ወቅት ያች ሴት ከሰላዮቹ ምሕረት በመለመኗ በራሷ ሳትወሰን ለቤተሰቦቿ ሁሉ መዳን ምክንያት ሆናለች።

አስቀድሞ ይልቁንም ተግቶ መጸለይ የድል ሁሉ ምንጭ ነው። ለውጊያውም ምሪት የሚገኘው ወደ ሠራዊት ጌታ በመጮኽ ነው። የጠላትን ፍላፃዎች ለመቁረጥ አስቀድሞ አቅጣጫቸውን መለየት የግድ ይላል። መለየቱ ደግሞ ያለጸሎት የማይታሰብ ነው። ኢየሱስ ከተኛበት የተነሣው ብሎም ማዕበልና ወጀቡን የገሠፀው ደቀመዛሙርቱ ስለቀሰቀሱት ነው። ቀርበው ባያንኳኩ ኖሮ የተአምራት በር ባልተከፈተም ነበር።ወታደራዊ ጠበብት እንደሚሉት በሰላሙ ጊዜ ብዙ ላብ ካፈሰሰን በጦርነት ጊዜ ብዙ ደም አይፈሰንም። የኛም ላብ መፍሰስ ካለበት ያ በጸሎት ሥፍራ ቢሆን በክፉው ቀን መቋቋም አይቸግረንም።

<u>ሐ) ድምፆችን መለየት</u>

በማንኛውም ጊዜ ወይም በየትኛውም ማዕበል ቢሆን ‘‘ወደ ማዶ እንሻገር’’ የሚለውን ድምፅ መለየት ብሎም ማስታወስ የግድ ይሆናል። ለምን ቢሉ ያ ድምፅ የተላከው ለመመሪያ ብቻ ሳይሆን በመሃሉ ለሚገጥመን እንቅፋት ማበረታቻ እንዲሆነንም ነው። ችግር ውስጥ ስንሆን ከግራና ቀኝ የሚመጣው ምክር ሊያሳስተን የሚለቀቀው መንፈሳዊ ድምፅ ብዙ ነው። አየሩን የሞላው ድምፅ ለጆሮ ያታክታል። ሁሉ ሰው ስለ ችግራችን ዐዋቂ ይሆናል። ነገር ግን ከየትም አቅጣጫ ቢሲነዘርም የትኛው ትክክለኛ እንደሆነ ለማወቅ ድምፆችን መለየት ያስፈልጋል። ግን ሁሉ መፍትኼ የሚመስል አሳብ ካመጡ ከዚያ መሃል እርግጠኛውን እንዴት መለየት ይቻላል? ለዚህ አንዱ መፍትኼ አስቀድሞ በሰላሙ ቀን የመሪያችንን ድምፅ መለማመድ ነው። ያለበለዚያ ሁሉ በተተራመሰበት የሚያዘው የሚጨበጠው በቸገረበት በጭንቅ ቀን ለመስማት ስንሞክር ይምታታብናል።

በመጨረሻው የምጥ ቀን ስንጠራው ጌታ መልአክ አይልክም። ራሱ ድምፁን ያሰማናል። ወይም ይመጣል። ሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ ወደ እሳቱ በተጣሉ ጊዜ የሆነው ይኼ ነው። ከውጭ ይመለከታቸው የነበረው ንጉሥ ራሱ’’ ወደእሳቱ የጣልነው ሦስት ሰዎችን ሆኖ ሳለ አሁን ግን የማየው አራት ሰዎችን ነው። እንግዳው ሰው ደግሞ የአማልክትን ልጅ ይመስላል’’ ሲል በመደነቅ ተናግሯል።

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ይህንን እንግዳ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለው ይስማማሉ። ችግሩ ግን እንዲህ ከተፍ ሲል ድምፁን ወይም እርሱነቱን ለመለየት ያለመቻላችን ጉዳይ ነው። ደቀ መዛሙርቱ “ እሰይ ጌታ መጣ!” ከማለት ይልቅ “ መንፈስ ነው” ብለው መሸበሩ ቀደማቸው።

ዳዊት ከጎልያድ ጋር ሊጋጠም ሲወጣ ከሁሉ ጎልተው የተሰሙት ሁለት ድምፆች ከቶውንም አበረታች አልነበሩም። የመጀመሪያውተስፋ አስቆራጭ ድምፅ የወጣው ከገዛ ቤተሰቡ ነው። ወንድሙ ኤልያብ የዳዊትን መምጣት ለርሱና ለሌሎቹ የያዘውንም ስንቅ ዐይቶ “እንኳን ደህና ደረስክ” አላለውም። ይልቁንም ተቆጣው፤ ተቃወመውም። በመጀመሪያ ለምን ወደዚያ ሥፍራ እንደመጣና በጎቹንስ የት እንደተዋቸው አበክሮ የጠየቀው ሲሆን ከዚያው ጋር አያይዞም “ ኩራተኛና ልበ ክፉ” ሲል በአደባባይ ዘልፎታል። ያንን እና ሌሎችንም አልፎ ወደ ንጉሡ በቀረበ ጊዜም የሚያበረታታ ቃል አላገኘም። ይልቁንም ንጉሡ ከሁሉ አስቀድሞ የዳዊት ዕድሜ ለእንዲህ ዓይነቱ ግዳጅ ያልደረሰ እንደሆነ አስታወሰው። ቀጥሎም ጎልያድ ምርጥ ጦረኛ መሆኑን ከልጅነቱም ጀምሮ በውጊያ ብቃቱ የተካነ መሆኑን አረዳው። በሌላ አነጋገር ንጉሡ ራሱ እንኳ ሳይታወቀው ሥፍራውን ለቅቆ ጎልያድ ለአርባ ቀናት በአደባባይ የሰበከውን በጉዳ እያብራራ ነበር። በመጨረሻም “ ጎልያድን ለመውጋት

ችሎታው የለህም’’ ሲል እቅጩን ነገረው። ዳዊት ግን ይህንን ሁሉ ሰምቶ አልተበገረም። ‘‘ቢቀርብኝ ይሻላል’’ ብሎ አላፈገፈገም። አልያም ‘‘ ምስክር በሁለት ወይም በሦስት ይጸናል’’ ብሎ ለሽሽት የሚሆን ጥቅስ አላዘጋጀም። ከምንም ይልቅ ድምፆቹ የመጡት ከታላቅ ወንድሙና ከርዕሠ ብሔሩ ነው ብሎ እርሱ ከሚያውቀው ድምፅ ጋር ሊያስተካክላቸው አልከጀለም። የሚገርመው ወደ ግጥሚያው ክልል ሲያመራ ጎልያድም የተቀበለው በእርግማን ነበር። ከርግማኑ አያይዞ ደግሞ ሥጋውን ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እንደሚሰጥ ተናገረው። አስቀድሞ ሊያስደነግጠው መሞከሩ ነው። እንግዲህ ይህ ብላቴና ምን ቀረው? የቤተሰቡን ድጋፍ አላገኘም። የአገሪቱ መሪም ቁርጠኛ ውሳኔውን በብዙ ማቅማማት ነው የተቀበለው። ደግሞ ለውጊያ ሲወጣ ተገዳዳሪው ሰደበው።ዓለም ሁሉ ፊቱን ያዞረበት ነው የሚመስል።

የሆኖ ሆኖ ዳዊት ይሰማው የነበረው ድምፅ ሌላ ነበር። ‘‘ አንበሳና ድብ እንድመታ የረዳኝ አምላኬ ዛሬም አብሮኝ ነው፤ ይህንን ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ አሳልፎ ይሰጠኛል፡ ጭንቅላቱን እቆርጣለሁ፤ የርሱን ብቻ ሳይሆን የሠራዊቱንም ራስ ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ፤ ያኔ ምድር ሁሉ በእስራኤል አምላክ መኖሩን ያውቃል!’’። በርግጥም አሸነፈ። የጎልያድን መውደቅ ያዩት

ወገኖቹ ሸሽተው ጠፉ። ዳዊት እንዳለውም የሠራዊታቸው ሬሳ ለአራዊት ቀለብ ሆነ።ዳዊት ይህንኑ ልምዱን ከነገሠ በኋላ እንኳ አልተወም። ለምሳሌም ምርኮውን ለማስመለስ ወደ ውጊያ ከመሄዱ በፊት ኤፉዱን እንዲያቀርብ ካህኑ አብያታርን አዝዟል። በዚያም እግዚአብሔርን አናግሮ ዘራፊዎቹን አማሌቃውያን ተከትሎ ቢሄድ እንደሚያገኛቸው የተወሰደበትንም እንደሚያስመልስ ካረጋገጠ በኋላ ነው ለውጊያ የሄደው። ደግሞም ተሳካለት። ይህን ድምፅ ከሌሎች ለይቶ እየሰማ ነው ሕይወቱ በድል አሸብርቆ የኖረው።

ኢዮሳፍጥም በተራው “ የእግዚአብሔርን ቃል የምናገኝበት ነቢይ የለምን?” ብሎአል። የሰው ሁሉ ጆሮ የሚያልፍ ውኃ ድምፅ ለመስማት ባቆበቆበበት በዚያ ፈታኝ ሰዓት የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚያሰማውን ሰው ፍለጋ ዐይኖቹን አነሣ። ነገሥታቱ ወደ ነቢዩ ኤልሣዕ የሄዱት ሞዓብን ሊገጥሙ ለጦርነት በሄዱበት ምድር የሚቀመስ ውኃ አጥተው በተቸገሩበት ጊዜ ነው። ለሰባት ቀናት ያለውኃ መጓዝ ከውጊያው በፊት የገጠማቸው ሌላ ውጊያ ነበር። እንዲያውም ዘመቻውን የጠራው የእስራኤል ንጉሥ ኢዮራም ይህንን በማጤን ከጠላቶቻቸው ሽንፈት እንደማያመልጡ በአግድመት ተናግሮ ነበር። በኢዮሳፍጥ ጠያቂነት ወደ ነቢዩ ማምራታቸው ግን የአካባቢው ገዢ ስለነበረ አይደለም። የአካባቢው የውኃ ኃላፊ ስለነበረም አይደለም። ነገር ግን

በሚገባቸው ቋንቋ የእግዚአብሔርን የውጊያ ዕቅድ የሚነግር ዐዋቂ ስለነበር ነው። አካሄዳቸው ስለሚጠላ ውኃ ከመጠየቅ ያልዘለለ ቢመስልም ነቢዩ ግን ከዚያም አልፎ እግዚአብሔር ሞዓባውያንን አሳልፎ እንደሚሰጣቸው አበሠራቸው። የተመሸጉትና ያማሩትን ከተሞች ሁሉ እንደሚመቱ የሚያፈሩትን ዛፎች አንድ በአንድ እንደሚቆርጡ የውኃውን ምንጮች በሙሉ እንደሚደፍኑና መልካሙን እርሻ ሁሉ በድንጋይ እንደሚያበላሹት በዝርዝር ነገራቸው።

ኢየሳፍጥ ድምፆችን የሚለይ ንጉሥ እንደነበር ቀጥሎ በአጭሩ የተመለከተው ታሪክ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። በወቅቱ የነበረው የእስራኤል ንጉሥ ሬማት ዘገለዓድን ከሶርያ ንጉሥ ለማስመለስ ሊዘምት ባሰበ ጊዜ ኢዮሳፍጥን እንዲረዳው ጠይቆት ነበር። ኢዮሳፍጥ እንደ ሞዓቡ ዘመቻ ሁሉ በዚህኛውም ሊተባበረው ፈቃደኝነቱን ገለጠ። ከዚያም አያይዞ እግዚአብሔር የሚለውን እንዲሰማ አሳሰበው። ንጉሡም ለጉዳዩ ፈጣን ምላሽ በመስጠት አራት መቶ ያህል ነቢያትን ሰብስቦ "ልሂድ ወይስ ልቅር" ብሏቸዋል። እነርሱም በአንድ ድምፅ እግዚአብሔር ያችን ምድር አሳልፎ እንደሚሰጠው በመግለጽ "ሒድ ይቅናህ" እያሉ ገፋፉት። እንዲያውም ሴዴቅያስ የተሰኘው ጮሌ የብረት ቀንዶች ሠርቶ "እግዚአብሔር እስኪጠፉ ድረስ በእነዚህ ቀንዶች ሶርያውያንን ትወጋለህ" ይላል ሲል ድራማዊ በሆነ አቀራረብ

ነግሮታል። ዛሬም የሴዴቅያስ ምልምሎች ሞልተዋል። ከኪሳቸው አውጥተው ለመናገር እማያፍሩና ራሳቸውን የጠሩ ነቢያት በፈሉበት ዘመን ነው እምንኖረው። ስለሆነም ‘‘እከሌ ትንቢት ይናገራል/ትናገራለች’’ ብቻ ሳይሆን ንግግሩ ከየት እንደተገኘም የማወቅ ግዴታ ይኖርብናል። ለዚያ ደግሞ ቃሉን የመሰለ እውነተኛ ቱምቢ አይገኝም።

ይህ ሁኔታ ለኢዮሳፍጥ አላማረውም። ሆይሆይታው ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ለመለየትም ጊዜ አልወሰደበትም። ስለዚህ ሌላ ነቢይ ይፈለግ ዘንድ አሳሰበ። በዚሁ መሠረት በብዙ ማንገራገር ከሚናገረው እውነት የተነሣ ንጉሡን አይወድም ተብሎ የሚታሰበው የይምላ ልጅ ሚክያስ ተጠርቶ መጣ። ሊጠራው የተላከው ሰውም ከብዙኃኑ ነቢያት ጋር በአሳብ እንዲስማማ ሊያግባባው ሞክሮአል። ግን ሚክያስ እንቢ አለ። ያንን በማስታወስም ይመስላል ገና እንደደረሰ ‘‘ሒድና ተከናወን’’ ብሎ በንጉሡ ላይ ያላገጠበት። ግን ወደ እውነቱ ሲመለስ ‘‘ሂድና ሙት፤ እነዚህ ሁሉ ነቢያት በሐሰተኛ መንፈስ የሚናገሩ ናቸው’’ ነው ያለው። ያ ነበር ትክክለኛው የእግዚአብሔር ድምፅ።

ዙሪያችን በድምፅ የተከበበ ቢሆንም ከዚያ መሃል ጎልተው የሚሰሙን ሦስት ድምፆች አሉ። የመጀመሪያው የብዙኃኑ ድምፅ ነው።ይህ ምናልባትም ከሌሎች ጎልቶ የሚሰማና የሚያምታታም ነው። መያዣና መጨበጫው

በሚጠፋበት የጭንቅ ቀን የመካሪ እጥረት አጋጥሞ አያውቅም። ሁሉም ከየአቅጣጫው የመሰለውን ይሰነዝራል። የራሱን ልምድ የተፈተነ አድርጎ በማቅረብ ይሸው ካልተደረገ ይላል። ሌላው ደግሞ ከዚያኛው ፈጽሞ የማይታረቅ አሳብ ይዞ ከተፍ ይላል። አንዱ በአካል ቀርቦ ምክር ቢጤ ሲሰነዝር ሌላው ሳያስፈቅድ ጣልቃ ይገባል። ሌላው ደግሞ ያንን አቋርጦ ስልክ ይደውላል። በድንገት ሁሉ ሰው ዐዋቂ ይሆናል። ያንዱ ዕቅድ ከአንዱ በአብዛኛው አይመሳሰልም። አንዱ ከሌላው የተሻለ አሳብ ማቅረቡን ለማስረገጥ አብሮ የሚያያይዘው ማለቂያ የለሽ ማብራሪያ ደግሞ ጊዜ ከማባከኑም በላይ ተቀባዩን የበለጠ ያደናግራል። ምናልባትም በአንዱ ምክር ላይ ተመርኩዞ እርምጃ የጀመረው ችግረኛ ከመሃል መንገድ የመመለስ አለበለዚያም ሌላውን ሰምቶ ወደግራ ወይም ወደቀኝ የመታጠፍ መከረኛ ዕጣ ሊጠብቀው ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ መካሪዎች ተራ ካለመጠበቃቸው የተነሳ አዳማጩ ከህምህምታ ያለፈ ጠብ የሚል ነገር አያገኝም።

ሁለተኛው የሥጋችን ድምፅ ነው። የዚህኛው አደገኝነት ደግሞ ከውስጥ የሚደመጥ ከመሆኑ ይመነጫል። ለምን ቢሉ አድማጩ ከመንፈስ ድምፅ ጋር ሊያመሳስለው ይችላልና። ድምፆችን የመለየት ክሕሎት የሌለው ማንም ሰው ያንን ይዞ “ እግዚአብሔር ተናግሮኛል!” ከማለት

አይመለስም። ይህ የጥቂቶች ችግር አይደለም። ወዳጄ ዶክተር ሞገስ ታደሠ "አብርሃም አባታችን ካልክ መመለሻ የለህም" የምትል አባባል ነበረችው። እንዲሁ ነው። አብዛኛው ሰው ያንን ይዞ "ጌታ ተናገረኝ" ካለ መመለሻ የለውም። ይህም በተራው ቢያንስ ሁለት አደጋዎችን ይዞ ብቅ ይላል። የመጀመሪያው ነገሩ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ውጤቱ ውድቀት ትርፉ ኪሣራ ሲሆን የሚፈጠረው ግራ መጋባት ነው። ግለሰቡ " አድርግ ያለኝን አድርጌ ሳለ ዉጤቱ እንዴት እንዲህ ይሆናል?" እያለ ከአምላኩ ጋር ሌላ ሙግት ሊፈጥር ነው። እንደገና ለሌላ ጊዜም የጠራው ድምፅ ሲመጣ ደግሞ " ከሥጋዬ እንዳይሆን" እያለ ሊያመነታ ነው። አልፎ ተርፎም "ባለፈው የሆነብኝ ይበቃል፤ አሳብህን አልስተውም" እያለ ደም ሥሩ እስኪገተር መቃወም ሊጀምር ነው። ሁለተኛው አደጋ ደግሞ ጠቃሚ የመውጫ አሳቦችን ላለመቀበል በሮችን መዝጋት ነው። አንድ ሰው መዳፉን እያሻሸ " እግዚአብሔር ተናግሮኛል!" ካለ በኋላ የወዳጆቹን ምክር ይሰማል ማለት ዘበት ነው። በዚያ ወቅት እርሱ በጥልቅ አምልኮ ውስጥ ሲሆን ወዳጆቹ ደግሞ ሚልኮሎች ናቸው። ያ ደግሞ በተራው ትልቅ ማባከን ይሆናል። እነዚያ ወዳጆቹ በዚህ ከማዘንም አልፈው ለወደፊትም " አይ እርሱ ምክሬን አይቀበልም" ሊሉና ጀርባቸውን ሊሰጡት ይችላሉ። ሰውየው

የማይከፈልበትን ትልቅ የጥበብ በር በራሱ ላይ ዘጋ ብንለው ይቀላል። በጥቅሉ የሥጋን ድምፅ ከመለኮት ድምፅ ጋር ማምታታት ትልቅ ኪሳራ ነው።

ሦስተኛና የመጨረሻው ደግሞ የክፉው ድምፅ ነው። አማራጭ አሳቦችን ይዞ ያውም ሳይጠየቅ ከተፍ ይላል። የሚያቀርባቸው ዕቅዶች የረቀቁና ጥበብ በሚመስል በሽታ የተለከፉ ስለሆኑ ብዙ የዋሃንን እንደጎርፍ ጠራርገው ይወስዳሉ። የክፉው አሳቦች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ ማስተዋል እንጂ የሮኬት ሳይንቲስት መሆን አያሻም። ቅዱሱ መጽሐፍ ‘‘ የክፉውን አሳብ አንስተውም’’ ሲል ግልጥ ባለ ቋንቋ ይናገራል።(2 ቆሮ. 2:11) ኢየሱስ ለአርባ ቀን በምድረ በዳ ከጦመና ከተራበ በኋላ ድንጋዮችን ወደ ዳቦ የመቀየርን ዕቅድ ይዞለት ከተፍ አለ። (ማቴ.4:2) ነገሩ በመንፈስ እስካልተፈተሸ ድረስ ኢየሱስ ጦሙን ስለጨረሰና ተአምራት የማድረግ ብቃትም ስላለው በቀላሉ ተግባራዊ ሊሆን ይችል ነበር። ኢየሱስ ግን ምክሩን በመለኮታዊ አእምሮና በመንፈስ ስለፈተሸው አልተቀበለውም። ይህን የተገነዘበው ሰይጣን ደግሞ ሌላ አማራጭ አሳብን አቀረበለት። ይህ ምንን ያስተምረናል ከተባለ ክፉው ለአንድ ችግር አንዲት መፍትኼ ብቻ ይዞ እንደማይመጣ ነው። በዚህ ረገድ ችግር የለበትም። አንዱ ተቀባይነት ሲያጣ በጀት ፍጥነት ሌላ አጀንዳ ያቀርባል። አንዱን በቤተሰብ ሌላውን በሐኪም ሌላውን

በሹማምንት አንደበት እያስቀመጠ ሙከራውን ይቀጥላል። ሃያ አሳቦችን አቅርቦ አንዱ ብቻ እንኳ ተቀባይነት ካገኘለት አንድ ለዜሮ አሸነፈ ማለት ነው። የሚፈልገውም ይህንኑ የማለፊያና የማሸነፊያ ነጥብ ብቻ ነበርና። አደገኛው የማምታቻ ዕቅዱ ደግሞ ከኢየሱስም ጋር ሳይቀር እንደሞከረው አሳቡን በእግዚአብሔር ቃል ለማስደገፍና ዕቅዱን ለማመናፈስ መሞከሩ ነው። በቃሉ ብስለት የሌለው ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት ያልመረመረ ማንም ግለሰብ ከዚህ መሰሉ ወጥመድ ለማምለጥ ይቸገራል።

እንግዲህ በጥቂቱ እንደዘረዘርነው ዙሪያችን በድምፆች ተከቦአል። ይህን ሁሉ ወደጎን በመተው የፈጣሪን ድምፅ መስማት ብዙ ልምድና ልምምድ ይጠይቃል። ኤልያስ በእግዚአብሔር ፊት በቆመ ጊዜ የተገለጠው አንድና ትልቁ የሕይወት ልምምዱ የእግዚአብሔርን መገኘትና ድምፅ መለየቱ ነው። መጀመሪያ ታላቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰንጥቋል። ዓለቶቹንም ብትንትናቸውን አውጥቷል። ሰባብሯልም። ከዚያም የምድር መናወጥ ሆኖአል። አስከትሎም እሳት ተነስቷል። የእግዚአብሔር ድምፅ በነፋሱ፤ በምድር መናወጡም ይሁን በእሳቱ ውስጥ አልመጣም። ከዚያ ሁሉ በኋላ ግን የዝምታ ድምፅ ሆነ። ወይም ለስለስ ያለ ድምፅ ተሰማ። ያኔ ኤልያስ ሰምቶ ፊቱን በመጎናጸፊያው ሸፍኖአል። ይህም የአክብሮትና ትኅትና ምልክት ሊሆን

ይችላል። ሰምቶም የእግዚአብሔርንም ጥያቄ መልሶአል።(1 ነገ. 19፡. 11-13)። በመሠረቱ ለማንም አንባቢ እግዚአብሔር በታላላቅ ድምፆች ራሱን እንደሚገልጽ ማሰቡ ቀላል ነው። ግን ቢያንስ በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደዚያ አልሆነም።

መ) የተሻለውን መምረጥ

በችግርና በመከራ ቀን ሁለት ነገሮች ከፊታችን ይደቀናሉ። የሚያስገመግመው ማዕበል ወይም ጸጥተኛው ኢየሱስ! ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊው ዓለም ከሁለት በላይ ምርጫ የለም። ገና ወደ አደባባዩ ብቅ ስንል የቀረበልን ምርጫ “ ሕይወት ወይም ሞት” የሚል ነበር። አዎ የወንጌል ስርጭት እኛ ዘንድ በደረሰ ጊዜ ይዞልን የመጣው ሁለት ታላላቅ ምርጫዎች እነርሱ ነበሩ። የብርሃን ወይም የጨለማው ልጆች እንጂ መሃል ሰፋሪ ፍጡራን እንደሌሉ ቅዱሱ መጽሐፍ ይነግረናል። በመጨረሻው ፍርድም ሰዎች እንደ እምነትና ሥራቸው በጎችና ፍየሎች ተብለው ተለይተዋል። መለየቱን ተከትሎ ደግሞ የዘላለምን ሕይወት ለማስቀጠል መንግሥተ ሰማይ እና ገሐነመ እሳት የተሰኙ ሁለት ሥፍራዎች ተዘጋጅተዋል። በምድር ሳለን ለሁለት ጌቶች ማለትም ለገንዘብና ለእግዚአብሔር በአንድ ጊዜ መገዛት እንደማንችል መምረጥም እንደሚኖርብን ተነግሮናል። ሙሴን የተካው ታላቁ መሪ ኢያሱም በአንድ ወቅት ለሕዝቡ ምርጫን ሰጥቷል። “የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፤ እኔና ቤተሰቤ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን” ብሏቸዋል። ሕይወት በሁለት ምርጫ የታጠረች ነው

የሚመስለው። ጤናና በሽታ፤ ብርሃንና ጨለማ፤ እውነትና ሐሰት እያልን ብዙ መዘርዘር እንችላለን።

በዚሁም መሠረት ወጀቡ ሲነሣ ከፊታችን የሚደቀኑት ሁለት አማራጮች ናቸው። ወጀቡ ወይም ኢየሱስ! ኢየሱስን ማየት ወደር የለሽ ምርጫ ነው። የሕይወት መንገድ በተናወጠ ቁጥር ፍርሃትና እምነት ብቅ ይላሉ። ፍርሃት "ኀልያድ ግዙፍ ነው፤ ይውጠኛል" ሲል እምነት ግን "ኀልያድ ግዙፍ ነው፤ ስለዚህ ወርውሬ አልስተውም" ብሎ ይጀግናል። በእምነት መጋፈጥ የእውነተኛ አማኝ መገለጫ ነው። ማዕበሉን ስናይ እንሰጥማለን። ኢየሱስን ስናይ ግን በማዕበሉ ላይ እንራመዳለን።

መጽሐፍ የሚነግረንም ሆነ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተንታኞች ስለ ጴጥሮስ የሚሉት ከዚህ የዘለለ አይደለም። ጴጥሮስ እጅን በማያሰጥ ፍጹም ቆራጥነት በሚያስደንቅም እምነት በውኃው ላይ መራመዱ እውነት ነው። ዓይኖቹን በኢየሱስ ላይ አድርጎ አስደናቂ የውኃ ላይ ጉዞውን ጀምሮአል። ግን የኋላ ኋላ ነፋሱን አይቶ እንደፈራ ብዙም ሳይቆይ መስጠም እንደጀመረና ለእርዳታ ወደጌታው እንደጮኸ ለትምህርታችን ተጽፎልናል። በአንድ ጊዜ ኢየሱስና ነፋሱን ማየት አይቻልም። "ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም" እንደሚለው አባባል መሆኑ ነው። ስለሆነም ዓይኖቹን ከኢየሱስ ላይ አንስቶ በነፋሱ ላይ

ተክሎ እንደነበር አንረዳለን። ነፋሱ ደግሞ ሊያደርግለት የሚችለው ብቸኛ ርዳታ የስምጠቱን ሂደት ማፋጠን ብቻ ነበር። ግን ጴጥሮስ በዚህ አላቆመም። ስለዚህም አልተሸነፈም። ቀደም ሲል በውኃ ላይ ያራመደው ጌታ አሁንም ከውኃ ውስጥ ሊያወጣው እንደሚችል ያምን ነበር። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የተረዳ ሰው ምንም እንደማይሳነውም አብሮ ማመን አለበት። ጴጥሮስ እንደዚያ ነበር።ስለሆነም የአድነኝ ጥሪውን ወደጌታው ጆሮ አደረሰ። ኢየሱስ ልመናውን ሰማ። እጁንም ዘርግቶ ጎትቶ አወጣው። በአንድ ክስተት ውስጥ ሁለት ተአምራት የተደረገለት ሰው ሆነ። ነጥብ መቁጠር ካለብን አንድ ጊዜ እምነት የጎደለው ቢመስልም እንኳ ሁለት ጊዜ እምነቱን ስላሳየ ጥርጥርን ሁለት ለአንድ እንደረታው ልንስማማ ይገባል። የቆጠርነው እንዲህ ነው። አንድ ጊዜ ንፋሱን በማየት መስጠም ጀመረ። አንድ ነጥብ ጣለ። ከዚያ በፊት ግን አዳኙ እንዳደረገው በውኃ ላይ መራመድ እንደሚችል አምኖ ነበርና አንድ ነጥብ ነበረው። ስለዚህ አንድ እኩል ሆኑ። ኋላ ላይ ደግሞ ኢየሱስ ከውኃው ሊያወጣው እንደሚችል በማመን ይህንኑ ጠይቋል።በዚህም ሌላ ነጥብ አስመዘገበና ጥርጥርን ሁለት ለአንድ ረታው። አሸነፈ! ስለዚህ ጴጥሮስ ቋሚ ምሳሌያችን ነው። ኢየሱስን መርጧል። ነፋሱን ማየቱ ድካሙ እንጂ ምርጫው

እንዳልነበረ ለሁሉ አሳይቷል። አዎን ኢየሱስን መርጧል። ትክክለኛውን መምረጥ ይሏል ይህ ነው።

በነገራችን ላይ ትክክለኛው ምርጫ እውነቱን ከመቀበል ይጀምራል። ዓለምን የሞላውን የክፉ ሕልውና ሽምጥጥ አድርጎ መካድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች አጋንንት ስላመጡት ችግር ሲጠየቁ ስለዚያ መወያየት ለአጋንንት ዕውቅና መስጠት ይመስላቸዋል። ይህ መልካምነት ባያጣም ለጠላት ዕውቅና አልሰጥም ማለቱ ግን ሁሌ ላያዋጣ ይችላል። የሰይጣንን መኖር ማወቅ የምርጫው የመጀመሪያ ክፍል ነው። ለምሳሌ በአጋንንት ተፅዕኖ ውስጥ የወደቀ ግለሰብ የነፃ ማውጣት ጸሎት ወደሚካሄድበት ቢታደም ትክክለኛ ምርጫ አደረገ እንጂ ለጠላት ዕውቅና ሰጠ ልንለው አይገባም። እንዲያውም በዚያ ርምጃው አጋንንትን ለሚያባርረው ጌታ ነው ዕውቅና የሰጠው። ብሄድ ነፃ ልወጣ እችላለሁ ብሎ ካሰበ የኢየሱስን ሥልጣን በመርኅ ደረጃ ተቀብሏል ማለት ነው። ያለበለዚያ ግለሰቡ በአደባባይ በል እንደተባለው “ ሟርትና ድግምት በእኔ ላይ አይሠራም” እያለ በጓዳው ግን ብዙ ስቃይ ሊደርስበት ነው። “ በዝሙት ተቸግሬአለሁና ጸልዩልኝ” ለሚል ሰው ከመጸለይ ይልቅ እንዴት “ለአጋንንት ዕውቅና አትስጥ” ማለት እንደምን ትክክል ሊሆን ይችላል?

እንዲያውም በጸሎት እንዲመቱ አሳልፎ በመስጠት ስለካዳቸው ማበረታታት ነው እንጂ።

ሠ) አመለካከታችንን መቀየር

አንድ ኑሮ ያማረረው ሰው ችግሩን ለማዋየት በአካባቢው ወዳለ ጥበበኛ ይሄዳል። እንዲህም ይለዋል።" አስቸኳይ እርዳታ እፈልጋለሁ። ያለበለዚያ ማበዴ ነው። እኔ፤ ባለቤቴ፤ ልጆቼና አማቾቼ በአንዲት ክፍል ቤት ውስጥ ተጣበን ነው እምንኖረው። ምኞት አልባነቱን ልንቋቋመው አልቻልንም። ስንጨቃጨህ ነው የምንዉለው። ያች ክፍል ሲያል ሆናብናለች።"

"ችግርህ መፍትኼ አያጣም፤ ግን አድርግ የምልህን ሁሉ ለማድረግ ቃል ትገባለህ?"

"እንዴታ! እምላለሁ!"

"መልካም፤ ስንት የቤት እንሰሶች አሉህ?"

" አንዲት ላም፤ አንድ ፍየልና ስድስት ዶሮዎች"

" ከዛሬ ጀምሮ እነርሱም ከእናንተ ጋር ማደር ይጀምሩ፤ ከሳምንት በኋላ ታዲያ ተመልሰህ ና፤ ሁኔታውንም ንገረኝ"

ችግረኛው ሰው በዚህ ምክር ከመጽናናት ይልቅ ይበልጥ ግራ ተጋባ። ቢሆንም አንድ ጊዜ ተስማምቷልና የገባውን ቃል ለመጠበቅ ወሰነ። እናም እንሰሶቹን ማታ ማታ

እዚያችው ክፍል ውስጥ እያስገባ ማሳደር ጀመረ። እንደዓመት የረዘመበትን አንድ ሳምንት ከጨረሰ በኋላ ወደ ጥበበኛው ሲመለስ የበለጠ ነጭናጫ ሆኖ ነበር። መቀመጥም ሳያስፈልገው ገና እንደገባ እንዲህ አለው።

“ ችግሩ ጭራሽ ተባብሷል፤ መቋቋምም ተስኖኛል። ፍጉ፣ ግማቱና ጩኸቱ መጠን የለውም። ሁላችንም ልናብድ አንድ ሐሙስ ቀርቶናል!”

“በል አሁን ወደቤትህ ተመለስ፤ ከዛሬ በኋላ እንሰሶቹን ከቤትህ አስወጣቸው። እናም ነገ ብቅ በልና ያለውን ለውጥ አጫውተኝ”

ችግረኛው ሰው በፈጣን ሩጫ ወደ ቤቱ ሄደ። በሚቀጥለው ቀን ሲመለስ ዐይኖቹ በደስታ ያበሩ ነበር። ለጥበበኛውም ሲቃ በሚተናነቀው ድምፅ ይህን አበሠረው።

“ሕይወት እንዴት ትጣፍጣለች? እንሰሶቹ ወጥተዋል። ቤቱ ፀድቷል፤ ጸጥታ ሰፍኖአል፤ ለሁላችን በቂ ቦታ አለ!”

ከዚህ ችግረኛ ሰው ሕይወት የምንማረው የመጀመሪያ ነገር አመለካከቱ መቀየሩን ነው። በመሠረቱ ለጥበበኛው ያጫወተው ችግር አልተወገደም። አሁንም እርሱ ባለቤቱ ልጆቹና አማቾቹ በዚያችው አንዲት ክፍል ቤት ውስጥ ተጣበው ነው የሚኖሩት። ግን ምክሩን በሥራ ላይ በማዋል ችግሩን ከሌላ አቅጣጫ መመልከት በመቻሉ አመለካከቱን ቀየረ። የባሰም አለና አገርን አለመልቀቅ ይበጃል

ወደሚል የሚያዛልቅ ድምዳሜ ደረሰ። ምናልባትም እሱ ከሚኖርበት ሁኔታ በባሰ አካኋን የሚኖሩ መኖራቸውን ሳያያቸው ተረዳ።

እንዲያውም ይህ ታሪክ ጫማ ፍለጋ ከጸለየው ሌላ ችግረኛ ሰው ጋር ጥቂት ተመሳሳይነት አያጣም። በባዶ እግሩ መሄድ የሰለቸው ይኸው ሰው አምላክ በጫማ እንዲባርከው አብዝቶ ይጸልይ ነበር። ግን ጸሎቱ እንደ እርሱ ፍላጎት ፈጥኖ አልተመለሰም። በዚያ መማረሩ ታክሎበት በአንድ ማለዳ ለረጅም ጊዜ ሲጸልይና ሲያሳስብ ይቆያል። ንዝንዙን ጨርሶ ከቤት ሲወጣ መጀመሪያ ያጋጠመው ሰው ግን እግር አልባ ነበር። እርሱም ጊዜ ሳያጠፋ ተመልሶ ተንበረከከና እንዲህ አለ። ’’ የቅድሙን ጸሎቴን እርሳው ጌታ ሆይ፤ ጫማ ባይኖረኝም ሁለት እግሮች አሉኝ። ስለነዚህ እግሮቼ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ።’’

አመለካከታችንን ለመቀየር ከሚረዱ ነገሮች ዋነኛው ሁኔታዎች ከሚሉት ይልቅ ቃሉ የሚለውን ማመን ነው። የምንሰማውና የምናየው የሚምታታበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። ለምሳሌ በስደት መከራችንን በልተን መቀመጫ ፍለጋ ከአገር አገር ስንከራተት በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል እንበል። በዚህ ተወጥረን መላወሻ አጥተን ሳለ ቃሉ ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር እንደሆኑ ይነግረናል። ታዲያ የመሬቱ ባለቤት የኛ አምላክ ከሆነ እንዴት ነው ሣር ቅጠሉ

የሚያባርረን? እንዴትስ ነው የመኖሪያ ፍቃድ ለምትባለው ብጣሽ ወረቀት ደጅ ጥናት የበዛብን? ግራ እሚያጋባ ነገር ነው።ሐኪሙ አንገቱን እየነቀነቀ “ አዝናለሁ፤ የምርመራው ውጤት እንዲህ የሚባል በሽታ እንዳለብህ ያሳያል!” ባለን ሰሞን በሐዛን ተኮራምተናል። መጽሐፍ ቅዱስ በበኩሉ “ የግብፅን በሽታ አላመጣብህም” የሚለውን አጉልቶ ያሳየናል። ታዲያ ይህ በሽታ ከየት መጣ? እጃችን አጥሮ መሠረታዊ ፍላጎቶቻችንን እንኳ የምንሸፍንበት ሳንቲም ከኪሳችን ሲታጣ ሌላው ሰው እንዴት እንደሚኖር ለማየት አንገታችንን አስግገናል።የማይሻረው ሕገ እግዚአብሔር ደግሞ ራስ እንጂ ጅራት እንደማንሆን ገንዘብንም ቢሆን አበዳሪ እንጂ ተበዳሪ ልንሆን እንዳልተጠራን ያመለክተናል። ታዲያ እንኳን ልናበድር ለራሳችን እሚሆነውስ ብር የታለ? ቤተሰዎቻችን ስለ እምነታችን ሲያገልሉን እንኳን የኛን ምስክርነት ሊሰሙ ይቅርና አብረውን ማዕድ መቀመጥ ሲያስጠላቸው እያየን ነው። መንፈሳችን ግን “እመን ፤ አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ” የሚለውን ጥቅስ ሲያወጣና ሲያወርድ ይውላል። ያንን አጢነን እውን እነዚህ ይድናሉ የሚል ግርታ ይከበናል።በጥቅሉ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ነው ሁኔታዎች የሚሉትና ቃሉ የሚለው አልጣጣም የሚሉት። ግን ብዙዎች ያተረፉት ቃሉን የሙጥኝ በማለት ነው።

ለጌዴዎን ሁኔታዎች የነገሩት እንደሚከተለው ነበር። ምድያማውያን ኃያላን ናቸው።በእነርሱ ዕይታ ውስጥ ገብቶ እህል መውቃት በራስ ላይ አደጋ መጋበዝ ነው። ስለዚህ ጉድጓድ ቢጤ ፈልጎ ውቂያውን ማካሄድ እሷኑ እየበሉም መሰንበት ብልህነት ነው። ሁሉን ቻዩ ያለው ደግሞ የዚህን ተቃራኒ ነበር። የእግዚአብሔርን መልዕክት እንዳመጣው መልአክ ከሆነ ጌዴዎን በአምላኩ ዐይን ‘‘ጽኑና ኃያል ሰው’’ ነው። ያም ብቻ አይደለም። ራሱ እግዚአብሔር ከጌዴዎን ጋር ነው። ይህ ለጌዴዎን እጅግ ግራ የሚያጋባ ነገር ነበር። ስለሆነም ‘‘ የደረሰብን ነገር ብዛት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አለመሆኑን በግልጽ ያሳያል፤ በርግጥ አባቶቻችንን በብዙ ተአምራት ከግብፅ እንዳወጣቸው ሰምተናል። ግን እኛ ያየነው ነገር የለም። ያየነው ነገር ካለ በምድያማውያን እጅ ላይ መውደቃችንን ነው’’ ሲል ተከራከረ። እግዚአብሔር ግን ከሚያየውና ከሚሰማው ይልቅ የርሱ አሳብና ዕቅድ እንደሚሻል ለማብራራት ‘‘ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ምድያምንም እንደ አንድ ሰው ትመታለህ’’ ብሎታል (መሳ.6:16)። እናም ጌዴዎን ነገሮችን ሁሉ ለማመዛዘን ጊዜ ወሰደ። የሰማውም ድምፅ እንዲጸናለት በምልክት ጭምር ፈተነ። በመደምደሚያውም ሁለተኛውን መረጠና አመለካከቱን ቀየረ። ባለድልም ሆነ!

አመለካከትን ለመቀየር ከሚረዱ ነጥቦች ሌላው ደግሞ የጉዞውን መመሪያ የሰጠው ማን እንደሆነ ማስታወስ ነው። በሌላ አነጋገር እንሻገር ያለው ማን እንደሆነ በእርግጠኝነት ማወቅ ነው። ይህ በተራው ኋላ " የእግዚአብሔር ፍቃድ ባይሆን ነው" ከሚል ማመንታትና ግራ መጋባት ያድናል። ደቀ መዛሙርቱ ርኅራኄ የለሽ በሆነው ኃይለኛ ንፋስና ማዕበል ቢንገላቱም በወጀቡ ፍዳቸውን ቢያዩም ለሰዓታት መከራቸውን ቢበሉም እንኳ ቢያንስ ትእዛዙ ከየት እንደወጣ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። ስለዚህ የሚችሉትን ያህል ከታገሉ በኋላ መምህሩን ለመቀስቀስ ድፍረት አላጡም።

ኮሽ ሲል ወየው ከማለት ድነን ወደማይቀርልን ፍልሚያ የምንገባው አመለካከታችን ከተቀየረ ብቻ ነው። ያኔ የጦር ድምፅ ሲሰማ እንደሚጎደፍረው ፈረስ ሙሉ ድፍረት ይኖረናል። መጡብንም ሄድንባቸውም ድሉ በኢየሱስ ስም የኛ ነው። በሥራዊቱ ላይ ጥቃት የተሰነዘረበት አንድ ቆፍጣና አዋጊ መኮንን እንዲህ አለ " አገኘናቸው!"። አመለካከታችን ከተቀየረ ክፉ መናፍስት አያገኙንም። እንሔድባቸዋለን። እነርሱው ከመጡም "አገኘናቸው!"

<u>ረ) ጠንክሮ መዋጋት</u>

ደቀ መዛሙርቱ በሁለቱም የባሕሩ ነውጦች ጊዜ ጠንክረው በመዋጋት ቁርጠኝነታቸውን አስመስክረዋል።

ስጋት የገባቸው እስከመጨረሻው እየታገሉ ሰዓቱ በገፋ ቁጥር ነፋሱ መቆም ማዕበሉም መቀነስ ሲገባው እያየለ በመምጣቱ ነው። በተለይ በሁለተኛው አጋጣሚ ደቀ መዛሙርቱ የሚቀዝፉት ከነፋሱ በተቃራኒ በመሆኑ መከራቸው በዝቶአል። በዚህ ዓይነቱ ጊዜ ወደኋላ መመለስ ወይም በዘመኑ ቋንቋ አብሮ መንፈስ እጅግ ቀላል ቢሆንም እነርሱ ግን የመምህራቸውን ትዕዛዝ በማክበር እንደንስር በብዙ ትግል ወደፊት ቀጥለዋል። እናም ከነርሱ እምንማረው ትልቁ ነገር ይህንኑ ነው። በችግሮች መካከል እንኳ ወደ ጥሪአችን መገሥገሥ ነው ያለብን። መመለስ ሌላውና ቀላሉ ምርጫ ነው። ቢሆንም ግን ጥሩ ምርጫ አይደለም።

ጌታ አብሮአቸው በነበረ ጊዜ እርሱን ከመቀስቀሳቸው በፊት ወደ ጀልባይቱ የሚገባውን ውኃ በማፈስና ሸራዎቹን በመወጠር ብዙ ደክመዋል። ከባሕረኝነት ልምዳቸው የመነጨ በሚመስል አኳኋን ምናልባት ማዕበሉ የሚያልፍ እንደሆነ በሚል ጥቂት ለማይባል ጊዜ ጨክነዋል። ስለሆነም ገና ባሕሩ ከመናወጡ አልቀሰቀሱትም። በመጨረሻም “ መምህር ሆይ፤ ስንጠፋ አይገድህምን?” ማለታቸው ማዕበሉ ከቁጥጥራቸው ውጭ መሄዱንና ጀልባዋም ለመገልበጥ እያንገራገረች መሆኑን ያመለክታል። በሌላው ተመሳሳይ ሁኔታም ቢሆን ባለ በሌለ ጉልበታቸው ራሳቸውንና ጀልባዋን ለማዳን ተፋልመዋል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ

ማብራሪያዎች እንደሚሉት ከሆነ ኢየሱስ እስኪደርስላቸው ድረስ ከ6-7 ሰዓታት በትግል ላይ ነበሩ። አዎን ደቀመዛሙርቱ በመጀመሪያ የሚችሉትን አድርገዋል። ጠንክረውም ተዋግተዋል።

የጠንካራ ተዋጊ አንዱ መለያ ፊት ለፊት መግጠም ነው። ጎረቤቶቹ ያልተመቹት ሰው ሠፈሩን አለቃው ያልተስማማው ደግሞ ሥራውን ይቀይራል። እፍ እፍ ያሉና ለያዥ ለገራዥ ያስቸገሩ ጓደኞሞች መግባባት ከቸገራቸው ላይተያዩ ይለያያሉ። መንገድ ላይ ሲተላለፉም እንኳን የልብ ወዳጆች የነበሩ ይቅርና ተያይተው እሚያውቁም አይመስሉም። ባለትዳሮች የተሻለ አማራጭ ከታያቸው ወይም ሦስቱ ጉልቻ ካንገፈገፋቸው የፍች ወረቀት ይፈርማሉ። ስለሚበተኑት ልጆች ስለሚታመሰው ቤተሰብ ደንታ አይሰጣቸውም። የአሳብ አለመጣጣም አላሠራ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሁለት ይከፈላሉ። በማግሥቱም የሰሉ ቃላትን መለዋወጥ ይጀምራሉ። ያለመታመን ያከሳው ወይም ትርፍ እንደ ሰማይ የራቀው የንግድ ሽርክና በንብረት ክፍፍል ይደመደማል። እንጀራውን ከዚያ ይቆርስ የነበረ ታማኝ ሠራተኛ የት ይወድቃል እሚለው ጉዳይ ባለሃብቶቹን ፈጽሞ አያሳስባቸውም። አገሮች እንኳ ብለው ብለው ሲሰለቻቸው ዳግም ላለመዋጋት ድንበር ይካለላሉ።

በገሃዱ ዓለም እንዳለው አማራጭ ግን መንፈሳዊውን ችግር በአቋራጭ ማለፍም ሆነ መሸወድ አይቻልም። ግብግቡ ፊት ለፊት ነው። በጎንዮሽ የሞከሩም አልተሳካላቸውም። እንዲያውም ያመለጡት መስሎአቸው ችግሩን ያባባሱ ይበልጣሉ። ለዚህ የአስቄዋ ልጆች ጥሩ ምሳሌ ሳይሆኑን አይቀሩም። ከፊታቸው የቆመውን የኢጋንንት ሠራዊት "ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም" ለማባረር ታሪካዊ ሙከራ አድርገዋል። አባታቸው የካህናቱ አለቃ ስለነበረ ኢጋንንት በሰዎች ሕይወት ላይ ስለሚያመጡት ጨለማ ጥሩ ግንዛቤና ዕውቀትም ነበራቸው ማለት ነው። ቢያንስ ይህ በራሱ ክፉ አልነበረም።ደግሞም በዘመኑ ከሚያገለግሉት ሰባኪያነ ወንጌል ውስጥ የጳውሎስን ግንባር ቀደምነት ተቀብለዋል። ያ ባይሆን የአባታቸውን ስም በጠሩ ነበር። ይኸኛውም ትንሽ ቅንነት በውስጡ አያጣም። አልፎ ተርፎም የከፉው ሥራ በኢየሱስ ስም እንደሚፈርስ አምነዋል። ከእምነት መንደር ብዙ የራቁ አልነበሩማ! የሳቱትና በነዚህ ምክንያቶች ሊተካ የማይችለው ሐቅ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሠረተ እምነት ባለቤት ያለመሆናቸው ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝና ጌታ አላወቁትም። የልጅነት ሥልጣን መቀበልና የካህናቱ አለቃ ልጆች መሆን ለየቅል መሆኑን በቅጡ አልተረዱም። ስለዚህ ኢጋንንቱ በቀላሉ አልተረቱላቸውም። እንዲያውም በሰላ አነጋገር ሊመልሱት

በማይችሉት ጥያቄ አፋጠጧቸው። ‘‘ጳውሎስን እናውቀዋለን፤ ኢየሱስንም እንዲሁ። እናንተ ግን እነማን ናችሁ?’’ የሚለው ጥያቄ ከአስቄዋ ልጆች አመርቂ ምላሽ ሊያገኝ የሚችል አልነበረም። ዐይናቸው ፈጠጠ። ነገሩም የበለጠ የከፋው ከዚያ በኋላ ነው። በጥያቄ አልቆመም። መልስ እንዳጡ ያጤኑት እና ጠጠር የወረወሩባቸው ኢጋንንት ናዳ ለቀቁባቸው። መጽሐፍ እንደሚነግረን ጮኸው መውጣታቸው ቀረና እነርሱኑ አስጮኹአቸው። እንደበረቱባቸው ለማሳየት ልብሳቸውን ቀደዱ። በሌላ አተረጓጎም ክብራቸውን ገፈፏቸው። በዚህም በተከበሩበት ምድር መሳቂያ አደረጓቸው። የቀረላቸው አንድና ብቸኛ አማራጭ ነፍሳቸውን ለማዳን መሮጥ ብቻ ነበር። በአቋራጭ ሊዋጉ የሞከሩት ችግር መልሶ ተዋጋቸው። ስለሆነም የገደምዳሜ መንገድ የድል ጎዳና አይደለም ለማለት በቂ ምክንያት ይኖረናል።

ኢየሱስ የተራመደው በማዕበሉ ላይ እንጂ በሥሩ አልነበረም። የመጣው በተቆጣው ውኃ ላይ እንጂ በድልድይ ተሻግሮ አልነበረም። በቀጥታ መጋፈጥና መፍትኼ ማምጣት ወይም በድፍረት መጋጠምና ድል ማድረግ ካልተቻለ በቀር አብዛኛው ችግር አይቀረፍም። ተራራው ዐይን ዐይኑን በማየት ወይም ዙሪያውን በመዞር አይነቃነቅም። ጠላትም ሰልችቶ ወይም ራርቶ ሥፍራ አይለቅም። ከመቼውም ጊዜ

ይልቅ የችግሩን ትልቅነት ለእግዚአብሔር ከመንገር ይልቅ የእግዚአብሔርን ትልቅነት ለችግሩ መንገር አስፈላጊ የሚሆነውም ያኔ ነው።

ዳዊት ያንን አድርጎአል።

ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም ሲወጣ ዐይኑን ጨፍኖ ዘው ያለ ወይ በሞቅታ ራሱን ያታለለ አልነበረም። እዚህ ጦሰኛ ሥራ ውስጥ የገባው በዓይኑ ፊት የተደቀነውን ታላቅ ችግር ባለመገንዘብም አይደለም። ገና ከመድረሱ " ማነው የሚገጥመኝ? ሰው ላኩና ይዋጣልን!" እያለ ሲደነፋ በጆሮው አድምጦታል። አንዴ ሳይሆን ይህንኑ ደጋግሞ ይል እንደነበረም መረጃ አለው። እንድ እንኳ እኔ አለሁ የሚል ጠፍቶ አገር ሙሉ ወንድ ሲንጸረጸርም አስተውሎአል። ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነውን ጀግና እንደ ሌሎቹ እስራኤላውያን በርቀት ሳይሆን በቅርበት አይቶታል። ከልጅነቱ ጀምሮ ጦረኛ መሆኑን ከሌሎች የዜና አውታሮች ሳይሆን ከታመነ የዜና ምንጭ ያውም ከንጉሡ አንደበት ሰምቶአል። ወደሜዳው ሲወጣ ጎልያድ " አንተን ወከሉህ? ቢያንስ ቢያንስ ድፍረትህን አደንቃለሁ" በሚል አስተያየት አልተቀበለውም። ነገር ግን እርግማን አወረደበት። አክሎም ሥጋውን ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እንደሚሰጥ በመግለጽ ሊያሸብረው ሞክሮአል። እንግዲህ ዳዊት ይህን ሁሉ ካየና ከሰማ በኋላ ነው የችግሩን ትልቅነት

ለእግዚአብሔር ከመንገር ይልቅ የእግዚአብሔርን ትልቅነት ለችግሩ መንገር አስፈላጊ እንደሆነ የወሰነው። በዚሁም መሠረት ዳዊት የሚያመልከው ሁሉን ቻይ አምላክ ካጋጠመው ተግዳሮት በላይ መሆኑን ለመግለጽ ጎልያድን እንዲህ ብሎታል። “ አንተ የጦር መሳሪያ ይዘህ ብትመጣብኝም እኔ ግን የተገዳደርከውን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ይዤ እመጣብሃለሁ። እርሱ ደግሞ አንተን አሳልፎ ይሰጠኛል። ስለሆነም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት የሚሰጠው የኔ ሳይሆን ያንተ ሥጋ ነው!”።

ሰ) ትክክለኛ ርምጃ መውሰድ

የአየር ትንበያ ባለሙያ የሆነው አብሮ አደግ ጓደኛዬ ከዓመታት በፊት አንድ ገጠመኙን አጫውቶኛል። ይህንን ያየው ከመኖሪያው ብዙም ሳይርቅ በሚገኝ የሞተር ቢስክሌት መለማመጃ ቦታ ነበር። ሰዉዬው አነዳዱን ሲማር ሳለ በድንገት ከፊት ለፊቱ መኪና ይመጣበታል። ይህን ጊዜ አስተማሪው እንደነገረው መጀመሪያ ፍጥነት መቀነስ ቀጥሎም ፍሬን መያዝ ነበረበት። እርሱ ግን በመደናገጥም ይሁን በመዘንጋት የነዳጅ መስጫውን ተጫነው። ከዚያ በኋላ የሆነውን አላስታውስም። ግን ከአደጋ እንዳላመለጠ መገመት ይቻላል። እናም ትክክለኛ ርምጃ አልወሰደም ማለት ነው። እንዲያውም ነዳጅ መስጠቱ ችግሩን ከመቅረፍ ይልቅ የአደጋውን ይዘት ጨምሮታል። ይህን ታሪክ ከሰማሁ ከሦስት

አሥርት ዓመታት በሁዋላ ደግሞ እኔ ራሴ ተመሳሳይ ስሕተት ፈጽሜያለሁ።

ነገሩ እንዲህ ነበር።

ይህ የተፈጠረው የምነዳውን መኪና ቦታ ፈልጌ ለማቆም እየሞከርኩ ሳለ ነው። ችግሩ ግን ለመጠለል እጅግ ጠባብ የሆነች ሥፍራ ነበር ያገኘሁት። እናም በዔሊ ፍጥነትና በነብር ጥንቃቄ ወደ ኋላ ተስቤ አቋቋሜን አመቻቸሁ። ከመውረዴ በፊት እንደሚገመተው ፍሬን መያዝ ነበረብኝ። ያንን አደረግሁ ብዬ ግን የነዳጅ መስጫውን በሙሉ ኃይሌ ረገጥኩት። ስሕተቴ የገባኝ የሁለቱ መኪኖች ግጭት የፈጠረው ድምፅ ጆሮዬ ላይ ሲያስተጋባ ነበር። አሁን ሳስበው ዝም ብዬ ብተወው እንኳ ያ ሊሆን እንደማይችል እገምታለሁ። ፍጥነቴ ቀስስተኛ እንደመሆኑ መጠን ይነካኩ ነበር እንጂ አይጋጩም። ትክክለኛውን እርምጃ ባለመውሰዴ ግን የያዝኩትን መኪናም ሆነ የሌላውንም ንብረት ጎዳሁ።

ዳዊት ጎልያድን ያሸነፈበትን ምሥጢር ስንመረምር ይህንኑ የሚደግፉ በርካታ ነጥቦችን ለማግኘት ዕድሉ አለን።። ግን በእግዚአብሔር ስም እንደሚዋጋ መግለጹን ቀዳሚ ብናደርግ የተሻለ ይሆናል። የድሉ ቁልፍ እሱ ነውና። ከዚያ በኋላ ግን የሚከተለውን ማንሳት እንችላለን። በርቀት ሊመታው መወሰኑ አንዱ መልካም ጎኑ ነው። ትክክለኛ ርምጃም ነበር። “ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው” ብሎ

ጎልያድን በጥፊ ለመምታት አልከጀለም። ስድስት ክንድ ቁመት ያለውን ግዙፍ ሰው ሊታገል አልሞከረም። ግን አንበሳና ድብን ደጋግሞ በመታበት ስልት በርቀት ወንጭፎ መትቶታል። የርምጃውን ትክክለኛነት የሚያሳይ ሌላ ነጥብ ነው። በዚያ ላይ ለመምታት ያነጣጠረው ግንባሩ ላይ እንጂ ሌላ ቦታ አልነበረም። ያ ሥፍራ ደግሞ በምንም የማይተካ ቁልፍ የአካሉ ክፍል ነበር። ጭንቅላቱ ከተመታ የማዘዣ ጣቢያው ተመታ ማለት ይቻላል። ባለንበት ክፍለ ዘመን ሽምቅ ተዋጊዎች ከመንግሥት ሠራዊት ጋር ሲፋለሙ ከሚጠቀሙባቸው ውጤታማ የውጊያ ስልቶች አንዱ የግዙፉን ሠራዊት የማዘዣ ጣቢያ አስቀድሞ መምታት ነው። ያ አካባቢ ከተደመሰሰ አልያም ከተተራመሰ ከዚያ በኋላ ውጊያው ለነርሱ አስቸጋሪ አይሆንም። ለምን ቢሉ ተጋጣሚያቸው መሪና ተመሪ በማጣት ይፍረከረካል። አዛዥና ጭፍራ ርስ በርሱ የሚተላለቅበት ሁኔታም አለ።

ዳዊት ርቀቱን የመረጠበት ሌለኛ ምክንያት ሁለተኛ ዕድል ለማግኘትም ይሆናል። ምናልባት በመጀመሪያው ጠጠር ቢስተው ወይም ሌላ የአካል ክፍሉን ቢመታው ዳግም ለመወንጨፍ በቂ ጊዜና ርቀት ነበረው። ይህን ለማለት የሚያስደፍሩን ሁለት ምክንያቶች አሉን። የመጀመሪያው ለንጉሥ ሣዖል ያቀረበው የሥራ ልምድ ማመልከቻ ነው። አንበሶችና ድቦችን ደጋግሞ ስለመታበት ሁኔታ ሲያብራራለት

እንዲህ ብሎታል። “ መትቼ የወሰዱትን ጠቦት አስመልሳቸው ነበር፤ እኔው ላይ ከተነሡም ጉሮሮአቸውን ይዤ እገድላቸው ነበር።” ዳዊትና በጎቹን የተተናኮለ አንበሳ ወይም ድብ አንዳንዴ ሁለት ጥቃት ይጠብቀው ነበር ማለት ነው። የመጀመሪያውን ቀምሶ የነከሳትን ተፍቶ ከሄደ በዚያው ያልፍለታል። ተናደድኩ ብሎ ተመልሶ ዳዊት ላይ ከጮኸም በሁለተኛው ምት ያሸልባል። ሁለተኛና የመጨረሻው ምክንያት ደግሞ ከወንዝ የወሰዳቸው ጠጠሮች ቁጥር ነው። አምስት ናቸው። ይህም በትንሹ አምስት ጊዜ እንኳን ሊመታው ዝግጁነት እንደነበረው ያመለክተናል። እነዚህ ሁሉ ተዳምረው የማሸነፍ ዕድሉን አስፍተውለታል። ትክክለኛ ርምጃ መውሰዱ ግን የድሉ ቁልፍ ሆኖ ይጠቀሳል።

ምንጊዜም ማዕበሉን ለመቋቋም መሞከር ተገቢ ነው። ሕፃኑ ሁልጊዜ ሲያለቅስ አይኖርም። ከፍ ሲል ማልቀሱን ያቆምና እንደሱ የሚያለቅሱትን ታናናሾች ማባበል ይጀምራል። በጌታ ቤትም ይኸው ነው፡ የሚጠበቅም ነው። ወጀቡ እጅግ ሲያይል ደግሞ መምህሩን መቀስቀስ ትክክለኛ ርምጃ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ወጀቡ እንደበረታ ከአቅም በላይም እንደሆነ ተረድተው በጭንቀት ጮኸዋል። ግን መምህራቸው የሚጠብቀው የዕለቱ ፈተና ትክክለኛ መልስ ጩኸት ሳይሆን እሱ ሲያደርግ እንዳዩት ያለ ተግባራዊ ርምጃ ነበር። አጋንንትን ሲያወጣ ዐይተው እነርሱም ሄደው

አጋንንትን አውጥተው የለም እንዴ? አርፍዶስ ቢሆን ጴጥሮስ በውኃ ላይ አልተራመደም እንዴ?

የዘመናችንም ዓይነተኛ ችግር ይኸው ነው። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሲፈጠር ብድግ ብለው በፍቅር የሚገሥፁ ሰዎች አይታዩም። ከሁለቱ ተፋላሚዎች ወደ አንዱ ጎራ መወገን ነው የተለመደው። በስብከት ስም ከመድረክ ብዙ ቆሻሻ ሲወረወርስ? በቁጣ ብድግ ብሎ "የለም፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ አያስተምርም" ለማለት የሚደፍር አላየንም። ትክክለኛው ርምጃ ግን እርሱ ነው። በርግጥ ዋጋ ያስከፍል ይሆናል። ይሁና። ዋጋ ያልተከፈለበት ሕይወት አይደለም እኮ የምንኖረው።

ደጋግመን ባነሣነው ታሪክ እንደተመለከተው ጴጥሮስ በውኃ ላይ ለመራመድ ወስኗል። አብሮ ተማሪዎቹ የነበሩት አስራ አንዱ ግን ተመልካች መሆንን መርጠዋል። ይህ በቀላል ስሌት ዘጠና ሦስት ከመቶ መሆኑ ነው። ስሌቱ አሁንም ይሠራል። በታላላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የተመልካችና የቲፎዞ ችግር ገጥሞን አያውቅም። ትክክለኛው ርምጃ ግን ዳር ቆሞ ለሌሎች ማጨብጨብ ሳይሆን ወደውጊያው ቀጠና ገብተን የምንችለውን ማድረግ ነው። ታዋቂው ሰባኪ ቫንስ ሔቨነር "የተጠራነው ለውድድር እንጂ የሌሎችን ነጥብ ለመቁጠር አይደለም" ይሉ ነበር። ምንኛ እውነት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን

ስለሚጠብቀው መከራ በመንገርና የሚከተለውንም ክብር በማብራራት በብዙ መልኩ አዘጋጅቶአቸዋል። በኃጢአተኞች እጅ እልፎ እንደሚሰጥ እንደሚሰቀልና ከዚያም ከሞት እንደሚነሳ ደጋግሞ የነገራቸው መረጃ ነው። በተለይም አልፎ በተሰጠባት ምሽት በዚያው ዕለት የሚደርስበትን መከራ ዘርዝሮ ነግሯቸዋል። መጽሐፍ እንደሚነግረን ቀደም ብሎም ይህንኑ ሲነግራቸውና ምክንያቱንም ሲያብራራላቸው ነበር። በዕለቱም ያንኑ ደግሞ በስፋት ከገለጸላቸውና ከጸለየላቸውም በኋላ ነበር ዘምረው ወደ ጌተሰማኒ የአትክልት ሥፍራ ያቀኑት። በዚያም ወደ መከራ እንዳይገቡ ተግተው እንዲጸልዩ ደጋግሞ መክሮአቸዋል። ከነርሱ ዘወር ብሎ ጸልዮ ሲመለስ ግን ሁለት ጊዜም ደክመውና ተኝተው ነው ያገኛቸው። እናም ቢያንስ ቢያንስ ከፈተና ለማምለጥ ለአንድ ሰዓት ተግተው እንዲጸልዩ በድጋሚ አሳስቦአቸዋል። ግን ያንን ዕድል ቢያገኙም አልተጠቀሙበትም። በመጨረሻ ደግሞ አሁን ማረፍ እንደሚሻል ነግሯቸው ሳለ ነቅተው ኢየሱስን ለመያዝ ከመጡት ጋር ግብግብ ጀመሩ። እንዲያውም ስምዖን ጴጥሮስ ሰይፍ መዝዞ የአንዱን ጆሮ እስከመቁረጥ ጨከነ።

ኢየሱስ በዚህ የተለመደ የሥጋ ለባሽ የመከላከል ስልት ፈጽሞ አልተስማማም። ምክንያቱም ትክክለኛ ርምጃ አልነበረም። ስሕተቱ ደግሞ በጸሎት ትጉ ተዋጉ ሲባል

መተኛት አሁን ዝም ብላችሁ የሚሆነውን ተመልከቱ ሲባል ደግሞ ለውጊያ መነሳት ሰይፍም መምዘዝ ነው። በርግጥም ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ከከሳሾቹ ለማዳን የወሰዱት ርምጃ ትክክል አልነበረም። ከሚጠብቀው ክብር የሚያዘገየው እንጂ ወደዚያ የሚገፋው አልነበረማ። ለዚህም ነው የሊቀካህናቱ ባሪያ ሳይጠይቀው ጆሮውን ነክቶ የፈወሰው። አንዳንዴ እኛም ወገኖችን ያገዝን እየመሰለን ምናልባት እግዚአብሔር ካየላቸው ከፍታ እያወረድናቸው ይሆን? እነርሱስ በተራቸው ያዳኑን መስሏቸው እያስረፈዱብን ይሆን? ሁለቱም ረብ የለሽ ነው። የእግዚአብሔር ድንጋጌ ከቶም አልተለወጠምና።

መጀመሪያ መስቀል በኋላም አክሊል!

መጀመሪያ መከራ ቀጥሎም ክብር!

እርሱ ይርዳን!

መደምደሚያ

ጥሪአችን ወደ ማዶ መሻገር ነውና በደህና እንደርሳለን።

ይህ መልካሙ ወሬ ነው።

አብሮት ደግሞ ሌላ ሰበር ዜና አለ። ማዕበል ሊነሣ ይችላልና ተዘጋጁ የሚል። ማዕበል አልባው ጉዞ አሰልቺ ነው። ውኃው ሲናወጥ ግን ተሳፋሪዎች ሁሉ ፊታቸውን ወደ ጋራ ጠላታቸው ያዞራሉ። የርስ በርስ መናከስ ጋብ ይላል። ጉልበቶች መሬት ይይዛሉ። የአምላክን ፊት መፈለግ ዋነኛው አጀንዳ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ማዕበል ባለውለታችን ነው!

ማዕበሉ የሚነሣው ከውጭ ብቻ አይደለም። ከውስጥም ነው። ለምሳሌ የጤና እክል ያጋጠመ እንደሆነ ነውጡ ከውስጥ ጀመረ ማለት ይቻላል። አያስጠነቅቅም። በድንገት ነው የሚመጣው። ተደርቦና ተደራርቦም ሊከሰት ይችላል። በምድር ገጽ ለሚኖር የአዳም ዘር ሁሉ የማይቀር ዕዳ ነው። መልካም ጉዞ!

አንዳንዶች እንደሚገምቱት ክርስቲያን መሆን ከማዕበል ነፃ መሆን አይደለም። ግን ምርጫ ነው። በማመቻመች ከጊዜአዊው ማዕበል መትረፍ ይቻል ይሆናል። ያለበለዚያ ጌታ ቢኖርም ወጀብ አይቀርም። የማለፍ ተስፋ ግን አለ። ያኔ ማዕበል ይናፈቃል። ተስፋንም ያስናፍቃል!

ቢያንገላታም እንኳ ማዕበል የራሱ በረከቶች አሉት። ያስጠጋናል። ጌታ ሆይ ያሰኘናል። በመከራው ውስጥ የመሠራትን ታላቅ ዕድል ያጎናጽፈናል። በጻድቃን ጉባዔ እውነተኛውና አስመሳዩ ማን እንደሆነም ገልጦ ያሳየናል።

ማዕበሉን ለመሻገር ራስን ማዘጋጀት ብልህነት ነው። ቀድሞ መጸለይም አስተዋይነትን ያመለክታል። ድምፆችን መለየትና የተሻለውንም መምረጥ የግድ የሚሆነው ያኔ ነው። ወጀቡን ለማለፍ አመለካከትን መቀየር አማራጭ የለሽ

መፍትኼ ሆኖ ይቀርባል። እስከመጨረሻው ጠንክሮ መዋጋትና ትክክለኛ ርምጃ መውሰድንም የግድ ይላል።

ግን ይታለፋል።

ወደ ማዶም ይደረሳል።

መልካም ቀዘፋ!

ማሰናበቻ

ባለፉት ሃያ ዓመታት በበርካታ መጻሕፍት ዝግጅት ሥራ ላይ የመሳተፍ አስደሳች ዕድል ገጥሞኛል። ጽፌአለሁ፣ ተርጉሜአለሁ፣ ገጥሜአለሁ። እንዲሁም አርሜአለሁ። ከነዚያ መሃል የሕትመት ብርሃን ያዩና አንባቢያን እጅ የገቡት ወደ ሠላሳ ደርሰዋል። በነፃ የተቀበልኩትን በነፃ ለመስጠት ጊዜው ደርሶ ይኸው ዛሬ አንዱን ለማንበብ በቁ። አመሰግናለሁ። እባክዎ ለሌሎችም ያስነብቧቸው። ወደድረገጻችን ያመልክቷቸው። ራሳቸው ፈቅደው ድጋፍ ካላደረጉልን በስተቀር ለጥበብ ሥራዎቻችን ዋጋ እንደማንጠይቅም በግልጥ ይንገሩልን። ደግሞም የበለጠ መሥራት እንድንችል ይጸልዩልን።

t.me/BooksandYou